**የጎልማሶች ሰንበት ትምህርት: የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያ**

*መደበኛ ዕትም*

# መጋቢነት፡ ልብ አነሳሹ ሞተር

የትምህርቱ አዘጋጆች፡- **ጆን ኤች. ኤች. ማቲዉስ**

**ዘላለም አስረስ እንደተረጎመው**

ይህ የጎልማሶች ሰንበት ትምህርት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያ የሚዘጋጀው በሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን ዋና መስሪያ ቤት በሆነው በጀነራል ኮንፍረንስ ውስጥ ሆኖ፤ የጎልማሶች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያን በሚያዘጋጀው ቢሮ ነው፡፡ መምሪያዎቹ የሚዘጋጁት የጀነራል ኮንፈረንስ አስተዳደር ኮሚቴ ንዑስ ኮሚቴ በሆነውና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መምሪያዎችን በሚያሳትመው የሰንበት ትምህርት ሕትመት ቦርድ ነው፡፡ የታተመው መምሪያ በውስጡ ዓለም አቀፋዊ የሆነ የምዘና ኮሚቴ ሀሳቦችንና የሰንበት ትምህርት ሕትመት ቦርድን ማረጋገጫ ስለሚያንጸባርቅ የአዘጋጁን (የአዘጋጆችን) ሀሳብ ብቻ የሚወክል አይደለም፡፡

*በተለየ ካልተጠቀሰ በቀር በዚህ ሰንበት ትምህርት ጥቅም ላይ የዋሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሙሉ የተወሰዱት ከአዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው፡፡*

*በኢትዮጵያ አድቬንቲስት ማተሚያ ቤት ታተመ*

*1ኛ ሩብ ዓመት*

ከታህሳስ 21-*መጋቢት* 21፣ 2010 ዓ.ም

# ማውጫ


| አርዕስት | ቀን | ገጽ |
|---|---|---|
| 1. የቁሳዊው ነገር ተጽእኖ | ከታህሳስ 21-27 2010 ዓ.ም | 6 |
| 2. ማየት፣ መመኘት፣ ማድረግ | ከታህሳስ 28-ጥር 4 | » 17 |
| 3. እግዚአብሔርን ወይስ ቁሳዊውን ሀብት? | ከጥር 5-11 | » 28 |
| 4. ከዓለማዊ አካሄዶች ማምለጥ | ከጥር 12-18 | » 38 |
| 5. መጋቢነት በድኅረ ኤደን | ከጥር 19-25 | » 48 |
| 6. የመጋቢው ምልክቶች | ከጥር 26-የካቲት 2 | » 59 |
| 7. ከእግዚአብሔር ጋር በታማኝነት መመላለስ | ከየካቲ 3-9 | » 70 |
| 8. የአሥራት ተጽእኖ | ከየካቲት 10-16 | » 81 |
| 9. የምስጋና ስጦታዎች | ከየካቲት 17-23 | » 92 |
| 10. የመጋቢነት ሚና | ከየካቲት 24-30 | » 102 |
| 11. የእያንዳንዱን ቀን ውሳኔ የሚሻው-- ዕዳ | ከመጋቢት 1-7 | » 112 |
| 12. የመጋቢው ልማዶች | ከመጋቢት 8-14 | » 123 |
| 13. የመጋቢነት ውጤቶች | ከመጋቢት 15-21 | » 133 |

# መግቢያ

## የመጋቢው ክርስቲያን ሕይወት

እንደ ክርስቲያን የመለወጣችንን አስፈላጊነት ከመመልከታችን አስቀድሞ የምንገኝበትን ኃጢአተኛ ሁናቴ ማስተዋል ግድ ይላል፡፡ ልባችን የናፈቀው ለውጥ ተገቢውን አካሄድ ተከትሎ ገቢራዊ መሆን የሚችለው በእኛ ውስጥ በሚሠራው ክርስቶስ ብቻ ነው፡፡ አምላካዊው ሥራ በውስጣችን ከሚገለጥባቸው መንገዶች አንዱ ደግሞ መጋቢነት ነው፡፡ ምንም እንኳ መጋቢነት በዘርፈ ብዙ የክርስትና ህይወት ገጽታዎች የተከበበ ቢሆንም ነገር ግን *ተጨባጭ የሆኑ* እና *ተጨባጭ ያልሆኑ* ሐብትና ንብረቶችን ለእግዚአብሔር ክብር ማስተዳደር የሚል ሰፋ ያለ ፍቺ ልንሰጠው እንችላለን፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተደጋግሞ እንደ ተወሳው መጋቢነት ከዓለማዊነት (ከፍቅረ ንዋይ) አደጋ ልንጠበቅ የምንችልበት ብርቱ መሣሪያ ነው፡፡ እንደውም የነፍሳት ጠላት በፊታችን ከሚሸርባቸው ታላላቅ መንፈሳዊ ሴራዎች ልንጠበቅ ከምንችልባቸው መንገዶች አንዱ ይኸው መጋቢነት ነው፡፡ ሐብትና ንብረት ውሎ አድሮ ለዛውን የሚያጣ ከንቱ ዓለማዊ ነገር መሆኑን ብዙዎች ማስተዋል ሲሳናቸው ይታያል፡፡ አያሌ ወገኖች የሚጠፉት ከዓለም መፋታት አልሆንላቸው እያለ የመሆኑ እውነታ በእጅጉ አሳዛኝ ነው፡፡ "በዓለም ያለው ሁሉ የዐይን አምሮትና የኑሮ ትምክህት ከዓለም እንጂ ከአብ የሚመጣ አይደለም" (1ዮሐ. 2፡16)፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሁሉ በሕይወታችን ውስጥ በሚኖሩት የመጋቢነት መርኅዎች--ማለትም መሻታችንን በመግዛት መወገድ ይችላሉ፡፡

ዓለምን ከመውደድ በተቃራኒ በሚገኘው ነጻነት እየተመላለስን እግዚአብሔር እንደሚፈልግብን እንዴት መኖር እንዳለብን ይኸው ፈርጀ ብዙ የመጋቢነት ጽንሰ

ሃሳብ ሊያስተምረን የሚችለውን ትምህርት በዚህ ሩብ ዓመት ጥናታችን በጥልቀት ለመመልከት እንሞክራለን፡፡ መጋቢነት የሱስን በየዕለቱ የመከተልን ትርጉም በተጨባጭ የምንገልጽበት፣ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር እና በክርስቶስ የተሰጠንን እውነት የምናሳይበት መንገድ ነው፡፡ እግዚአብሔር እኛን አስቀድሞ ከመውደዱ የተነሳ እነሆ መጋቢዎቹ ሆነናል፡፡

በየዕለቱ በእኛ የሚገለጠው የመጋቢነት ህይወት ጠባይና አኳኋናችንን፣ መለወጣችንን፣ ቁርጠኝነታችንን እንዲሁም መሻታችንን መግዛታችንን ጨምሮ ሌሎች አያሌ አንኳር ነገሮችን አካቶአል፡፡ በምናደርገውም ሆነ በምንናገረው በእያንዳንዱ ነገር ከየሱስ ጋር ብርቱ ትስስር ፈጥረንና ከራስ ወዳድነት አረንቋ ተላቀን የእግዚአብሔር ታማኝና እምነት የሚጣልባቸው አገልጋዮች እንድንሆን ተጠርተናል፡፡ በዚህ ሩብ ዓመት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን የመጋቢነት ህይወት አስደሳች የጽድቅ ኑሮ እንደሚያቀዳጅ ከክርስቶስ አስተምህሮዎች ለመመልከት እንሞክራለን፡፡ የወንጌልን ሥራ በገንዘባችን እየደገፍን ሥራውን ወደ ፍጻሜ በማምጣት የእግዚአብሔርን ንብረት ስለ አምላካዊው ክብር እንዴት ማስተዳደር እንዳለብን እንማራለን፡፡

አሁን የእግዚአብሔር መጋቢዎች "በመስታወት ውስጥ እንደሚታይ በድንግዝግዝ" (1ኛ ቆሮ. 13፡12) ቢያዩም የሱስ ግን በግልጽ ይመለከታል፡፡ ሥራውን እንድንሠራ ዐደራ ይለናል፡፡ ምንም እንኳ ይህች ምድር አማላይ ብትሆንም መክሊታችንን፣ ገንዘባችንን፣ ጤናችንና አካባቢያችንን በአግባቡ የማስተዳደርና የመምራት ኃላፊነቱ ዛሬም ለእኛው ተትቷል፡፡ የዚህ ሩብ ዓመት የሰንበት ትምህርት ጥናታችን መጋቢነትን እንደ ጽድቅ ማግኛ ምጸዋት አድርገን ለማለም በመሞከር ፋንታ--ይልቁንም አስቀድሞውኑ በውስጣችን እንዳለ የመንፈስ ፍሬነት በማስተዋል፤ ይህን የተሸከምነውን ኃላፊነት በእግዚአብሔር ጸጋ እንዴት ከዳር ማድረስ እንደምንችል በቂ ዕውቀት ለመገብየት እንዲያስችለን ሆኖ ተቀርጾአል፡፡

የክርስቲያን መጋቢ ህይወታችን እግዚአብሔር ለዓለም ያለውን ጸባይ ያንጸባርቃል፡፡ ምድራዊውን ወግና ልማድ ከመከተል በተቃራኒ ለመጽሐፍ ቅዱስ መርኅዎች ለመቆም ወኔው ያላቸው ወገኖች ህይወት--በውበት የተሞላ፣ በደስታ የተፍነከነከና

እግዚአብሔርን እየመሰለ የሚያድግ ነው፡፡ እያንዳንዱ ሰው ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌለው ህይወት እንዲኖር እየተፈተነ የሚገኝ ሲሆን፤ ይኸው ውጊያ በግልጽም ሆነ በስውር እነሆ በዙሪያችን እየተካሄደ ይገኛል፡፡ እኛ እንደ ክርስቲያን--በተለይም እንደ ክርስቲያን መጋቢነታችን እነዚህን ፈተናዎች የምናመልጥበትን መንገድ ብቻ አልተጠቆምንም፤ ይልቁንም ኃይሉንም ተችረናል፡፡

በቅርቡ እውን በሚሆነው የምድር ታሪክ መደምደሚያ የእያንዳንዱ ሰው ምርጫና የግል ውሳኔ "'ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ክፉዎች፤ ከእኔ ራቁ!'" (ማቴ. 7:23) ወይም " 'ደግ አድርገሃል፤ አንተ መልካም ታማኝ አገልጋይ፤ በትንሽ ነገር ላይ ታማኝ ስለ ሆንህ በብዙ ነገር ላይ እሾምሃለሁ፤ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ!'" (ማቴ. 25፡23) -- ከሚሉት ከእነዚህ ሁለት ጥቅሶች በአንዱ መዋሉ አይቀሬ ነው፡፡

በዚህ ሩብ ዓመት የሰንበት ትምህርት ጥናት በመጋቢነት ጽንሰ ሃሳብ ዙሪያ የቀረቡት እነዚህ ትምህርቶች በእርግጥም አረማመዳችን " 'ወደ ጌታህ ደስታ ግባ!' " ወደሚለው ጎዳና እንዲያቀና ያስችሉ ዘንድ ጸሎታችንና ተስፋችን ነው፡፡

ጆን ኤች. ኤች. ማቲዩሰ ከአንድሪውስ ዩኒቨርሲቲ በሚኒስትሪ የዶክትሬት ዲግሪ ያላቸው ሲሆን በፓስተርነት የአገልግሎት ዘርፍ በፍሎሪዳ፣ አላባማ፣ አይዋ፣ ሚዙሪ፣ ቴኔሲ እና ነብራስካ--የአሜሪካ ግዛቶች አገልግለዋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በሰሜን አሜሪካ ዲቪዥን የመጋቢነት ዘርፍ ሥራ መሪ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡

# አንደኛ ትምህርት

ከታህሳስ 21 -27

# የቁሳዊው ነገር ተጽእኖ

**ሰንበት ከሰዓት**

**ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡**-- 1 ዮሐ. 2:16-17፣ ሉቃ. 14:26–33፣ 12:15–21፣ ዘዳ. 8:10–14፣ 1 ጢሞቴ. 6:10፣ ዮሐ. 15:5፣ ገላ. 2:20፡፡

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡-**

"መልካም፣ ደስ የሚያሰኝና ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታወቁ ዘንድ በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ" *(ሮሜ 12፡2)፡፡*

አምላካዊው ቃል "ይህን ዓለም አትምሰሉ" እያለ ምክሩን ለሰብዓዊው ዘር እየለገሰ ቢገኝም ነገር ግን የዓለማዊው ቁሳዊ ሐብትና ንብረት ምኞት--የማባበልና የመማረክ ተጽእኖው እጅግ ብርቱ እንደመሆኑ፤ እኛ ከምናስበው በላይ በሥርዓት ከመመላለስ ሊገታን የሚችል ኃይል አለው፡፡ ቢደኸዩ ወይም በሐብት ቢበለጽጉ--ትኩረታቸውን ከቁስ አካላዊው ነገር ባሻገር ያደረጉ በጣም ጥቂት ሕዝቦች አሉ፡፡ ክርስቲያኖች ከእነዚህ ጥቂት ሕዝቦች መሃል ይካተታሉ፡፡

ሐብታም መሆን ወይም ብዙ ሐብት ለማካበት ጠንክረው ሠርተው ከፍ ያለው ማግ ላይ መውጣት፣ ለራስም ሆነ ለተወዳጅ የቤተሰብ አባላት ምቾት ማምጣት ስህተት የለበትም፡፡ ነገር ግን ፍቅረ ንዋይ አቅላችንን ሲያስተንና ብር የደም ስር ሲሆን ያኔ በዲያብሎስ ወጥመድ እንወድቅና በእርግጥም "ይህን ዓለም" እንመስላለን፡፡

ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ ዓይነቱ ሁሉ በእጄ፣ ሁሉ በደጄ የተትረፈተፈ ህይወት ቁልፉ ንዋይ ብቻ ነው--የተሰኘውን ጽንሰ ሀሳብ ዓለም ሲያስተጋባ ይደመጣል፡፡ ሰይጣን አድብቶ ታማኝነታችንን ከእጁ ለማስገባት የሚጠቀምበት ጭምብል ገንዘብ ነው፡፡ የክርስቲያኖችን ምርጫ ከሚዋጋባቸው መሣሪያዎቹም አንዱ ይኸው ብልጭልጭ ነገር ነው፡፡ ለነገሩ ዛሬ ከምንገኝበት ሁኔታ አኳያ ገንዘብን የሚጠላ ማን ነው? ገንዘብ ዛሬ የምንፈልገውን በፍጥነት እጃችን በማስገባት ደስ ቢያሰኘንና ቢያረካንም ውሎ አድሮ ጥልቅ ለሆነው ውስጣዊ ፍላጎታችን ጉድለት ምላሽ መስጠት ግን አይሆንለትም፡፡

## እሁድ ታህሳስ 22

# የዚህ ዓለም አምላክ

እነሆ ገንዘብ ለሰብዓዊው ዘር አምላኩ፣ ተብለጭላጩ ነገር ደግሞ ኃይማኖቱ በሆነበት ዓለም እንገኛለን፡፡ እጅግ የተራቀቀውና የሚያነሆልለው ተብለጭላጭ ነገር ጊዜያዊ ከለላ ከመሆን ባሻገር ዘላቂ ደኅንነት ሊያስገኝልን አይችልም፡፡

የአንድ ሰው ትኩረት ከመንፈሳዊው ተጨባጭ ነገር ባሻገር ባለው ምድራዊ ግዑዝ፣ ብልጭልጭ ሐብትና ንብረት ምኞት ላይ ብቻ ተወስኖ መቅረት--ዓለምን ለመምሰል ዓይነተኛ ፍቺ መሆን ይችላል፡፡ ምንም እንኳ ተብለጭላጩ ቁሳዊ ነገር ምድራዊ ዋጋ ሊኖረው ቢችልም እኛን ሊቆጣጠር ግን አይገባም፡፡ "ገንዘብን የሚወድ፣ ገንዘብ አይበቃውም፣ ብልጽግናም የሚወድ በትርፉ አይረካም" (መክ. 5፡10) እንደተባለው በዚህ ዓለም የቱንም ያህል የተትረፈረፈ ሐብት ብናካብት አብልጠን

ከመመኘት ወደ ኋላ አለማለታችን አንዱና ዋንኛው ችግር ነው፡፡ እንደውም ከቀድሞው የበለጠ ለማግኘት አብልጠን በገፋን ቁጥር ፈጽሞ ወደ እርካታ መምጣት የማንችል እንሆናለን፡፡ ወጥመድ ሊሆኑብን በሚችሉ ጉዳዮች ዙሪያ ተነጋገሩ፡፡

**የሚከተሉት ጥቅሶች ትኩረት ልንሰጠው ስለሚገባው ፍሬ ነገር አስመልክቶ ምን ይላሉ 1ዮሐ. 2፡16-17**

-----------------------------------------------------------------------------------------

**በተጨማሪ--የሱስ በሉቃ. 14፡26-33 መልእክቱ አንድ ክርስቲያን ብርቱ አጽንኦት ሊሰጠው ስለሚገባው ነገር ምን እያለን ነው?**

-----------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------

ገንዘብን እንደ ጣኦት እያመለኩ ህይወታቸው በተጨባጭ በፍቅረ ነዋይ አዙሪት ስር የወደቀ ሰዎች በእርግጥም ይህ ውሳኔያቸው የሚያስከፍለውን ዋጋ ሊያጤኑ የተገባ ነው--“ሰው ዓለሙ ሁሉ የእርሱ ቢሆንና ነፍሱን ቢያጣ ምን ይጠቅመዋል?” (ማር. 8፡36)፡፡

“ክርስቶስ ወደዚህ ምድር ሲመጣ ሰብዓዊነት በፍጥነት አሽቆልቁሎ የአንድ ማኅበረሰብ መሰረት የሚባሉ እሴቶች የመሸርሸር አደጋ ገጥሟቸው ነበር፡፡ ህይወት የታይታና ኢ-ተፈጥሮአዊ ገጽታ ይዞ ነበር... በዓለም ዙሪያ የነበሩ ኃይማኖቶች በሰብዓዊው አእምሮና ነፍስ ላይ የነበራቸውን ተጽእኖ አጥተው ነበር፡፡ ይቀርቡላቸው በነበሩ ልቦለድ ተረቶችና በሬ ወለደ አስተምህሮዎች የተንገፈገፉት ሕዝቦች ከእንዲህ ዓይነቱ ሁናቴ ለመውጣት ከነበራቸው ብርቱ ምኞት የተነሳ የእምነት ኪዳናቸውን እያፈረሱ ፊቶቻቸውን ወደ ዓለማዊው ብልጭልጭ ነገር አዞሩ፡፡ ዘላለማዊውን ነገር ከአእምሮአቸው እያወጡ ለጊዜው ብቻ ኖሩ” —Ellen G. White, *Education*, pp. 74, 75.

**ሰዎች ዘላለማዊውን ነገር ከአእምሮአቸው እያወጡ ለጊዜው ብቻ የመኖራቸው ነገር ዛሬስ የተለመደ አይደል?**

**ሐብትም ሆነ ንብረት ማፍራት የማይፈልግ ማን አለ? ጥያቄው ግን እንዲህ ነው፡ ያፈራነው ሐብትና ንብረት ምናልባት ብዙ ሊባል የማይችል እንኳ ቢሆን ነገር ግን-- ማን ማንን እየገዛ እንደሆነ ማወቅ የምንችለው እንዴት ነው? ንብረታችን እኛን ወይስ እኛ ንብረታችንን? እኛን በብቸኝነት እንዲገዛ የተገባው ማን ነው? ለእርሱ እየተገዛን ለመሆኑ እርግጠኞች መሆን የምንችለውስ እንዴት ነው?**

## ሰኞ **ታህሳስ 23**

# ኀተራዎችን መሙላት

በሉቃስ **12፡15–21 የተሰጠን መልእክት ምን ይመስላል? መቼም አንድ ሰው የግድ ሀብታም መሆን ባይጠበቅበትም በመልእክቱ የቀረበውን መርኅ ገቢራዊ ማድረግ የሚችለው እንዴት ነው?**

-------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------

ሀብታም ሆንን ወይም ደሃ ቁሳዊውን ነገር ለማፍራት የሚኖረን ብርቱ ምኞት የአእምሮአችንን ትኩረት ሚዛን ከሚደፋው የከበረ ነገር ላይ እያማለለ ወስዶ በጊዜያዊው፣ በብልጭልጩና በአላፊው ምድራዊ ነገር ላይ እንዲተከል የማድረግ ኃይል አለው፡፡

እንደ ጥንቱ ሁሉ በዚህ ዘመን ከንጹህ ወርቅ ወይም ብር ለተሠራ ምስል አጎንብሰን ባንሰግድም--ወርቅና ብር የማምለክ አደጋ ውስጥ ልንወድቅ ግን እንችላለን፡፡

ምንም እንኳ ህይወት ሀብትና ንብረት እንዲፈራበት ብቻ የተበረከተ ገጸ በረከት ባይሆንም ምሳሌው ለአብዛኛው የዓለማችን ክፍል ገጣሚ ነው፡፡ ነጋዴዎች ለገበያ የሚያወጧቸው አማላይ ሸቀጦች እዚህ ቀረሽ ሳይባል በዓለማቀፍ ደረጃ የገበያተኛውን ቀልብ ከመዳፍ ያስገቡ ናቸው፡፡ አጠቃላዩ የንግድ ስልታቸው የሚሸጡልንን ሸቀጥ ካልገዛን በቀር ደስተኛ እንደማንሆን ወይም እርካታ እንደማናገኝ ተደርጎ በረቂቅ የተነደፈ ነው፡፡ ማንኛውም የተሳካለት የተባለ ሸቀጥ አምራች ተቋም ሸቀጡ እንደሚያስፈልገን እንድናስብ አድርጎ በመቅረጽ ይሸጥልናል፡፡ የሸያጩ እርከን እየጨመረ መሄድ አካሄዱ እየተሳካለት የመሆኑ እውነታ ማሳያ ነው፡፡ ተስፋቸውን በዚህ ዓለም ላይ ያላደረጉት ክርስቲያኖችም ቢሆኑ ከዚህ መደለያ የተጠበቁ ሊሆኑ አይችሉም፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ--(ዘዳ. 8፡10-14) ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን አባል ከላይ ከቀረበው አደጋ መጠበቅ የሚችለው በምን መንገድ ነው?**

-----------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------

**የምድራዊው ሀብትና ንብረቱ መከማቸት መንፈሳዊ ህይወቱ እንዲያድግ፣ ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅርና ለሰማያዊው ነገር ያለው ምኞት እንዲበለጽግ የረዳውን ግለሰብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ወይም ዛሬ በዚህ ዘመን በምሳሌ ሊያቀርቡ የሚችሉት ማን ይሆን? መልስዎን በሰንበት ትምህርት ጥናት ላይ ተወያዩበት፡፡**

## ማክሰኞ ታህሳስ 24

# አማላዩ ብልጭልጭ ነገር

ዛሬ ማስታወቂያ በዓለም ላይ ብርቱ ኃይል አለው፡፡ የንግድ ድርጅቶች ምርቶቻቸውን ከእያንዳንዳችን ዐይንና ጆሮ ለማድረስ አያሌ ቢሊዮን ብሮች ይረጫሉ፡፡ ሸቀጦቻቸውን ለመሸጥ የሚጠቀሙባቸው የሽያጭ ሠራተኞች ውብና

ዐይነ ግቡ ናቸው፡፡ በዚህም ትኩረታችን ምርቱ ላይ መሆኑ ቀርቶ ማስታወቂያውን የሠሩት ላይ ይሆንና እነሱን፣ እነሱን እያየን ሸቀጡን እንገበያለን፡፡

የሸቀጥ ንግድ ሥራ ስሜትን የሚኮረኩሩ ማማለያዎችን በማስታወቂያ አማካይነት ጥቅም ላይ ባያውል፤ ገበያው እንዲህ እንደምናየው ባልደራ ነበር፡፡ ዘዴን ከብልሃት ለተካነው የማስታወቂያ ሥራ ምስጋና ይግባውና የሸቀጥ ሥራ አመርቂ ደረጃ ላይ ደርሶአል፡፡ ሆኖም ግብስብሱ ነገር ከሚያስከትለው አደጋ ለመጠበቅ ብርቱ ግብግብ ላይ ያሉትን ክርስቲያኖች ማስታወቂያ እየገዘገዘ ይገኛል፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ--ማቴ. 6፡22-24፡፡ ከክርስትና እሳቦትና ግብር አኳያ ዐይን ምን ይወክላል? እንደ ክርስቲያን የማያስፈልጉንን ሸቀጦች እንድንገዛ ለሚፈትኑን አማላይ ማስታወቂያዎች አጸፋችን ምን ሊሆን ይገባል?**

------------------------------------------------------------------------------------------------

የገበያተኛውን ስሜት ከብልጭልጩ በአንድ ያቆራኘው ማስታወቂያ እንደ ብርቱ መሣሪያ ሊቆጠር ይችላል፡፡ የጅምላም ሆነ የችርቻሮ ነጋዴዎች በገበያተኛው አእምሮ ላይ ደስ የሚል ስሜት እየፈጠሩ ብልጭልጩን በዘዴ ይቸበችባሉ፡፡ በማስታወቂያ ሥራ የሚጠቀሙት የማማለያ ዘዴ ከተጨባጩ እውነታ ያፈነገጠ ቢሆንም--ይሠራል፡፡ አላፊ ለሆነው ነገር የሰዎችን ስሜት ወደ ሌላ ዓለም ጭልጥ አድርጎ መውሰድ በእርግጥም ረቂቅ አካሄድ ነው፡፡ ማስታወቂያ ሰዎችን አነሁልሎ ይሁንታቸውን ከእጁ ካስገባ፤ አንዳች ዕውቀትም ሆነ መንፈሳዊ እውነት የማይገበይበት ሃሳዊሐሁ ስብከት ይሆናል፡፡ ይኸው ስብከት ግብስብሱ ሁሉ እንደሚያስፈልገን አድርጎ ይሞላንና--ታዲያ የማልገዛው ለምንድን ነው? ወደሚለው ውሳኔ ያደርሰናል፡፡ የማስታወቂያ ባለሚሎች አሰሱን፣ ገሰሱን አንገብጋቢ አድርገው ሰብዓዊውን አእምሮ እያሳመኑ ከየኪስ እንዲመዘዝ የሚያደርጉትን ረብጣ ብር መጠን የሚያውቀው አንድ እርሱ ብቻ ነው፡፡

**“እንግዲህ በመንፈስ ኑሩ እላለሁ፤ የሥጋንም ምኞት አትፈጽሙ” (ገላ. 5፡16)፡፡ ብዙውን ጊዜ “የሥጋን ምኞት” የሚለውን አነጋገር ከፍትዎት ጋር ብቻ ማያያዝ ቢቀናንም፤ ሃሳቡ አደጋ ያላቸው ሌሎች ምን ዓይነት ፍቺዎችን ይዞአል?**

--------------------------------------------------------------------------------------

**ረቡዕ** **ታህሳስ 25**

# ራስ ወዳድነት

“እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችሁ በሰጣችሁ እምነት መጠን ራሳችሁን በአግባቡ መዝኑ እንጂ፣ ከሆናችሁት በላይ ራሳችሁን ከፍ አድርጋችሁ እንዳታስቡ በተሰጠኝ ጸጋ እያንዳንዳችሁን እመክራለሁ” (ሮሜ 12፡3)፡፡

“በውበትህ ምክንያት፣ ልብህ ታበየ፤ ከክብርህ ታላቅነት የተነሳም ጥበብህን አረከስህ፡፡” (ሕዝ. 28፡17) በማለት እግዚአብሔር ተናግሮአል፡፡ ሉሲፈር ከሆነው በላይ ማንነቱን አግዝፎ በማሰብ ራሱን አታለለ፡፡ በልቡ “ራሴንም እንደ ልዑል አደርጋለሁ” ብሎ ሲያስብ የሌለውን መብት አለኝ የሚል ክፉ ምኞት በእርሱ እየተገለጠ ነበር፡፡ ራስን መሸንገልና ከንቱ ክብር የሚሻ ምኞት--እነዚህ ሁለቱ የወደቀው የሉሲፈር ልብ ባሕርዮች ነበሩ፡፡

በሉሲፈር ውድቀት ዙሪያ የሚያጠነጥኑት እነዚህ ጥቅሶች ያ የቀደመው ኃጢአት ራስን ማምለክ መሆኑን ከብዙ አቅጣጫዎች ሊነግሩን ይገባል፡፡ ለመሆኑ ራስን ስለ መሸንገል ከእነዚህ በላይ ግዙፍ ማሳያ ባህሪዎች የትኞቹ መሆን ይችላሉ?

እነዚህ ባህሪዎች አንድ ሰው ከሚያስበው በላይ የተለመዱና ተደጋግመው የሚስተዋሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ናቡከደነፆር ዕብሪት በተሞላ አስተሳሰብ ከተጨባጭ ማንነቱ በላይ ራሱን አግዝፎ ይመለከት ነበር (ዳን. 4፡30)፡፡ እንዲሁም ፈሪሳውያን ከዚህ ተመሳሳይ የሆነውን አሳች የቁም ቅዠት አስተምህሮ የእምነታቸው አካል

አድርገው ነበር (ሉቃ. 18፡11-12)፡፡ እኛም ተገቢውን ጥንቃቄ ካላደረግን በቀር ሀብት በራሱ ወደ ተመሳሳይ ሽንገላ ሊመራን ይችላል፡፡

**ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ጢሞቴ. 6፡10 መልእክቱ ከምን ዓይነት አደጋ መጠበቅ እንደሚኖርብን እያስጠነቀቀን ነው?**

-------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------

ጳውሎስ በ2ጢሞቴ. 3፡1-5 መልእክቱ ጢሞቴዎስ "ገንዘብን የሚወዱትን" ጨምሮ ሊጠነቀቃቸው ስለሚገባ አጉል ሰዎች ያሰፈረውን ሃሳብ እናገኛለን፡፡ አፍቅሮተ ንዋይ ሰዎችን ወደ ትምክህትና መታበይ የመምራት ኃይል አለው፡፡ የብልጭልጩ ነገር ክምችት በሰዎች ላይ አጉል የተፈላጊነት ስሜት እንዲያይል አድርጎ ይሞላቸዋል፡፡ በባንክ ሂሳቡ ውስጥ የተትረፈረፈ ገንዘብ ያለው ሰው ከሌለው ይልቅ ራሱን አግዝፎ ማየት ይቀናዋል፡፡ ለነገሩ ሁሉም ሰው ሀብታም መሆን ቢፈልግም የሚሳካላቸው ግን በጣም ጥቂቶች ናቸው፡፡ ይህን ተከትሎ መመጻደቅ፣ ኩራትና ትዕቢት ለሀብታም ቅርቡ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡

**ይህን ጥቅስ ያንብቡ--ፊልጵ. 2፡3፡፡ ከክርስትና አስተሳሰብ በተቃራኒ የሚጓዘውን ብልጭልጩን ነገር ሊያበረታታ የሚችለውን መንፈስ እንድናስተውል ጥቅሱ እንዴት ሊረዳን ይችላል?**

**ሐሙስ** **ታህሳስ 26**

## የዛገው ወርቅና ብር መጨረሻ

ማንነታቸው ቁሳዊው ነገር ሊፈነቅለው እንዳይችል ሆኖ ከእርሱ ጋር በአንድ የተዋሃደ፣ እግዚአብሔርን የሚወዱ ኢያሌ ሕዝቦች አሉ፡፡

**የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡--ዘዳ.7:6፣ 1ጴጥ. 2:9፣ ዮሐ. 15:5፣ ገላ. 2:20፡፡ የእግዚአብሔር ርስት መሆን ምን ማለት ነው? እውነተኛውን ማንነት ማግኘት የምንችለው ከወዴት ነው?**

-----------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------

"እኔ የወይን ተክል ነኝ፣ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ" (ዮሐ. 15፡5) በማለት ጌታ ይናገራል፡፡ ይህ ግንኙነት ቀጥተኛ፣ ደህንነቱም አስተማማኝና የተጠበቀ ነው፡፡ "ማንኛውም እውነተኛ መታዘዝ ከልብ ይመነጫል፡፡ መታዘዝ ከክርስቶስ ጋር በልብ ውስጥ የሚሠራ ሥራ ነው፡፡ እኛ ፈቃዳችንን የምንሰጠው ከሆነ እርሱ የአስተሳሰባችንም ሆነ ለመድረስ ያሰብነው ግብ አካል ይሆናል፡፡ ልባችንንና አእምሮአችን ከእርሱ ፈቃድ ጋር ውህደት ሲፈጥር እርሱን መታዘዝ ዱብ-ዕዳ ሳይሆን ውስጣችን የተቀመጠውን መከወን ይሆናል፡፡" —Ellen G. White, *The Desire of Ages*, p. 668.

በሌላ በኩል በብልጭልጭ ነገር ላይ ያለን ትኩረት ከሃብትና ንብረት ጋር ውሁድ ማንነት ያሰጠናል፡፡ በሌላ አነጋገር ለገዛ ማንነታችን የምንሰጠው ፍቺ ካፈራነውና የዚህን ዓለም ሸቀጥ መግዛት ከምንችለው አቅም አኳያ ነው፡፡ ሐዋርያው ያዕቆብ ከዚህ ተጠበቁ ሲል ይመክረናል "ወርቃችሁና ብራችሁ ዝጎአል፣ ዝገቱም በእናንተ ላይ ይመሰክራል፤ ሥጋችሁንም እንደ እሳት ይበላዋል፤ ለመጨረሻው ዘመን ሀብትን አከማችታችኋል፡፡" (ያዕ. 5፡3)፡፡ በጥቅሱ "አከማችታችኋል" በሚል የቀረበው ቃል--ምድራዊ ሃብት ንብረት ሰብስባችኋል የሚል ፍቺ አለው፡፡ ሰዎች ጥቂት ሃብት ያፍሩ ወይም ብዙ--አያሌዎች ማንነታቸውን የሚያገኙት በዚያ ውስጥ መሆኑ ሊስተዋል የተገባ ዋና ነጥብ ነው (ሉቃስ 12፡19-21)፡፡

ብልጭልጩን ነገር ብቻ ለማፍራት የሚደረግ ሩጫ የማንነት ቀውስ ውስጥ ይከታል፡፡ ይህ ማለት የአብዛኞቻችን ማንነት ያፈራነው ሃብትና ንብረት ውሁድ ነው፡፡ ይህን ተከትሎ ምድራዊው ሃብትና ንብረት ጣኦት ሆኖብናል (ማቴ. 6፡19-

21)፡፡ "በዚህ ምድር ካፈራሁት ሃብትና ንብረት ውጪ እኔ ምንም ነኝ" ሲል አንድ ሰው በአንድ ወቅት ተናግሮ ነበር፡፡ ራሳችንን የምንገልጸው ከምድራዊ ሀብታችን አኳያ ብቻ መሆኑ እንዴት አሳዛኝ ነው! በተለይ ራሱን ክርስቲያን ብሎ የሚጠራ የእንዲህ ያለው ገለባና ብልጭ ብሎ የሚጠፋ ከንቱ ህይወት አካል መሆኑ በእርግጥም ልብ ይሰብራል፡፡ ራሳችንን የምንገልጸው እንዴት ነው--ከሀብት ንብረታችን ወይስ የእግዚአብሔር ርስት ከመሆናችን አኳያ? ውሎ አድሮ ከአንዱ ጎን መሰለፋችን አይቀሬ ነው፡፡

**ግላዊ ማንነትዎ አሉኝ ከሚሏቸው ነገሮች ጋር ምን ያህል ተዛምዶ አለው?**

## አርብ ታህሳስ 27

**<u>ተጨማሪ ሃሳብ</u>፡** "ዛሬ ጠላት ነፍሳትን እጅግ በወደቀ ዋጋ እየገዛ ይገኛል፡፡ የእግዚአብሔር ቃል 'ያለ ዋጋ ተሸጣችሁ ነበር' ሲል ይናገራል፡፡ አንዱ ነፍሱን ለዚህ ዓለም ክብርና ዝና ሲሸጥ ሌላው ደግሞ ለገንዘብ ይሸጣል፡፡ አንዱ ጥልቅ ስሜቱን ለማርካት ሌላው ደግሞ ለምድራዊው ተድላና ጨዋታ ራሱን ይሸጣል፡፡ እነዚህ የሽያጭና የግዢ ስምምነቶች በየቀኑ ይከናወናሉ፡፡ ምንም ዓይነት ተመን ሊወጣለት በማይችለው በክርስቶስ ደም የተገዙትን ነፍሳት ሰይጣን በወደቀ ዋጋ እየሸመታቸው ይገኛል፡፡" —Ellen G. White, *Testimonies for the Church*, vol. 5, p. 133.

የሰይጣን እቅድ አሰሱን ገሰሱን ተጠቅሞ ነፍሳትን መግዛት ነው፡፡ እንደ ነገሩ ከፊታችን የተደነቀሩት እነዚህ መሰናክሎች የእያንዳንዱን ልብ በቀላሉ ያገኛሉ፡፡ ምንም እንኳ ይኸው ምድራዊ ሀብትና ንብረት የሚናገርበት አንደበት ባይኖረውም ነገር ግን ሁሉንም ቋንቋ ያውቃል፡፡ ሀብታሙንም ሆነ ደሃውን እንዴት ጮቤ ማስረገጥ እንዳለበት ስለሚረዳ "ለጊዜው የሚያሻኝ ተሟልቷል፤ ታዲያ ስለ ሌላው ነገር ምን አጨናነቀኝ?" ብለው እንዲያስቡ ያደርጋል፡፡ ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ ከመታመን በተቃራኒ ባላቸው ነገር ላይ እንዲታመኑ የሚያደርገው ቁሳዊው ነገር

አእምሮን ያበላሻል፡፡ ታዲያ ለዚህ ማርከሻ አለው፡፡ "'በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም' ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት" (ዘካ. 4፡6)፡፡

ራሳችንን ለእግዚአብሔር አሳልፈን ስንሰጥና በአምላካዊው ጸጋ ብልጭልጩ ነገር ህይወታችንን እንዳይገዛ ቁርጥ ሃሳብ ስናደርግ ቁሳዊው ነገር በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር የሚመላለስን ነፍስ መቋቋም አይችልም፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

❶ **ደሃ ወይም እጅግ የተትረፈረፈ ነገር የሌለን ብንሆን እንኳ በዚህ ሳምንት ከተመለከትናቸው አደጋዎች እንድንጠበቅ የሚያስችሉን መንገዶች የትኞቹ ናቸው?**

❷ **ምናልባት አንዳንዶች "ስለ ገንዘብ ደንታ የለኝም፤ ገንዘብ ለእኔ ምንም ማለት ነው፡፡" ብለው ሲናገሩ ይደመጣሉ (ነገር ግን ብዙ ገንዘብ ሊኖራቸው ይችላል)፡፡ እንዲህ ያለው አባባል ብዙውን ጊዜ ከእውነት የራቀ የሚሆነው ለምንድን ነው? በቂ መተዳደሪያ ገንዘብ በእጅጉ አስፈላጊ እንደ መሆኑ ገቢያችን ለምድራዊው ህይወታችን አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን ጥያቄው፡--ገንዘብንና ለገንዘብ ያለንን ብርቱ ፍላጎት ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ አኳያ ማጣጣም የምንችለው እንዴት ነው? የሚል ይሆናል፡፡**

❸ **"ብል ሊበላው፣ ዝገት ሊያበላሸው፣ ሌባም ቆፍሮ ሊሰርቀው በሚችልበት በዚህ ምድር ላይ ለራሳችሁ ሀብት አታከማቹ፡፡ ነገር ግን ብል ሊበላው፣ ዝገት ሊያበላሸው፣ ሌባም ቆፍሮ ሊሰርቀው በማይችልበት በዚያ በሰማይ ለራሳችሁ ሀብት አከማቹ፤ ሀብትህ ባለበት ልብህም በዚያው ይሆናልና" (ማቴ. 6፡19-21)፡፡ የሱስ በእነዚህ ጥቅሶች የሚለንን በጥንቃቄ ይመልከቱ፡፡ መልእክቱ ከአፍቅሮተ ቁስ አደጋ መጠበቅ እንድንችል በብርቱ ሊረዳን የሚችለው እንዴት ነው?**

# ማየት፣ መመኘት፣ ማድረግ

**ሰንበት ከሰዓት**

**ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡**-- 2ቆሮ. 8:1–7፣ ማቴ. 13:3–7፣ 22፣ ዘፍ. 3:1–6፣ ኢሳ. 56:11፣ ማቴ. 26:14–16፣ 2ጴጥ. 1:5–9፡፡

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡-**

*" 'በእሾኽ መሃከል የተዘራው ቃሉን ሰምቶ ለዚህ ዓለም በመጨነቅና በብልጽግና ሐሳብ በመታለል ታንቆ ያላፈራውን ሰው ይመስላል' " (ማቴ. 13:22)፡፡*

አፍቅሮተ ንዋይና አፍቅሮተ ቁስ በብዙ አቅጣጫዎች ሊመጡብን ይችላሉ፡፡ ኤለን ኋይት በተንኮል የተሞሉትን ማራኪ የዲያብሎስ ማዘናጊያ ዘዴዎች እንዲህ ስትል ትገልጻቸዋለች፡፡ " 'በተትረፈረፈ ሀብትና ንብረት ወደ ተሞሉት እያመራችሁ ለምድራዊው ህይወት ብቻ እንዲጨነቁ፣ እንዲጠበቡ አድርጓቸው፡፡ የምድራዊው ርስት ባለሀብት ብቻ ሆነው ይቀሩ ዘንድ ዓለምን እጅግ ውብና ማራኪ አድርጋችሁ በፊታቸው አቅርቡላቸው፡፡ ፍቅራቸውም ሆነ መውደዳቸው በምድራዊ ነገሮች ላይ ብቻ ተተክለው እንዲቀሩ አድርጉ፡፡ ከእኛ በተቃራኒ ለአምላካዊው ጉዳይ የተሰለፉ አማኞች ዓላማቸውን የሚያሳኩበት

የገንዘብ አቅም እንዳይኖራቸው በተቻለ አቅም *መሥራት* ይጠበቅብናል፡፡ ገንዘብ ሁሉ በመዋቅራችን ሥር ካልተዳደረና በአማኞች እጅ የሚገባ ከሆነ ምርኮዎቻችንን ከመዳፋችን እየፈለቀቁ በመንግሥታችን ላይ ጉዳት ያደርሳሉ፡፡ የክርስቶስን መንግሥት ስለ ማነጽና ስለ ምንጠላው እውነት መሰራጨት በመትጋት ፋንታ ስለ ንዋይ ብቻ አብልጠው እንዲጨነቁ የምናደርጋቸው እስከሆነ ድረስ ተጽእኖአቸውን መፍራት አያሻንም፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ ራስ ወዳድና አጉል ምኞት የተጸናወተው ሰው ከጉልበታችን ስር ውሎ በስተመጨረሻ ከእግዚአብሔር ሕዝብ የተነጠለ እንደሚሆን አበጥረን እናውቃለን’ ”— *Counsels on Stewardship,* pp. 154, 155.

እንዳለመታደል ሆኖ ከላይ የቀረበው ማዘናጊያ ዘዴ በሚገባ እየሠራ እንደሆነ መመልከት ይቻላል፡፡ ይህን መንፈሳዊ መሰናክል መገርሰስ እንችል ዘንድ የእግዚአብሔር ቃል የሚለንን እየተመለከትን ከፊታችን የተጋረጡትን አደጋዎች ለማጤን እንሞክር፡፡

## **እሑድ** ታህሳስ 29

# የብልጽግና ወንጌል

ታዋቂው የቴሌቪዥን ሰባኪ እንዲህ ሲሉ አንድ ቀለል ያለ መልእክት አቅርበው ነበር፡--*እግዚአብሔር ሊባርክዎ ይፈልጋል፡፡ የመባረኩ ማረጋገጫ ደግሞ በእጅዎ የሰጠዎ የተትረፈረፈ ቁስ ነው፡፡* በሌላ አነጋገር *ለእግዚአብሔር ታማኝ እስከሆኑ ድረስ እግዚአብሔር ባለሀብት ያደርጎታል፡፡*

ይህ ጽንሰ ሃሳብ ወይም የጽንሰ ሃሳቡ ልዩ ልዩ ፈርጅ *የብልጽግና ወንጌል* በመባል ይታወቃል--*እግዚአብሔርን ተከተል በዓለም ሀብትና ንብረት ይሞላሃል*--የሚል፡፡ ይህ ጽንሰ ሃሳብ የተሳሳተ የነገረ መለኮት አስተምህሮ ከማለት ውጪ ሌላ ሊባል አይችልም፡፡ *በምድራዊ ቁስ የተሞሉና ደስተኛ መሆን ይሻሉ? እንግዲያውስ ለእርስዎ “ መልካም የምስራች” አለን፡፡*

ወንጌልን ለምድራዊው ሀብት ዋስትና አድርጎ ማቅረብ የተዛባ አመለካከት ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ቋንቋ በግማሽ ከላዩ ጣል ከማድረግ በዘለለ መላወስ ያልቻለው እንዲህ ያለው እምነት፤ ከአምላካዊው ቃል ጋር መጣጣም ስለሚሳነው እኔነትን ማዕከል ያደረገ አስተምህሮ ያንጸባርቃል፡፡ በዚህ ሐሰት ውስጥ የኃጢአት ሁሉ መሰረት የሆነው እኔነትና ከማንኛውም ነገር በላይ እኔነትን የማርካት ምኞት ቁልጭ ብሎ ተቀምጦአል፡፡

የብልጽግና ወንጌል ነገረ መለኮት አስተምህሮ እንደሚለው ለእግዚአብሔር ስንሰጥ ቁሳዊውን ሀብትና ንብረት ለማፍራት ማስተማመኛ እናገኛለን፡፡ ሆኖም እንዲህ ያለው አስተምህሮ እግዚአብሔርን ሱቅ በደረቴ--ከእርሱ ጋር ያለን ግንኙነት ደግሞ ገበያ ተኮር ውል ይሆንና፤ *ይህን ሳደርግ በምላሹ ያንን እንደምታደርግ ቃል ግባልኝ*-ዓይነት ቅርጽ ይይዛል፡፡ ስለዚህ የምንሰጠው በመስጠት አግባብ ሳይሆን ምላሹን ከመጠባበቅ አኳያ ይሆናል፡፡ የብልጽግና ወንጌል ማለት ይኸው ነው፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ--2ቆሮ. 8፡1-7፡፡ የሐዋርያው መልእክት ምን ይመስላል? ከብልጽግና ወንጌል በተቃራኒ ምን ዓይነት መርኅዎች በጥቅሶቹ ሰፍረዋል? ሐዋርያው "የቸርነት *ሥራ*" (2ቆሮ. 8፡7) ሲል ምን ማለቱ ነው?**

__________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________

ምንም እንኳ እነዚህ ሕዝቦች "ድኽነታቸው ብርቱ ቢሆንም" (2ቆሮ. 8፡2) አብልጠው ለጋሶች ስለነበሩ ከአቅማቸው በላይ ይሰጡ ነበር፡፡ እነዚህን የመሳሰሉት ብዛት ያላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አንድ ሰው የሚያፈራው የተትረፈረፈ ሀብት ከእግዚአብሔር ጋር በጽድቅ ለመመላለሱ በቂ ማስረጃ መሆን ይችላል የሚለውን የብልጽግናን ወንጌል የተሳሳተ አባባል እንድናስተውል ይረዱናል፡፡

**ለእግዚአብሔር ታማኞች ሆነው ነገር ግን ይህ ነው--የማይባል ምድራዊ ሀብትና ንብረት ያልነበራቸው በምሳሌ የሚያቀርቧቸው ሰዎች ይኖራሉ? በተቃራኒው**

**በምድራዊ ሀብት በልጽገው ለእግዚአብሔር ታማኝ ያልሆኑትስ? ሀብትን እንደ አምላካዊ በረከት ማሳያ መቁጠርን አስመልክቶ ይህ ምን ሊነግረን ይገባል?**

## ሰኞ ታህሳስ 30

# የተዛባው መንፈሳዊ ዕይታ

በዚህ ምድር ያለው የሁሉም መጨረሻ ወይም መደምደሚያ አለመሆኑን ተከትሎ-- መጽሐፍ ቅዱስ በዐይን ስለሚታየው አንድ እውነት ይኸውም ስለ ጊዜያዊው ምድራዊ ህይወትና ሙላት ማሰብና መጨነቅ ብቻ እንዲነግረን አንፈልግም፡፡ "ስለዚህ ዐይናችን የሚያተኩረው በሚታየው ነገር ላይ ሳይሆን በማይታየው ላይ ነው፤ የሚታየው ጊዜያዊ ነውና፤ የማይታየው ግን ዘላለማዊ ነው" (2ቆሮ. 4፡18)፡፡ የክርስቲያን ዐይኖች በሰማያዊው መንገድ ፋንታ በአላፊው በዚህ ምድር ተተክለው፣ ለዚህ ዓለም ሲጨነቁና ሲጠበቡ ብርሃናቸው በዳፍንት የተዋጠ ይሆናል፡፡ የዐይን ብርሃን ያልነበራት ታዋቂዋ ሔለን ኬለር "የዐይን ብርሃን እያለው የማያይ፤ እርሱ በዓለም እጅግ አሳዛኙ ሰው ነው፡፡" ብላ ነበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የዐይን ብርሃን እያላቸው ነገር ግን ለመንፈሳዊው ነገር የታወሩ የአያሌዎችን ምሳሌ ይዞአል፡፡

"አንዳንዶች ለዚህ ምድር ያላቸው ብርቱ መውደድ ለእውነት ሊኖራቸው የሚገባውን ፍቅር ይውጠውና፤ የምድራዊ ሀብታቸው መጨመር ለሰማያዊው ርስት የሚኖራቸውን ፍላጎት ያመነምነዋል፡፡ ሀብታቸው እየተንሰራፋ በሄደ ቁጥር እንደ ጣዖት የሚያዩት ቁስ ከእጃቸው ይወጣ ይመስል የልብ ትርታቸው እየሆነ ይመጣል፡፡ ሀብት ንብረታቸው እየበዛና እየተትረፈረፈ ሲሄድ እነርሱ ግን ምንም እንደሌለው ደኻ አድርገው ራሳቸውን ስለሚያስቡ ንፉግና እጃቸው የማይፈታ ይሆናሉ፡፡ በምድራዊው ሀብት በመታለላቸው አምላካዊው ጉዳይ የሚያሻውን ነገር ሊያዩም ሆነ ሊሰማቸው አይችልም!" —Ellen G. White, *Spiritual Gifts,* vol. 2, p. 267.

ግልጽነት የጎደለው የተዛባ መንፈሳዊ ዕይታ ዘላለማዊውን ደኅንነት አደጋ ላይ ይጥላል፡፡ የሱስን ማየት ብቻ ሳይሆን ነገር ግን እርሱ ሁሌም በዕይታችን ውስጥ ሊሆን የግድ ነው፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ--ማቴ. 13፡3-7፣ 22፡፡ የሱስ ከምን ዓይነት ወጥመድ እንድንጠበቅ እያስጠነቀቀን ነው? ወጥመዱ ሀብታሙንም ሆነ ደኻውን በቀላሉ ምርኮኛው ማድረግ የቻለበት ምክንያቱ ምንድን ነው?**

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

የሱስ ለዚህ ዓለም እንዳንጨነቅ (ማቴ. 13፡22) ያስጠነቅቀናል፡፡ ገንዘብን ጨምሮ ብዙ ሊያስጨንቁን የሚችሉ ነገሮች እንዳሉ የሱስ ያውቃል፡፡ ደኻው በቂ ነገር የለኝም ብሎ ሲጨነቅ ሀብታሙ ደግሞ ተጨማሪ ፍሊጋ ይጨነቃል፡፡ መጨነቅና መጠበባችን ቃሉን ሰምቶ ለዚህ ዓለም በመጨነቅ ታንቆ ያላፈራው ሰው ላለመሆናችን እርግጠኞች እንሁን፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የሱስ "በብልጽግና ሀሳብ እንዳንታለል" (ማቴ. 13፡22) ያስጠነቅቀናል፡፡ ምንም እንኳ ሀብት በራሱ ክፉ ባይሆንም ነገር ግን ወደ ዘላለማዊ ጥፋት መምራት የሚችል አታላይ ኃይል አለው፡፡

**በብልጽግና ሃሳብ ሊያታልሉ የሚችሉ ምን ዓይነት ነገሮች በህይወትዎ መመልከት ይችላሉ? ራስዎን ከዚህ ማታለያ መንገድ መጠበቅ ይችሉ ዘንድ ምን ዓይነት ተጨባጭ ምርጫዎች ማድረግ ይችላሉ?**

**ማክሰኞ** ጥር 1

# የክፉ ምኞት ቅደም ተከተሎች

ክፉ ምኞት እንደ ማንኛውም ኃጢአት መጀመሪያ በልብ ውስጥ ይጠነሰሳል፡፡ በመቀጠል በውስጣችን ይጎለብትና በውጪ መታየት ይጀምራል፡፡ በኤደን የሆነው ይኸው ነበር፡፡

**ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡ ዘፍ. 3፡1-6፡፡ ሰይጣን ሔዋንን ለማጥመድ ምን ተጠቀመ? ከዚያን ጊዜ አንስቶ ሰብዓዊውን ዘር ለማታለል ተመሳሳይነት ያላቸውን መርኅዎች ጥቅም ላይ እያዋለ ያለው እንዴት ነው?**

-------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------

“ሴቲቱ የዛፉ ፍሬ ለመብል መልካም፣ ለዐይን የሚያስደስትና ጥበብንም ለማግኘት የሚያጓጓ እንደ ሆነ ባየች ጊዜ፣ ከፍሬው ወስዳ በላች፤ ከእርሷም ጋር ለነበረው ለባሏ ሰጠችው፤ እርሱም በላ፡፡” (ዘፍ. 3፡6)፡፡

አንድ ሰው ነገሮችን በጥልቅ መመልት ከቻለ፤ የማስታወቂያው ኢንደስትሪ ብልጭልጩን አጓጊ አድርጎ እያቀረበ የኤደንን ታሪክ በምሳሌነት እየደገመ እንደሆነ ሊያስብ ይችላል፡፡ ሔዋን የማያስፈልጋትን ነገር ያስፈልገኛል ብላ እንድታስብ ያደረገው ዲያብሎስ፤ ቀድሞውኑ በእጇ ካለው ሁሉ በላቀ እንድትመኘውና ጉጉት እንዲያድርባት አድርጎ ያን የተከለከለ ዛፍ ፍሬ አቀረበላት፡፡ እንዴት ያለ ብልህ ዘዴ ነው! የእርሷ ውድቀት እያንዳንዳችን በክፉ ምኞት ስንወድቅ የሚከሰቱት ሦስት ቅደም ተከተሎች ማሳያ ነው-- *ማየት፣ መመኘት፣ ማድረግ*፡፡

እንደ ምንዝር ሁሉ ከሥጋችን መጋረጃ ጀርባ ተሸሽጎ የሚገኘው ክፉ ምኞት ኃጢአት የመሆኑ ነገር እርግጥ ነው፡፡ ውሎ አድሮ ፍሬ እንዲያፈራ ከፈቀድንለት

ውጤቱ አውዳሚ ሊሆን ይችላል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ግንኙነት በመጉዳት በምንወዳቸው ወገኖች ላይ ጠባሳ ሊተውና ነጋ ጠባ በጸጸት ሊጠብሰን ይችላል፡፡

ክፉ ምኞት በመላው ማንነታችን እንዲንሰራፋ ስንፈቅድ ማንኛውንም የህይወት መርኅ ገለባብጦ ዐናት ላይ ፊጥ ይላል፡፡ ንጉሥ አክዓብ የናቡቴን የወይን ተክል ቦታ ተመለከተ፣ ተመኘው፣ ንግሥቲቷ ሚስቱ እስክታስገድለው ድረስ እንደተበሳጨና እንደተቆጣ ሰነበተ (1ነገሥ. 21)፡፡ አካን የሚያምረውን ካባና ገንዘብ በተመለከተ ጊዜ እጅግ ከመጎምጀቱ የተነሳ ወሰደው (ኢያሱ 7፡20-22)፡፡ ክፉ ምኞት ውሎ አድሮ ለየት ያለ ራስ ወዳድ ቅርጽ የመያዝ ባህሪ አለው፡፡

"ራስ ወዳድነት በመላው ማንነት የሚሰራጨውን ኃጢአት ቅርጽ የሚይዝ ከሆነ፤ ክፉ ምኞት ደግሞ በመላው ማንነት የሚሰራጨውን ራስ ወዳድ ቅርጽ እንደሚይዝ ሆኖ መታየት ይችላል፡፡ ይህን አስመልክቶ ሐዋርያው ጳውሎስ "የሚያስጨንቅ ጊዜ" (2ጢሞቴ. 3፡1) በማለት በመጨረሻዎቹ ዘመኖች ላይ ገቢራዊ ስለሚሆነው ክህደት ሲገልጽ በዚያን ወቅት አብልጦ እያየለ የሚሄደውን ራስ ወዳድነት የሁሉም ክፉ ፍሬዎች ስር አድርጎ ያቀርብና፤ ክፉው ምኞት ግን የዚህ ኃጢአት ቀዳሚ ፍሬ ነው በማለት በሁለቱ መሃል ያለውን አስደናቂ ትስስር ያሳየናል፡፡ 'ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ፣ ገንዘብን የሚወዱ ይሆናሉ' *[2 ጢሞቴ. 3:2]*"—John Harris, *Mammon*,(New York: Lane & Scott, 1849) p. 52.

**ማንኛውም የዓለማዊ ክፉ ምኞት አዝማሚያ በእኛ ውስጥ መኖሩን መገንዘባችን አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?**

## ረቡዕ ጥር 2

# ስስት--ነገሮችን እንደ ሥጋ ፈቃድ መምራት

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ኢሳ. 56፡11፡፡ ስለ ምን ዓይነት ኃጢአት የተሰጠ ማስጠንቀቂያ ነው?**

__________________________________________________________________________

በኃጢአት መውደቃችንን ተከትሎ ሁሌም ጠገብኩን የማናውቅ፣ የግል ጥቅማችንን ብቻ አሳዳጅ ፍጡራን ሆነናል፡፡ ስለዚህ ጸባያችን ከስስት ውጪ የክርስቶስን ባህሪ ያንጸባርቃል ብሎ ለመገመት አዳጋች ነው፡፡ “የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ጸጋ ታውቃላችሁና፤ በእርሱ ድኽነት እናንተ ባለጠጎች ትሆኑ ዘንድ እርሱ ሀብታም ሆኖ ሳለ ለእናንተ ሲል ድኻ ሆነ” (2ቆሮ. 8፡9)፡፡

በምድር ታሪክ ስስት በዓለማችን ላይ ያስከተለውን ጉዳት የሚያውቀው አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ስስት አያሌዎችን ለጦርነት አሰልፏል፡፡ ስስት ብዙዎችን ወደ ወንጀል በመምራት በራሳቸውም ሆነ በቤተሰቦቻቸው ላይ ሰቆቃና ውድመት አስከትሎአል፡፡ ስስት ማንኛውንም የአስተናጋጁን መልካም ስብዕና በዝብዞ ግለሰቡ አብልጦ ስስታም እስኪሆን እንደማይለይ ቫይረስ ነው ሊባል ይችላል፡፡ ስስት ማንኛውንም ምኞት፣ ሥልጣንም ሆነ ንብረት አጥብቆ የሚሻ ደዌ ነው፡፡ አሁንም በድጋሚ--ያያል፣ ይመኛል ያደርጋል፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡--ማቴ. 26፡14-16፡፡ ከዚህ አሳዛኝ ታሪክ ስለ ስስት ብርቱ ኃይል ምን መማር እንችላለን?**

__________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________

ይሁዳ “‘እርሱን አሳልፌ ብሰጣችሁ እናንተስ ምን ትሰጡኛላችሁ?’ ” (ማቴ. 26፡15) በማለት የተናገረውን ልብ ይሏል፡፡ ስስት ማንነታችንን እንዲቆጣጠር ስንፈቅድ ምን ሊከተል እንደሚችል ተነጋገሩ፡፡ በምድር ታሪክ በጣም ዕድለኞች ከሚባሉ ጥቂቶች አንዱ የነበረው ይሁዳ ሥጋ ለብሶ ወደዚህ ምድር ከመጣው የሱስ ጋር አብሮ ኖሮአል፣ ለሠራቸው ተአምራቶች ምስክር ሆኖአል፣ የህይወትን ቃላት ሲሰብክም ሰምቶአል፡፡ ይህ ሁሉ ሆኖ ስስትና አጉል ምኞት ወዴት እንደመሩት ይመልከቱ፡፡

“አዳኛችን ውሎ አድሮ ክህደት የሚፈጽምበትን ሰው እንዴት አድርጎ ተንከባከበው! የሱስ ስለ ቸርነትና መርኅ ሲያስተምር ስግብግብነትን ክፉኛ አወገዘ፡፡ የሱስ ለይሁዳ

የአልጠግብ ባይነትን አስከፊነት አሳየው፡፡ ይሁዳም ይህ ጸባዩ በተደጋጋሚ ተገልጦ መታየቱንና ኃጢአቱም በግልጽ መስተዋሉን ቢገነዘብም፤ ለመናዘዝና ኃጢአቱን ለመተው ግን አልፈለገም ነበር፡፡" —Ellen G. White, *The Desire of Ages*, p. 295.

**አጥብቆ ካልተጠነቀቀ በቀር በህይወቱ ወይም በጸባዩ ንፉግነት ሊታይበት የማይችል ሰው ማን ነው? ይህን ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ በእግዚአብሔር ጸጋ በቁጥጥራችን ስር ማዋል የምንችለው እንዴት ነው?**

**ሐሙስ** **ጥር 3**

## ራስን መግዛት

የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡፡ ሰዎች ባለሀብት ቢሆኑ ወይም ቢደኸዩ ስስት፣ አጉል ምኞት፣ አፍቅሮተ ንዋይና አፍቅሮተ ቁስ--በክርስቲያን ላይ ከሚያደርሱት ጉዳት እንዴት መጠበቅ እንደሚችሉ እናስተውል ዘንድ ጥቅሶቹ ምን ይላሉ?

*ሐዋ. 24:24–26*______________________________________________

*ገላ. 5:22–25*________________________________________________

*2ጴጥ. 1:5–9*________________________________________________

እነዚህ ጥቅሶች እንዴት መኖር እንዳለብን አስመልክቶ በምክረ ሃሳብ የበለጸጉና በመለኮታዊ ትእዛዝ የተሞሉ ናቸው፡፡ ከመሀከላቸው የተለመደውን አላባ ይኸውም ራስን መግዛት ልብ ይበሉ፡፡ ጉዳዩን በተለይ ከስስት፣ ከአጉል ምኞትና ከአፍቅሮተ ቁስ ባህሪ አኳያ ከተመለከትነው አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ በመጀመሪያ ሀሳባችንን፤ በቀጣይ ድርጊታችንን በመቆጣጠር ራሳችንን መግዛት ከቻልን ብቻ እየተነጋገርንባቸው ያሉት ነገሮች ከሚያስከትሉት አደጋ መጠበቅ እንችላለን፡፡

ራሳችንን ለጌታ ኃይል ለማስገዛት ባቀረብነው መጠን ብቻ እንዲህ ያለውን ራስ መግዛት መለማመድ እንችላለን፡፡ በተለይ እነዚህን ኃጢአተኛ ባህሪያት ረዘም ላሉ ጊዜያት ከተለማመድንና አብረውን ከኖሩ፤ ማናችንም በራሳችን ልናሸንፋቸው አንችልም፡፡ በእነዚህ ብርቱ ማታለያዎች ላይ ባለድል መሆን የምንሻ እስከ ሆነ ድርስ የመለኮታዊው መንፈስ ቅዱስ በህይወታችን መሥራት በእርግጠኝነት ያስፈልገናል፡፡ "በሰዎች ሁሉ ላይ ከደረሰው የተለየ ፈተና አልደረሰባችሁም፤ እግዚአብሔር ታማኝ ነው፤ ስለዚህ ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ አይተዋችሁም፤ ነገር ግን በምትፈተኑበት ጊዜ ፈተናውን መታገሥ እንድትችሉ፣ መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኋል" (1ቆሮ. 10፡13)፡፡

**ጥቅሶቹን በድጋሚ ያንብቡ፡--(2ጴጥ. 1፡5-9)፡፡ ጴጥሮስ እንድንራመድበት የሚያመላክተን መንገድ ምን ይመስላል? የአካሄዱ ቅደም ተከተሎችስ ምንድን ናቸው? በተለይ ከስስትና ከክፉ ምኞት ጋር ከምናደርገው ግብግብ አኳያ እንዴት መጓዝ እንዳለብን መማር የምንችለውስ በምን መልኩ ነው?**

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

## አርብ ጥር 4

**<u>ተጨማሪ ሀሳብ</u>፡-** ደስተኛ መሆንና እርካታ ማግኘት የሰብዓዊው ዘር የመጨረሻ ግቦች ቢሆኑም፤ ነገር ግን የሕንፃ፣ የመሬትና እንደ ውሃ የሚፈሰው መኪና ባለቤት መሆን የዚህ ግብ ባለቤት አያደርግም፡፡ ምንም እንኳ ሰዎች ይህ እውነት መሆኑን ውስጣቸው ቢያውቅም በሀብት መመሰጡን ግን እንደቀጠሉበት ነው፡፡ ከማየት፣ ከመመኘትና የተመኙትን የራስ ከማድረግ በላይ ምን የቀለለ ነገር አለ? ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች እንደ ማንኛውም ሰው በአፍቅሮተ ቁስ እሴቶች ይፈተናሉ፡፡ ይህም ሆኖ ባለማቋረጥ የሚሰበሰበው ቁስ ደስታ ወይም እርካታ አያስገኝም፡፡ በዚያ ፋንታ ችግሮች ይዞ ከተፍ ይላል፡፡ ብዙ ሀብት በነበረው በዚያ ጎልማሳ ሰው እንደታየው መስማት የተመኘውን ባለመስማቱ ወይም ልቡ የሻተውን

ባለማግኘቱ እያዘነ ከየሱስ ፊት ሄደ፡፡ “ቁሳዊ እሴቶች… ዝቅ ካለው የሕይወት እርካታና ደስታ እስከ ጭንቀትና ስጋት፤ ብሎም ከአካላዊ ችግሮች እንደ ራስ ምታት፣ የማንነት ቀውስ፣ ራስን ማምለክና ጸረ-ማኅበረሰባዊነት ድረስ የሰዎችን የደህንነት ስሜት ከማመንመን ጋር የተቆራኘ ዝምድና አላቸው፡፡” —Tim Kasser, *The High Price of Materialism* (Cambridge, Mass.: The MIT Press, 2002), p. 22.

አፍቃሪ ቁስ ክርስቲያኖች ከሀብት ዋንጫ በኩራት ቢጎነጩም መንፈሳዊ ህይወታቸው ግን በጥም የተቃጠለ ነው፡፡ ክርስቶስ ከሚሰጠው ውሃ የሚጠጣ ግን ፈጽሞ አይጠማም (ዮሐ. 4፡14)፡፡

## የመወያያ ጥያቄዎች፡

❶ **በብልጽግና ወንጌል ጽንሰ ሃሳብ ዙሪያ በቂ ቆይታ ያድርጉ፡፡ በዚህ ጽንሰ ሃሳብ የሚያምኑ አስተሳሰቡን ለማራመድ የሚጠቀሟቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የትኞቹ ናቸው? ይህ በእንዲህ እንዳለ አስተምህሮው ስህተት መሆኑን በምሳሌ የሚያስረዱ ታማኝ ሰዎችን ህይወት ከመጽሐፍ ቅዱስ ማግኘት ይችላሉ?**

❷ **አንድ አባት የመጀመሪያ ልጁ ጥቂት ዓመታት እንደሞላው እንዲህ ሲል ተናግሮ ነበር “ከልጄ ሁለት ጠቃሚ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነቶችን የተማርኩ ሲሆን-- እነርሱም የመጀመሪያው ኃጢአተኞች ሆነን መወለዳችንን፤ በቀጣይ ደግሞ ራስ ወዳድ ሆነን ከእናታችን ማህጸን መውጣታችን—ናቸው፡፡” ተፈጥሮአዊው ራስ ወዳድነታችንና ስግብግብነታችን በህፃናት ሳይቀር ከመንጸባረቁ ጋር በተያያዘ አንዳንድ ታሪኮችን በምሳሌ ማቀረብ የሚችል ይኖራል?**

❸ **“ችግሮቻችንን ከስረ መሰረቱ ለመመርመር የምንሻ ከሆነ” በማለት አንድ ሰው ጽሑፉን ሲቀጥል “ሰዎችን ልንመረምር የሚገባው አደንዛዥ እፅ በመውሰዳቸው ሳይሆን ነገር ግን ጅልነታቸውን፣ አለማወቃቸውን፣ ስስታምነታቸውንና የሥልጣን ጥመኝነታቸውን መሆን ይኖርበታል፡፡” ብሏል፡፡ በራሱ በስስታሙ ሰው ላይ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን በዙሪያው ያሉ ወገኖች ላይ አስከፊ ጉዳት አድራሹ ስስት ምንድን ነው? ስስት ስላስከተለው አሳዛኝ ውድመት የሚያውቁትን ታሪክ በምሳሌ ያካፍሉ?**

# ፩ኛ ትምህርት

ከጥር 5 - 11

# እግዚአብሔርን ወይስ ቁሳዊውን ሀብት?

**ሰንበት ከሰዓት**

**ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡**--*መዝ.* 33:6–9፣ *ማቴ.* 19:16–22፣ 1ጴጥ. 1:18፣ *ዕብ.* 2:14-15፣ *ዘፀ.* 9:14፣ *መዝ.* 50:10፡፡

የሳምንቱ ጥናት ወርቃማ ጥቅስ:-

"ስለዚህ እግዚአብሔር እጅግ ከፍ አደረገው፤ ከስምም ሁሉ በላይ የሆነውን ስም ሰጠው፤ ይኸውም በሰማይና በምድር፣ ከምድርም በታች ጉልበት ሁሉ ለኢየሱስ ስም ይንበረከክ ዘንድ፣ ምላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው፡፡" *(ፊልጵ. 2፡9-11)*

እግዚአብሔር ስለ ገንዘብና ቁሳዊው ነገር ከልክ ባለፈ ስለ ማሰላሰል ሃሳቡን ለመግለጽ ቃሉን አያባክንም፡፡ ምንም እንኳ በሉቃስ ወንጌል የተጠቀሰው ሀብታሙ ሰው በጌታ የተባረከና አብልጦ ያከማቸ ቢሆንም ነገር ግን ክርስቶስ ስለዚህ ንፉግ ሀብታም ሰው የተናገራቸው ቃላት እግዚአብሔርን መፍራት እንዳለብን ያሳዩናል፡፡ " 'አንተ ሞኝ፤ ነፍስህን በዚህች ሌሊት ከአንተ ሊወስዱ ይፈልጓታል፤ እንግዲህ፣ ለራስህ ያከማቸኸው ለማን ይሆናል?' አለው፡፡ ስለዚህ ለራሱ ሀብት የሚያከማች፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ሀብታም ያልሆነ ሰው መጨረሻው ይኸው ነው፡፡"

ዱባና ቅል አበቃቀሉ ለየቅል--እንዲሉ እግዚአብሔርን ማገልገልና ገንዘብን ማገልገል በጋራ የሚያገናኛቸው አንዳች ነገር የለም፡፡ መንታ ህይወት ለመኖር መሞከር ውሎ አድሮ መዘዝ እንደማያጣው ሁሉ፤ እነዚህን ሁለቱን በጋራ አስኬዳለሁ ብሎ ማሰብ ከቁም ቅዠት የዘለለ አይሆንም፡፡ ምናልባት ሌሎችን ብሎም ራሳችንን ጭምር እናታልል ይሆናል፤ ነገር ግን አንድ ቀን ለዚህ ሁሉ ምላሽ ለመስጠት በፊቱ የምንቀርበውን እግዚአብሔርን ማሞኘት አንችልም፡፡

ምርጫ ልናደርግ የግድ ነው፡፡ በሁለት ልብ እያመነታን ምክንያቶችን እየደረደርን ከዛሬ ነገ እያልን ብራችንን አንቀን የምንይዝ ከሆነ፤ ፍቅረ ንዋይ በነፍሳችን ይጠቀምብናል፡፡ ውሳኔ ላይ ለመድረስ እምነት ሊኖረን የግድ ነው፡፡

ትኩረታችንን አብልጠን በእግዚአብሔር ማንነት ላይ በማኖር እርሱ ለእኛ ያደረገልንንና የበጎነቱ ባለዕዳ መሆናችንን ማሰባችን ውሳኔያችንን በእጅጉ ሊያቀልልን ይችላል፡፡

## እሁድ ጥር 6

# ክርስቶስ--የሰማይና ምድር ፈጣሪ

**የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ዘፍ. 1:1፣ መዝ. 33:6–9፣ ኢሳ. 45:11-12፣ ኤር. 51:15፣ ዮሐ. 1:3፡፡ ጥቅሶቹ ስለ ቁሳዊው ዓለም መልካምነት ምን ይነግሩናል?**

____________________________________________________________

____________________________________________________________

"ሰማያትን የዘረጋውና የምድርንም መሰረት የጣለው ክርስቶስ ነበር፡፡ ዓለማትን በጠፈር ላይ ያንጠለጠለውና የሜዳ አበቦችንም የቀረጸ የእርሱ እጅ ነበር፡፡ 'ተራሮችን በብርታትህ መሠረትህ' 'ባሕር የእርሱ ናት፤ እጁም አበጀ' (መዝ. 65፡6፣ 95፡5)፡፡ ምድርን በውበት ያስጌጣትና አየሩንም በዜማ የሞላው እርሱ ነበር፡፡ በምድር፣ በአየርና በሰማይ ላይ ባሉ ነገሮች ሁሉ የአብን የፍቅር መልእክት ጻፈ፡፡" *የዘመናት ምኞት ገጽ 10 (አማርኛው ትርጉም)፡፡*

ቁሳዊ ነገሮች በራሳቸው ክፉ አይደሉም፡፡ አንዳንድ የኃይማኖት ተቋሞች መንፈሳዊው ነገር ብቻ መልካም እንደሆነ በማስተማር፤ ቁሳዊው አካልም ሆነ ዓለም በራሱ መጥፎ ወይም ክፉ ነው ሲሉ ቢደመጡም፤ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ለቁሳዊው ዓለም ዋጋ ይሰጣል፡፡

ለነገሩ ቁሳዊውን ዓለም ማን ፈጠረው? የሱስ ራሱ አይደለምን? ታዲያ እንዴት አድርጎ ነው ክፉ የሚሆነው? በሚያሳዝን ሁኔታ ሁሉም የእግዚአብሔር ስጦታዎች የታለመላቸውን ጤነኛ ባህሪ ለውጠው የክፉው መጠቀሚያ መሣሪያ ቢሆኑም ነገር ግን ኋለኛው ክስተት የቀደመውን ስጦታ ክፉ አያሰኘውም፡፡ እግዚአብሔር በዚህ ዓለም የፈጠራቸው ነገሮች ላይ ጉዳት እንዳናደርስ ወይም ከጤነኛ ተፈጥሮአቸው እንዳናወጣቸው መጽሐፍ ቅዱስ ያስጠነቅቀናል፡፡

እግዚአብሔር ቁሳዊውን ዓለም በመፍጠር ሕዝቦቹ ምድር በምታፈራው ፍሬ ደስ እንዲሰኙና ይህች ዓለም ባሏት ነገሮች ሁሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ፈለገ፡፡ “ከዚያም አንተ፣ ሌዋዊውና በመካከልህ የሚኖረው መጻተኛ፣ አምላክህ እግዚአብሔር ለአንተና ለቤትህ በሰጠው በጎ ነገር ሁሉ ደስ ይበላችሁ” (ዘዳ. 26፡11፣ ዘዳ. 14፡26)፡፡

የሱስ የዚህ ዓለም ፈጣሪ ሲሆን (ዮሐ. 1፡1-3) ምድር ደግሞ የአምላካዊው ንድፍ ጥሩ ማሳያ ምሳሌ ናት፡፡ የእርሱ የመፍጠር ችሎታ በራሱ በሕይወትም ሆነ በምድር ነዋሪዎች ላይ የተለየ አመለካከት እንዲኖረው ያደርገዋል፡፡ ቁሳዊ ነገሮች ስላላቸው ዋጋ ጠንቅቆ የሚያውቀው ይህ ጌታ ስለ እኛ ጥቅም--ብሎም ደስታና ፍስሐ ሲል አበረከተልን፡፡ ደግሞም ሰብዓዊው ዘር አብልጦ ለእግዚአብሔር ክብር እንዲሰጥ ታልመው ጥቅም ላይ የዋሉትን አምላካዊ ትሩፋቶች ከተፈጥሮአቸው ውጪ ሲጠቀምባቸው ወይም ዳግም እንዳያንሰራሩ አድርጎ ሲያወድማቸው እርሱ ያውቃል፡፡

**ይህች በእግዚአብሔር የተፈጠረች ዓለም የያዘችውን የተትረፈረፈ ቸርነት ይመልከቱ፡፡ ኃጢአት ካደረሰባት መጠነ ሰፊ ውድመት በኋላም እንኳ የተትረፈረፈውን መልካም ተፈጥሮ ማየት ይቻላል፡፡ የእግዚአብሔር ፍጥረት ሥራ የሆነው ይህ ዓለም በውስጡ የያዘው መልካምነት ስለ አበጃጀው ጌታ በጎነት ምን ይነግረናል?**

**ሰኞ** **ጥር 7**

# የእግዚአብሔር ልጅ / የሰው ልጅ

እንደ ክርስቲያንነታችን የሱስ ፍጹም ሰው፣ ፍጹም አምላክ መሆኑን እናምናለን፡፡ ይህ የመለኮትና የሰብዓዊ ፍጹም ውህደት አሁንም ሆነ ለዘላለም ለዚህች ምድር በእጅጉ የሚያስፈልጋትን ጠንቅቆ የሚያውቅና ለእርሷ ያለው ሃሳብ የተለየ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ እርሱ ፍጹም መለኮት፣ ፍጹም ሰው ተፈጥሮ እንዴት ሊኖረው እንደቻለ ማስተዋል አለመቻላችን እውነታውን ዋጋ ሊያሳጣው አይችልም፡፡

“የአንዱ አምላክ በሶስት ባህሪ መገለጥና የየሱስ ፍጹም መለኮትና ፍጹም ሰው ባህሪ የመውሰድ ምስጢር… እነዚህ ሁለቱ ከሰብዓዊው ልብም ሆነ እሳቤ የመጠቁ እጹብ ድንቅ ክስተቶች ናቸው፡፡” —J. I. Packer, *Knowing God* (Downers Grove, Illinois: InterVarsity Press, 1973), p. 53.

የሱስ ወደዚህ ምድር ከመጣባቸው ምክንያቶች አንዱ እግዚአብሔር ምን ያህል እያንዳንዳችንን የሚወድና የሚጠነቀቅልን አምላክ መሆኑን ለማሳየት ነበር፡፡ አንዳንዶች እንደሚያምኑት እግዚአብሔር እጅግ ርቆ የሚኖር ቀዝቃዛ አምላክ አይደለም፡፡ ስለዚህ የሱስ የሰማያዊ አባታችንን እውነተኛ ጸባይ ገለጠልን፡፡

ይህም ሆኖ ሰይጣን ሰብዓዊውን ፍጡር ከእግዚአብሔር ለመለየት ሞክሯል፡፡ የአምላካዊውን ትክክለኛ ባህሪ አዛብቶ በማቅረብ ስለ እኛ ግድ የማይለው አምላክ አድርጎ ለመሳል ጥረት አድርጎአል፡፡ ተጨባጩን የእግዚአብሔር መልካምነትና ጸጋ ከማወቅና ከመለማመድ እንድንገታ ለማድረግ የሚችለውን ሁሉ ተጠቅሞአል፡፡ ሰይጣን አፈንጋጩን አፍቅሮተ ቁስ በማዘናጊያነት ጥቅም ላይ ማዋሉ ዕቅዱን በጥሩ ሁኔታ ለማሳካት አስችሎታል፡፡

**ይህን ጥቅስ ያንብቡ--ማቴ. 19፡16-22፡፡ ሰይጣን እኛን ከጌታ ለማራቅ ለብልጭልጩ ግዑዝ ያለንን ፍቅር እንዴት መጠቀም እንደሚችል ታሪኩ ምን ይነግረናል?**

______________________________________________________________

ይህን ጎልማሳ ሀብታም ያናግር የነበረው ሰብዓዊውን ሥጋ የለበሰው ራሱ እግዚአብሔር እንደ ነበር ልብ ይሏል፡፡ የሱስ ከማንኛውም ሰው ወጣ ያለ ስብዕና የተላበሰ ሰው እንደነበር ጎልማሳው በእርግጠኝነት አውቆአል፡፡ ታዲያ በመቀጠል የተከሰተው ምን ነበር? ጎልማሳው በፊቱ ከቆመው ከራሱ ከእግዚአብሔር አምላክ ይልቅ ባፈራው መጠነ ሰፊ ሀብት ላይ ብርቱ ፍቅር እንዲኖረው ፈቀደ፡፡ ለዚህ ዓለምና ለአላፊው ነገር የነበረው ብርቱ ፍቅር ልቡን በማሳወሩ ቢያዝንም-- አዘኔታው ጥልቅ ባለመሆኑ ትክክለኛውን ነገር እንዲያደርግ አላስቻለውም፡፡ ጎልማሳው ዘላለማዊውን ህይወት በሚያልፈው በዚህ ዓለም ፍቅር በመለወጡ አዘነ እንጂ ምድራዊን ሀብት አጣለሁ ብሎ አልተከፋም ነበር፡፡

***ሀብታም ሆንን ወይም ደኻ ከዚህ ዓለም ነገሮች ጋር ያለን ግንኙነት አግባብ ያለው ለመሆኑ እርግጠኞች መሆን የምንችለው እንዴት ነው?***

## ማክሰኞ ጥር 8

# ክርስቶስ የዓለም ቤዛ

ብድር ወይም ዕዳ ሰማያዊ መርኅ አይደለም፡፡ ሆኖም አዳምና ሔዋን ኃጢአት በመሥራታቸው የተጣሰው ሕግ ሞት አስከተለ፡፡ በዚህም ሰብዓዊው ዘር የመለኮታዊው ፍትሕ ባለ ዕዳ ሆነ፡፡ እኛ ሁላችን ፍጹም ዕዳችንን መክፈል የማንችልና በመንፈሳዊ ኪሳራ ብቻ የምንቀሳቀስ ሆንን፡፡

እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር የደኅንነትን ዕቅድ ሐሳብ ማቅረቡን ተከትሎ የሱስ ለእኛ "ዋስ" ሆነ (ዕብ. 7፡22)፡፡ እስከ ዛሬ ከታሠሩት ውሎች ሁሉ እጅግ ብርቱው በክርስቶስ አዳኝ ማንነት የተገለጠው ነው፡፡ በመለኮት የተጠየቀውን የፍትሕ ዕዳ መክፈል የሚችለው በመሥዋዕትነት የቀረበው የእርሱ ህይወት ብቻ ሆነ፡፡ በዚህም የሱስ የኃጢአትን ዕዳ በመስቀል ላይ በመክፈል የፍትሕ እና የምህረት ባለ ውለታችን ሆነ፡፡ ለሰብዓዊው ፍጡር ዕዳ በቤዛነት የተከፈለው ይህ ግዙፍ የክፍያ መጠን በዩኒቨርስ ታሪክ ታይቶም ሆነ ተሰምቶ አይታወቅም (ኤፌ. 5፡2)፡፡

"እግዚአብሔር አምላክ ሰማያዊውን መዝገብ አንጠፍጥፎ ያለውን ሁሉ ይኸውም ክርስቶስን በመስጠትና በክርስቶስ የሰማይ ባለቤት በማድረግ የእያንዳንዱን ሰብዓዊ

ፍጡር ይሁንታ፣ ፍቅር፣ ልብና ነፍስ ገዛ፡፡" —Ellen G. White, *Christ's Object Lessons*, p. 326.

**በመቀጠል የቀረቡትን ጥቅሶች በጥንቃቄ ካነበቡ በኋላ ክርስቶስ ከምን ከምን እንዳዳነን ዘርዝረው ለማስቀመጥ ይሞክሩ፡፡ ቆሊ. 1:13፣ 1ተሰ. 1:10፣ 1ጴጥ. 1:18፣ ዕብ. 2:14-15፣ ገላ. 3:13፣ ራእ. 1:5፡፡**

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

በዮሐ. 19፡30 *ቴትለስታይ* በሚል ጥቅም ላይ የዋለው የግሪክ ቃል ከማንኛውም ቃል ይልቅ እጅግ ጠቃሚና ብርቱ ነው፡፡ ቃሉ "*ተፈጸመ*" የሚል ፍቺ ያለው ሲሆን፤ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የተናገረው የመጨረሻ ቃል ነው፡፡ የክርስቶስ የመጨረሻው እስትንፋስ እወጃ ወደ ምድር የመጣበት ተልዕኮ ከንዋኔ ማግኘቱንና ዕዳችን ሙሉ ለሙሉ መከፈሉን የሚያበስር ነበር፡፡ ቃሉ ከአንደበቱ የወጣው እንደው በተስፋ ቢስ ስሜት ሳይሆን--ጠፍቶ ለነበረው ዓለም ቤዛነቱን በሚያውጅ ድምፀት ነበር፡፡ የክርስቶስ ከሁለት ሺ ዓመታት በፊት በመስቀል ላይ ለዓለም ቤዛ መሆን ትናንትን ጨምሮ ለዛሬ እንዲሁም ለነገ ብሩህ ተስፋ ፈንጥቆአል፡፡ የሱስ ኃጢአትን፣ ሞትንና የዲያብሎስን ሥራ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከሥረ መሰረቱ ለመገርሰስ ህይወቱን መሥዋዕት አድርጎ ሰጠ፡፡ ምንም እንኳ ይህ ሁሉ በጎነት የማይገባን ቢሆንም ነገር ግን እንደ ባለጸግነቱ መጠን እነሆ በእርሱ ቤዛነት ተዋጀን (ኤፌ. 1፡7)፡፡ አስደናቂውን የደኅንነት ታሪክ በጨረፍታ መመልከት--አረማመዳችንን የተቀደሰ ማድረግ ነው፡፡

የክርስቶስ ቤዛነት ልብ የሚማርከው የእግዚአብሔር ገጽታ ነው፡፡ እኛን መዋጀት የእርሱ ተቀዳሚ ፍላጎት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለሰብዓዊው ዘር ያለውን ሀሳብ፤ በተለይም ከእኛ ጋር ላለው ግንኙነት ምን ያህል ዋጋ እንደሚሰጥ ያሳያል፡፡ ክርስቶስ ዕዳችንን ከፍሎ ሕጉ የሚጠይቀውን ፍትሕ ካሰፈነ በኋላ ትኩረቱን ምላሻችን ላይ አድርጓል፡፡

**እርስዎ ላደረጉት ክፉ ነገር ይጠብቅዎ የነበረውን ቅጣት--እርሱ አንድም ሳይቀር ሙሉ ለሙሉ ከፍሎልዎታል፡፡ ታዲያ ለዚህ በጎነት ምላሽዎ ምንድን ነው? (ኢዮብ. 42:5-6)፡፡**

**ረቡዕ** ጥር 9

# ቀናተኛው አምላክ

እግዚአብሔር ከፈርዖን ጋር ባደረገው ግጥሚያ እንዲህ ሲል ተናገረ "አለዚያ በአንተ፣ በሹማምቶችህና በሕዝብህ ላይ የመቅሰፍቴን መዓት ሁሉ አሁን አወርድብሃለሁ፤ ይኸውም በምድር ሁሉ እንደ እኔ ያለ ማንም እንደሌለ ታውቅ ዘንድ ነው፡፡" (ዘፀ. 9፡14)፡፡

**ጌታ "በምድር ሁሉ እንደ እኔ ያለ ማንም እንደሌለ" ሲል ምን ማለቱ ነው?**

____________________________________________________________

____________________________________________________________

"ውሱን በሆነው ሰብዓዊ አእምሮ የማይወሰነውን አምላክ ጸባይ ወይም ሥራ ማስተዋል የማይሆን ነገር ነው፡፡ ንቁ፣ ስል እና ላቅ ያለ አስተሳሰብ ባላቸው የተማሩ ሰዎች አእምሮ--ቅዱሱ አምላክ ምስጢር እንደሆነ ሊኖር የግድ ነው፡፡" —Ellen G. White, *Testimonies for the Church*, vol. 5, pp. 698, 699.

እግዚአብሔር እርሱን የሚመስል አቻ የለውም (1ነገሥ. 8፡60)፡፡ እርሱ እኛ ልናስተውል በማንችለው መልኩ ያስባል፣ ያስታውሳል፣ እንዲሁም ያደርጋል፡፡ የቱንም ያህል ከገዛ አምሳላችን ጋር ልናመሳስለው ጥረት ብናደርግ እግዚአብሔር ግን ያው ሁሌም እግዚአብሔር እንደሆነ ይኖራል፡፡ የእያንዳንዱን ሰው በዓይነቱ ልዩና ከሌላው የማይገጥም ሰብዓዊ አእምሮ፣ የፊት ገጽታና ባህሪ አበጥሮ ከሚያውቀው አምላክ "ከእርሱ በቀር ሌላ እንደሌለ" (1ነገሥ. 8፡60) አምላካዊው ቃል ይነግረናል፡፡ ደግሞም እርሱ ፈጣሪ ነው፤ እናም እንደ ፈጣሪነቱ እርሱ ከፍጥረት ሥራው ልዩ ነው፡፡

**እግዚአብሔር ከፍጥረት ሥራው የተለየ ስለመሆኑ የሚከተሉት ጥቅሶች ምን ይነግሩናል? 1ሳሙ. 2:2፣ መዝ. 86:8፣ 1ሳሙ. 55:8-9፣ ኤር. 10:10፣ ቲቶ1:2፡፡**

____________________________________________________________

እግዚአብሔር አምላክን ስንመለከት፣ ባለጸግነቱን ስናይና ሥራዎቹን ለመቃኘት ስንሞክር በእርግጥ እርሱ ተወዳዳሪ የሌለው አስደናቂ አምላክ መሆኑን ለመረዳት አንቸገርም፡፡ እንደዚያም ሆኖ ግን ስለ ሰብዓዊው ፍቅርና መውደድ ሲል ራሱን "ውድድር" ውስጥ በመክተት ሲገልጽ ይስተዋላል፡፡ ምናልባት እርሱ "ቀናተኛ"

አምላክ ነኝ ያለበት ምክንያት ይኸው ይሆናል (ዘፀ. 34፡14)፡፡ እግዚአብሔር ለሰዎች ነፃ አስተሳሰብ ሰጥቶ የፈጠረበት ምክንያት እርሱን ወይም ከእርሱ ውጪ የመረጡትን እንዲያመልኩ ምርጫ እንዲኖራቸው ነው፡፡ የመላው ዩኒቨርስ ፈጣሪና ባለቤት የሆነውን፣ ሰብዓዊውን ዘር በአምሳሉ የፈጠረውንና በብቸኝነት አምልኮ የሚገባውን ጌታ ከማገልገል በተቃራኒ ሌሎች አማልክትን መምረጥ--በብዙ መልኩ እየታየ የኖረና ያለ የሰው ልጅ መሰረታዊ ችግር ነው፡፡

**የእግዚአብሔርን ፍቅር እየተፎካከረ ያስቸገረዎ ነገር ካለ ምንድን ነው?**

## ሐሙስ ጥር 10

# እውነተኛ ባለቤትነት

በእግዚአብሔር የተፈጠርንና በእርሱ የተዋጀን እንደመሆናችን ያው የእርሱ ነን፡፡ ደግሞም እኛ ብቻ ሳንሆን ያፈራነውም ንብረት የእርሱ ነው፡፡ እኛ ከገዛ ምርጫችን ውጪ በራሳችን ምንም የለንም፡፡

ነገር ግን ዓለማዊው መርኅ ራሳችንን የሀብታችን ባለቤት አድርጎ በተቃራኒ ያስተምራል፡፡ ነገር ግን ይህ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ቃል ከሚያስተምረው በተቃራኒ የምድራዊ ሀብታቸው የመጨረሻው ባለቤት እንደሆኑ አድርገው እንዲያስቡ የተቀናበረ ማታለያ ነው፡፡

የሁሉም ነገር ባለቤት እግዚአብሔር እንጂ እኛ አይደለንም (ኢዮብ 38፡4-11)፡፡ የተስፋው ምድር ለእስራኤሎች ቃል እንደተገባው እኛም እንግዶችና ጭሰኞች ነን፡፡ ቀጣይዋ እስትንፋሳችን ሳትቀር በእግዚአብሔር ላይ ጥገኛ ናት (ሐዋ. 17፡25)፡፡ እኛ የራሳችን ነው ብለን የምናስበው የእርሱ ነው፡፡ የእርሱ መጋቢዎች እንደመሆናችን ተጨባጩንም ሆነ ተጨባጭ ያልሆነውን ንብረት ለእግዚአብሔር ክብር ልናስተዳደር የተገባ ነው፡፡

**በጥቅሶቹ መሰረት የእግዚአብሔር የሆኑትን ንብረቶች ዘርዝረው ለማስቀመጥ ይሞክሩ ዘዳ. 10:14፣ መዝ. 50:10፣ 104:16፣ ሕዝ. 18:4፣ ሐጌ. 2:8፣ 1ቆሮ. 6:19, 20፡፡ በሀብትነት የያዝናቸውን ነገሮች እንዴት ልንመለከት እንደሚገባ አስመልክቶ ጥቅሶቹ ምን ይነግሩናል?**

__________________________________________________________________________

“ሁሉም ነገር የእግዚአብሔር ነው፡፡ ሰዎች የእግዚአብሔርን ባለቤትነት ችላ ይሉ ይሆናል፡፡ እርሱ በለጋስነት በረከቱን ሲያፈስላቸው ስጦታዎቹን ለገዛ ራሳቸው ራስ ወዳድ ፍላጎት ማርኪያነት ሊጠቀሙ ቢችሉም፤ ነገር ግን ስለ መጋቢነታቸው ምላሽ እንዲሰጡ ይጠራሉ፡፡” —Ellen G. White, *Testimonies for the Church*, vol. 9, p. 246.

የእግዚአብሔር ባለቤትነትና በአደራ የተቀበልነው የመጋቢነት ግንኙነት እኛን ለሰማይ ገጣሚ አድርጎ በማዘጋጀት ለሌሎች ጥቅምና በረከት ያስገኛል፡፡ ነገር ግን ታማኝ ያልሆኑ መጋቢዎች ባለቤቱ የገዛ ንብረቱን መጠቀም እንዳይችል ይገድባሉ፡፡ በትናንቱ ጥናታችን እንደተመለከትነው እግዚአብሔር ፈቃዱን እንድናደርግ አያስገድደንም፡፡ እርሱ እኛን ከፈጠረ በኋላ እርሱን ወክለን ዳግም እስኪገለጥ በዚህ ዓለም የምናስተዳድረው ሀብት ንብረት ሰጥቶናል፡፡ በእጃችን ባለው ንብረት ላይ የምንወስነው ውሳኔ ከእርሱ ጋር ያለንን ግንኙነት ያንጸባርቃል፡፡

***ነገሩን በእውነት ከተመለከቱት እርስዎ ባለቤት ከሆኑባቸው ነገሮች ውስጥ አንዱም የእርስዎ አይደለም፡፡ ሁሉም የእግዚአብሔር ስለ መሆኑ እስቲ አሰብ ያደርጉ፡፡ ሁኔታው ከንብረትዎ ጋር ሊኖርዎት ስለሚገባው ዝምድና ምን ሊነግርዎ ይችላል?***

## አርብ ጥር 11

***<u>ተጨማሪ ሀሳብ</u>፡*** *መጋቢነት የተሰኘውን ጽንሰ ሀሳብ እንደምናስተውለው ኃላፊነቱ የተጀመረው እግዚአብሔር ውብ የሆነውን የኤደን አትክልት ስፍራ ለአዳምና ለሔዋን መኖሪያቸው አድርጎ እንዲንከባከቡና እንዲጠብቁ በሰጣቸው ጊዜ ነበር (ዘፍ. 2፡15)፡፡ እነዚህ ጥንዶች በዚህ ፍጹም ስፍራ የሚገኘውን የአትክልት ቦታ ምቹ አድርገው ማሳመር የነበረባቸው ሲሆን ኃላፊነቱ ደግሞ ከአቅማቸው በላይ አልነበረም፡፡ እግዚአብሔር ለአዲሱ ሥራ ተገቢውን ሹመት በመስጠት የኃላፊነታቸውን ድርሻ በአግባቡ አስተምሯቸዋል፡፡ ኤደንን መንከባከብ ትርጉም ያለው ህይወት ከመስጠቱ ባሻገር ለአዲሱ ቤተሰብ ደስታ የሚያመጣ ነበር፡፡*

*በዘፍ. 1፡26፣28 “ሥልጣን ይኑራቸው” በሚል ጥቅም ላይ የዋለው የዕብራውያን ቃል “ቁጥጥር ማድረግና ማስተዳደር” የሚል ፍቺ አለው፡፡ አባባሉ በጭካኔና በማንቀጥቀጥ መግዛት ሳይሆን የእግዚአብሔርን ፍጥረታት በደግነት መንከባከብ የሚል አውድ አለው፡፡ ይህ ኃላፊነት ዛሬም አለ እንጂ አላበቃም፡፡ አዳምና ሔዋን ይኖሩበት በነበረው በዚያ ቅዱስ ድባብ እግዚአብሔር የሁሉም ነገር ባለቤት፤ እነርሱ ደግሞ የንብረቱ አስተዳዳሪዎችና መጋቢዎች መሆናቸውን መማር ነበረባቸው፡፡ ገና ከመጀመሪያው አዳምና ሔዋን*

የማስተዳደሩን ኃላፊነት በመውሰድ ለእርሱ ያላቸውን ታማኝነት እንዲያሳዩ እንጂ ባለቤቶች እንዲሆኑ አምላካዊው እቅድ አልነበረም፡፡ ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እየተወጡ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ታማኝነት ማሳየት ከእነርሱ ይጠበቅ ነበር፡፡

“አዳምና ሔዋን የኤደንን የአትክልት ስፍራ እንዲንከባከቡ ተሰጣቸው፡፡ እንዲያለሙና እንዲጠብቁ ኃላፊነቱን ወሰዱ፡፡ እነርሱ በሥራቸው ደስተኞች ነበሩ፡፡ አእምሮአቸው፣ ልባቸውና ፈቃዳቸው ፍጹም ስምሙ ነበር፡፡ በሥራ መድከምም ሆነ ልፋት አያውቁም፡፡ ጊዜና ሰዓታቸው በጠቃሚ የሥራ እንቅስቃሴ ብሎም እጅግ በቀረበ የእርስ በርስ ግንኙነት የተሞላ ነበር፡፡ የሚሠሩት ሥራ በእጅጉ አስደሳች ነበር፡፡ እግዚአብሔር አብ እና እግዚአብሔር ወልድ ይጎበኟቸውና ያናግሯቸው ነበር፡፡ ፍጹም ነጻነት የተሰጣቸው የእነዚህ ጥንዶች. . . መኖሪያ የነበረው ኤደን ባለቤት እግዚአብሔር ነበር፡፡ እነርሱም ከእርሱ በታች ሆነው ያስተዳድሩት ነበር፡፡”—Ellen G. White, *Manuscript Releases*, vol. 10, p. 327.

## የመወያያ ጥያቄዎች:

**❶ እግዚአብሔር የዚህ ዓለም ባለቤት የመሆኑ ሐቅ ከአካባቢያችን ጋር በተያያዘ ስላለብን መሰረታዊ ኃላፊነት ምን ያስተምረናል? ምንም እንኳ አንዳንድ አክራሪ አመለካከት ያላቸው ሰዎች እንደሚያደርጉት ራሱን ፍጥረትን ማምለክ ባይዳዳንም ነገር ግን እንደ ክርስቲያን አካባቢያችንን ስለ መንከባከብ ምን ዓይነት አመለካከት ሊኖረን ይገባል?**

**❷ እግዚአብሔር “ቀናተኛ” አምላክ ስለመሆኑ በሚገልጸው ጽንሰ ሀሳብ ዙሪያ ጠለቅ ያለ ምልከታ ያድርጉ፡፡ ይህን ጽንሰ ሃሳብ ማስተዋል ሁሌም ቀላል ላይሆን ይችላል፡፡ በተለይ ሰብዓዊው አባባል ሃሳቡን ከእኛ ልናርቅ ወደሚገባ አሉታዊ አባባል ማለትም ወደ ምቀኝነት መውሰዱን ተከትሎ፡፡ ታዲያ በተለምዶ አግበስብሶ ከሚይዘው አሉታዊ ፍቺ በተቃራኒ ይህን ቃል ማስተዋል የምንችለው እንዴት ነው?**

**❸ እግዚአብሔር የፈጠራቸውን ነገሮች በአግባቡ በመጠቀምና ጉዳት በማድረስ መካከል ያለውን ልዩነት እንዴት መማር እንችላለን? ልዩነቱን ጠንቅቆ መገንዘብ ጠቃሚ የሆነው ለምንድን ነው?**

# አራተኛ ትምህርት

ከጥር 12 – 18

# ከዓለማዊ አካሄዶች ማምለጥ

**ሰንበት ከሰዓት**

***ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ መዝ. 119:11፣ ኤፌ.6:18፣ ሮሜ 8:5-6፣ ዕብ. 11:1–6፣ 1ነገሥ. 3:14፣ ሕዝ. 36:26-27፡፡***

**የሳምንቱ ጥቅስ፡-** "በቁጣ ቀን ሀብት ፋይዳ የለውም፤ ጽድቅ ግን ከሞት ትታደጋለች፡፡… በሀብቱ የሚታመን ሁሉ ይወድቃል፤ ጻድቃን ግን እንደ አረንጓዴ ቅጠል ይለመልማሉ፡፡" *(ምሳ. 11:4፣ 28)፡፡*

ምንም እንኳ ሰይጣን በየሱስ ባይሳካለትም እያንዳንዱን ሰብዓዊ ፍጡር መጣል ችሎአል፡፡ እርሱ ብቻ ነጻነት ሊሰጠን በሚችለው አምላክ ታምነንና በመንፈሳዊው የጦር ትጥቅ--በእግዚአብሔር ኃይል ካልተዋጋን፤ ዓለም እኛን አባብሎ ከመውሰድ አይቦዝንም፡፡

ስለዚህ ትኩረታችንን በሰማያዊው ቸርነት ላይ ልናደርግ የግድ ነው፡፡ ዳዊት የሚከተለውን ሲጽፍ ይህ ህይወት ያለውን እውነተኛ ዋጋ ተገንዝቧል፡፡ "አንበሶች ሊያጡ፣ ሊራቡም ይችላሉ፤ እግዚአብሔርን የሚሹ ግን መልካም ነገር አይጎድልባቸውም፡፡" (መዝ. 34:10)፡፡ ሰለሞን ጥበብና ማስተዋል ከብርና ወርቅ የላቀ ዋጋ እንዳለው ተረድቷል (ምሳ. 3:13-14)፡፡ ዐይኖቻችንን ከንብረቶቻችን ላይ

አንስተን የሁሉም ባለቤት በሆነው ክርስቶስ ላይ ስናሳርፍ፤ ያን ጊዜ የእውነተኛ ደስታና ቀና ህይወት ባለቤት እንሆናለን፡፡

ስሜታችንን በቀላሉ መግዛት ከሚችለው ከአማላዩ ዓለም ማምለጥ የምንችለው ከየሱስ ጋር በምንፈጥረው ስኬታማ ብሎም ወሳኝ ግንኙነት ነው፡፡ በዚህ ሳምንት የዚህን ግንኙነት አላባዎች እናጠናለን፡፡ ከጭምብሉ ዓለም በስተጀርባ የሚገኘውን ኃይል ለይተን ማወቃችን ለገዛ ራሳችን መንፈሳዊ ህይወት ስኬት ምን ያህል ፋይዳ እንዳለውና፤ ክርስቶስ በዚህ ምድር ለመመላለሳችን ምን ያህል ተጨባጭ ምክንያት እንደሆነ እናያለን፡፡

## እሁድ ጥር 13

# ከክርስቶስ ጋር የተመሰረተ ግንኙነት

እምብዛም የተትረፈረፈ ነገር የሌላቸውን ጨምሮ የዚህን ዓለም ንብረት የሚወዱ ሰዎች ነፍስ--ከክርስቶስ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ሊኖራት ሲገባ፤ ከዚህ ዓለም ጋር በብርቱ ሰንሰለት ተቆራኝታለች፡፡ እዚህ ግባ የማይባል ምድራዊ ሀብት ንብረት ሊኖረን ባይችልም ነገር ግን አንቅልፍ አጥተን ቁሳዊውን ነገር የምንመኝ ከሆነና፤ ይኸው አጉል ምኞት በጌታ ቁጥጥር ስር መዋል ካልቻለ፤ ነፍስን ከደኅንነት መስመር አውጥቶ ለአስከፊ ችግር ሊዳርግ ይችላል፡፡ ሰይጣን ይህን ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ሰዎችን በቁሳዊው ነገር ፍቅር ለማጥመድ የተቻለውን ያህል ይሠራል፡፡

***ታዲያ ለዚህ ብቸኛው መከላከያችን ምንድን ነው?***

**“አሳባችሁም በላይ ባለው ላይ እንጂ በምድራዊው ነገር ላይ አይሁን” (ቆሊ. 3፡2)፡፡ ጳውሎስ አድርጉ ያለንን የምናደርገው እንዴት ነው? (በተጨማሪ እነዚህን ጥቅሶች ይመልከቱ፡ መዝ. 119፡11፣ ኤፌ. 6፡18)፡፡**

--------------------------------------------------------------------------------------------

**አስተሳሰባችን በምን ላይ ሊያርፍ እንደሚገባ የሚናገር ሌላ ጥቅስ ማግኘት ይችላሉ? (ፊልጵ. 4፡8)**

--------------------------------------------------------------------------------------------

ከክርስቶስ ጋር የሚደረግ የማያቋርጥ አምልኮ (መዝ. 34፡1) የህይወትን ውጣ ውረድ ተከትሎ በየትኛውም አቅጣጫ ሊመጣ ከሚችል ዓለማዊነት ብቸኛው ፈውስ ነው፡፡ ሙሴ "ከግብፅ ሀብት ይልቅ ስለ ክርስቶስ መከራን መቀበል እጅግ የሚበልጥ ሀብት መሆኑን ተገነዘበ" (ዕብ. 11፡26)፡፡ ከማንኛውም ግንኙነት በፊት ቅድሚያ ልንሰጥ የሚገባው ለክርስቶስ ነው፡፡ ክርስቶስ በጽኑ እምነት ላይ የተመሰረተ መተማመን ከእኛ ይፈልጋል፡፡ ይህ ማለት እርሱ--እርሱ በመሆኑና ስላደረገልን ነገር ልናመልከው ይገባል እንጂ እምነታችንና ቁርጠኝነታችን ሊያስገኝልን የሚችለውን ጥቅም ተከትሎ መሆን የለበትም፡፡

ህይወታችን በየሱስ ሊሸሸግ፣ አምላካዊው ዕቅድም እቅዳችን ሊሆን የተገባ ነው፡፡ እውነተኛ ቁርጠኝነት እርፍ ጨብጦ "ወደ ኋላ" አለመመልከት ነው (ሉቃ. 9፡62)፡፡ እንደዚያ ያለውን ኪዳን ስንጠብቅ የሱስ በሙላት የምንንቀሳቀስበትን ኃይል ይሰጠናል፡፡ ራሳችንን ለእርሱ ስናስገዛ ይህ ዓለም በነፍሳችን ላይ ያለውን ይዞታ ይሰባብርልናል፡፡ ህይወታችን ተብለጭላጩን ግዑዝ ሳይሆን በነፍሳችን ውስጥ ያለውን ክፍተት ሊሞላ የሚችለውን ክርስቶስ ያማከለ ሊሆን የግድ ነው፡፡

**እጅግ አጥብቀው ሽተውት ስለነበር ቁሳዊ ንብረት አሰብ ያድርጉ፡፡ የፈለጉትን እጅዎ ካስገቡ በኋላ በውስጥዎ የነበረው ደስታ ሳይደበዝዝ ለምን ያህል ጊዜ አብሮት መቆየት ቻለ?**

## ሰኞ ጥር 14

# በዓለም ውስጥ

**በዓለም ዙሪያ ከስድስት ቢልዮን የሚበልጡ መጽሐፍ ቅዱሶች ተሰራጭተዋል፡፡ ታዲያ ከእነዚህ ውስጥ እንደ ሕያው አምላክ ቃል የተስተዋሉት ስንቶቹ ናቸው? እውነትን ለማወቅ በቅን ልቦና የተነበቡትስ ምን ያህል ይሆኑ?**

የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ--ዮሐ. 5፡39፤ 14፡6፤ 20፡31፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ--በተለይም ወንጌል ስለ የሱስ እጅግ ጠቃሚ መረጃ ይሰጠናል፡፡ **በዮሐንስ ወንጌል**

**የተጠቀሱት እነዚህ ጥቅሶች በተለይ ስለ እርሱ ምን ይላሉ? እርሱ ለእኛም ሆነ ለእምነታችን ያን ያህል አስፈላጊ የሆነበት ምክንያቱ ምንድን ነው?**

__________________________________________________________________________

__________________________________________________________________________

መጽሐፍ ቅዱስን የምናጠናው የእውነት ዋንኛው ምንጭ ስለሆነ ነው፡፡ የሱስ እውነት ነው፡፡ ይህ እውነት በመጽሐፍ ቅዱስ መገለጡን ተከትሎ እርሱን ወደ ማወቅ እንመጣለን፡፡ ብሉይ ኪዳንም ሆነ አዲስ ኪዳን ስለ የሱስ ማንነትና እርሱ ለእኛ ስላደረገልን ነገር በቂ ዕውቀት ይሰጡናል፡፡ ይህ ዕውቀት ከእርሱ ጋር በፍቅር ይጥለንና ህይወታችንንም ሆነ ነፍሳችንን በዘላለማዊ ጥበቃው ስር እናስገዛለን፡፡ የሱስን በመከተልና በአምላካዊው ቃል የተገለጸውን ቃሉን በመታዘዝ ከዓለምና ከኃጢአት ግዞት ነጻ መውጣት እንችላለን፡፡ "እንግዲህ ወልድ ነጻ ካወጣችሁ፣ በእውነት ነጻ ትሆናላችሁ" (ዮሐ. 8፡36)፡፡

**በሮሜ 8፡5-6 የተሰጡን ማስጠንቀቂያዎች ምንድን ናቸው? የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት በአእምሮአችን ለሚካሄደው ትግል እንዴት ሊረዳን ይችላል?**

__________________________________________________________________________

ዓለምን መውደድ በተለይም ለምድራዊው ቁስ የሚኖር ፍቅር ተገቢውን ጥንቃቄ ካላደረግን በቀር በቀላሉ ከእግዚአብሔር ሊያርቀን ይችላል፡፡ ለክርስትና ህይወት እጅግ ወሳኝ የሆነውን--ዘላለማዊና ተጨባጭ መንፈሳዊ እውነታዎችን በሚያመላክተን በቃሉ ውስጥ ተጠብቀን መኖር አለብን፡፡

ለዓለማዊ ነገሮች የሚኖር ፍቅር አእምሮን ላቅ ወዳለ መንፈሳዊ ምግባር ማሳደግ አይችልም፡፡ ይልቁንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርኅዎችን በስግብግብነት፣ በራስ ወዳድነትና በክፉ ምኞት ይተካቸዋል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተገለጠው--ፍቅር ራሳችንን ለሌሎች የመስጠትን አስፈላጊነት በማስተማር ግንኙነትን ያጠናክራል፡፡ ዓለማዊነት ግን የሱስ ከሚወክለው ማንኛውም እውነት በተቃራኒ ሁሉንም ነገር ለራስ ብቻ ያግበሰብሳል፡፡

**ማክሰኞ** **ጥር 15**

# የጸሎት ህይወት

“ ‘አንተ ብቻ እውነተኛ አምላክ የሆንኸውንና የላክኸውን ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት’ ” (ዮሐ. 17:3)፡፡ ብዙውን ጊዜ ክርስቲያኖች እምነታቸው ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት መሆኑን ሲናገሩ መደመጣቸው እምብዛም አይገርምም፡፡ እግዚአብሔርን ማወቅ “ ‘የዘላለም ሕይወት’ ” ከሆነ፤ ይህን ሕይወት ከእርሱ ጋር በሚኖር ግንኙነት እናገኘዋለን እንደ ማለት፡፡ ደግሞም የዚህ ትስስር ማዕከል ግንኙነት መሆኑ አይታበልም፡፡ በትናንቱ ጥናታችን እግዚአብሔር በመለኮታዊ ቃሉ አማካኝት እንደሚገናኝን መመልከታችንን ልብ ይሏል፡፡ እኛም በበኩላችን በጸሎት አማኝነት ከእርሱ ጋር መገናኘት እንችላለን፡፡

ከላይ እንደ ተመለከትነው አዕምሮአችንንና ልባችንን ከዚህ ዓለም ነገሮች በተቃራኒ በሰማያዊ ነገሮች ላይ የምናኖር እስከሆነ ድረስ ጸሎት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ የሆነው ጸሎት ከራሱ ከዓለም ይልቅ እኛን ከፍ ወዳለው ግዛት የማመላከት ተፈጥሮ ስላለው ነው፡፡

ጸሎታችንም ቢሆን አንዳንዴ ራስ ወዳድነታችንን ብቻ የማንጸባረቅ ባህሪ ሊኖረው ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ አለብን፡፡ ጸሎታችንን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ማስገዛት ተቀዳሚ ተግባራችን ሊሆን የተገባ ነው፡፡

ይህን የተሳሳተ ጽንሰ ሃሳብ በመዝሙር ለማሳየት የፈለገች አንዲት ሴት “አ ጌታ ሆይ፤ አንዲት ማርቼዲስ አትገዛልኝም ወይ?” ብላ ነበር፡፡ እኛም ብንሆን ለዓለም መሞታችንን በምናሳይበትና ራሳችንን ለእግዚብሔር አሳልፈን በምንሰጥበት በጸሎት ወደ ጌታ ስንቀርብ፤ የእርሱን ፈቃድ እንጂ የራሳችን ላለመሻታችን እርግጠኞች ልንሆን የተገባ ነው፡፡

የጸሎታችን አካል ሊሆን የተገባው ዕብ. 11፡1-6 ላይ የምናገኘው እጅግ አስፈላጊ ክፍል ምንድን ነው? **በተጨማሪ በእምነት ወደ ጌታ መምጣትና መጸለይ ምን ማለት ነው?**

ከጸሎታችን ጋር የተሳሰረ እምነት ከሌለን ከንቱ ድፍረትና የሰይጣን ከአንገት በላይ እምነት በውስጣችን ሊገለጥ ይችላል፡፡ “ጸሎትና እምነት በቅርብ የተሳሰረ ህብረት ስላላቸው በአንድነት ሊጠኑ የተገባ ነው፡፡ በእምነት የሚጸለይ ጸሎት ውስጥ መለኮታዊ ሳይንስ አለ፡፡ ህይወቱን በተሳካ ሁኔታ የሚያከናውን እያንዳንዱ ሰው ይህን ሳይንስ መረዳት አለበት፡፡ ክርስቶስ እንዲህ ይላል ‘ስለዚህ በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ እንደተቀበላችሁት አድርጋችሁ ብታምኑ ይሆንላችኋል፡፡’ (ማር. 11:24)፡፡ ልመናችን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሊሆን እንደሚገባ በግልጽ አስቀምጠልናል፡፡ በመሆኑም እንደሚሰጠን ቃል የገባልንን ነገሮች መጠየቅና የምንቀበለውን ነገር የእርሱን ፈቃድ ለመፈጸም ማዋል ይኖርብናል፡፡ የተጠየቀው ከተሟላ ተስፋው ቁርጥ ያለና የማያጠራጥር ነው፡፡” — Ellen G. White, *Prayer*, p. 57.

**ወደ ራስዎ የጸሎት ህይወት ይመልከቱ፡፡ ስለ ምን ይጸልያሉ? ቅድሚያ ስለሚሰጧቸው ነገሮች ጸሎትዎ የሚናገረው ነገር አለ? ሊጸልዩባቸው የሚገቡ ሌሎች ነገሮች ምን ሊሆኑ ይችላሉ?**

## ረቡዕ ጥር 16

# የጥበብ ሕይወት

በመጽሐፍ ቅዱስ ከምናገኛቸው እጅግ ውብ ታሪኮች አንዱ እግዚአብሔር ከሁሉ አስበልጦ እንዲሰጠው ሰሎሞን ያቀረበው ልመና ነው፡፡ “መልካሙንና ክፉውን በመለየት ሕዝብህን ማስተዳደር እንዲችል ለባሪያህ አስተዋይ ልብ ስጠው፤ አለዚያማ ይህን ታላቅ ሕዝብህን ማን ሊያስተዳድር ይችላል?’ ” (1ነገሥ. 3:9)፡፡

ሰለሞን የእግዚአብሔርን ሀሳብ ሰምቶ የሚከተል ከሆነ ምድራዊ ሀብትና ብልጽግና ሊያደርስበት ከሚችለው ውድመት እንደሚታደገው ለሰሎሞን የነገረው ጠቃሚ ነገር ምን ነበር? 1ነገሥ. 3:14፣ 1ዮሐ. 5:3፣ 1ጴጥ. 4:17፡፡

________________________________________________________________

________________________________________________________________

ሰሎሞን የታላቅ ጥበብ ባለቤት ነበር፡፡ ሆኖም ጥበብ እንደሚገባው ካልተመላለሱባት ከመልካም መረጃ ያለፈ ዋጋ አይኖራትም፡፡ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚነግረን ጥበብ በመጽሐፍ ቅዱሳዊው አባባል መሰረት ገቢራዊ መሆን ካልቻለ እውነተኛ ጥበብ አይደለም፡፡ ስለ እግዚአብሔር አምላክና እርሱ ከእኛ ስለሚፈልገው ነገር መጠነ ሰፊ ትክክለኛ መረጃ የነበሯቸው ብዙዎች በዓለም ተውጠው ጠፍተዋል፡፡ የሰሎሞን እግዚአብሔርን ሳይታዘዝ መቅረትም ጌታ በጠራው መንገድ ከመራመድ ባከኖ እንዲቀር መንስኤ ሆኖት ነበር፡፡ ሆኖም የዕድሜው አመሻሽ ላይ በእውነት ወደ ህሊናው ተመልሶ እንዲህ ሲል በትህትና ጻፈ "ጥበብ ከቀይ ዕንቁ ይበልጥ ውድ ናትና፤ ከምትመኙት ነገር ሁሉ አንዳች የሚስተካከላት የለም" (ምሳ. 8፡11)፡፡

ጥበብ የዕውቀትና ማስተዋል ትግበራ ነው፡፡ ዕውቀት በማስረጃ የተደገፈውን እውነት--ግንዛቤ ደግሞ ማስተዋልን ይወክላል፡፡ ዕውቀታችንንና ማስተዋላችንን በሕይወታችን ላይ ማዋል ስንችል በሂደት ጥበብ ይመጣል፡፡ ብልህ መጋቢ የሚሻው ዕውቀትንና ማስተዋልን ብቻ ሳይሆን በዕውቀትና ማስተዋል በመመላለስ የሚያካብተውን ተሞክሮ ነው፡፡

አንድ ሰው በተሰጠው ጥበብ ካልተመላለሰ፤ እጅግ አስተዋይና ብልህ የተባሉ ሰዎች ሳይቀር ባዶ በሆነው ቁስ የተከበበ አኗኗር ዘይቤ በቀላሉ ተጠልፈው ሊጠፉ እንደሚችሉ የሰሎሞን ምሳሌ ያሳየናል፡፡

**ሁለቱን ጥቅሶች ያመሳክሩ፡ 1ቆሮ. 3፡19፣ ምሳ. 24፡13-14፡፡ በሁለቱ የጥበብ ዓይነቶች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? መልስዎን ለሰንበት ትምህርት ጥናት አባላት ለማካፈል ይሞክሩ፡፡**

## ሐሙስ ጥር 17

# መንፈስ ቅዱስ

በበጎና በክፉ መካከል ውጊያ እየተካሄደ መሆኑ እሙን ነው፡፡ አንደኛው ወገን ወደ ክርስቶስ (ዮሐ. 6፡44) ሌላኛው ደግሞ ወደ ዓለም ይስበናል (1ዮሐ. 2፡16)፡፡ እኛ

ራሳችንን ለማስገዛት ፈቃደኞች ከሆንን፤ በሕይወታችን ውስጥ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ ሊመራን ይችላል--ፈቃደኛም ነው፡፡

" 'የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል' " (ዮሐ. 16፡13፣ ዮሐ. 14፡16)፡፡ መንፈስ ቅዱስ የራሱን መንገድ በሚሻና በስሜታዊነት ሳይሆን በመርኀና በእውነት ላይ የተመሰረተ ህይወት እንድንኖር ኃይል ይሰጠናል፡፡ ለሰማያዊው ሕይወት ገጣሚ ዝግጅት ማድረግ ማለት በዚሁ ምድር በመንፈስ ቅዱስ አመራር የሚመላለስ ታማኝ ህይወት መኖር መጀመር ነው፡፡

ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይመክራል "ይኸውም እምነታችሁ በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰው ጥበብ ላይ እንዳይመሰረት ነው" (1ቆሮ. 2፡5)፡፡ ብዙውን ጊዜ ዓለም በማባበያ ቁስ እየተጠቀመ ከጌታ ወደ ራሱ ቢስበንም፤ የመንፈስ ቅዱስ ኃይል ደግሞ መልሶ ወደ ጌታ ሲያመጣን ይስተዋላል፡፡

**ከዓለምና ከማባበያዋ ጋር በሚደረግ ውጊያ የሚገኘው ስኬት የሚመጣው ከእኛ በላይ በሆነ ኃይል ነው--ሕዝ. 36:26-27፣ ዮሐ. 14:26፣ ኤፌ. 3:16-17፡፡ መንፈስ ቅዱስ እንዲገዛን ስንፈቅድ የመንፈሳዊ ድል ባለቤቶች መሆናችንን ለማረጋገጥ እግዚአብሔር ምን ዓይነት ነገሮችን ያደርጋል?**

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

"ሰይጣን በሰብዓዊው አእምሮ ላይ ኃይልና ብርታት እንዲኖረው የሚያስችሉት፤ ሐሰተኛ ንድፈ ሃሳቦችና ባህሎች ናቸው፡፡ የሰዎችን ትኩረት ሐሰተኛ መሰረት ወዳላቸው ነገሮች እየመራ የተሳሳተውን ባህሪ በውስጣቸው ይቀርጻል፡፡ መንፈስ ቅዱስ በአምላካዊው ቃል አማካይነት ለአእምሮ እየተናገረ እውነትን በልብ ውስጥ ያነቃቃል፡፡ በዚህም ስህተትን እያጋለጠ ከነፍስ ውስጥ ያባርራል፡፡ ክርስቶስ ምርጦቹን ሕዝቦቹን በስሩ የሚያስገዛው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በሚሠራው የእውነት መንፈስ አማካኝነት ነው፡፡" —Ellen G. White, *The Desire of Ages*, p. 671.

የሱስ ከእርገቱ በኋላ እግዚአብሔርን በምድር እንዲወክል ሊሰጠን የሚችለው የመጨረሻው ስጦታ የእውነት ዘጋቢ የሆነውን መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ ዓለምንና ዓለማዊውን “አዚም” የምናሸንፍበትን ኃይል ለእኛ ለመስጠት ብርቱ ፍልሚያ ያደርጋል፡፡

**ዓለም ሁላችንንም የመሳብ ኃይል አላት--አይደል? የዓለምን ፈተና ለመቋቋም የሚያስችል ኃይል ሊሰጥዎ ለሚችለው ለመንፈስ ቅዱስ ራስዎን አሳልፈው ለመስጠት የሚረዳዎ--ምን ዓይነት ምርጫ ባሁኗ ደቂቃ ማድረግ ይችላሉ?**

## አርብ ጥር 18

***<u>ተጨማሪ ሀሳብ</u>*፡-** *መጋቢነት በሁለት መንታ መርኅዎች ይዘወራል--በውዴታ ግዴታ እና በፍቅር፡፡ “የውዴታ ግዴታ--ፍቅር የምትባል መንትያ እህት እንዳለችው አንዘንጋ፡፡ ታዲያ ሁለቱ ኅብረት ከፈጠሩ የሚሳናቸው ነገር የለም፡፡ ከተነጣጠሉ ግን--አንዳቸውም በተናጥል መልካም የማድረግ ችሎታ የላቸውም፡፡”* —Ellen G. White, *Testimonies for the Church*, vol. 4, p. 62. ፍቅርን በተግባር ገልጦ ማሳየት የውዴታ ግዴታ ነው፡፡ ፍቅር በውስጣችን መነሳሳት ይፈጥር ዘንድ ሁሌም በክርስቶስ *መሥዋዕትነት* ውስጥ ብቻ ውለን ልናድር ይገባል፡፡

*መንትዮቹ ጥላቻና ዐመፅ ከላይ ከቀረቡት ተቃራኒ የዓለም መርኅዎች ናቸው፡፡ ዐመፅ ጥላቻ በተግባር የሚገለጥበት መንገድ መሆን ይችላል፡፡* ሉሲፈር በእግዚአብሔር ላይ *ዐመፀ* (ሕዝ. 28፡16-17)፡፡ እርሱ እስከ መጨረሻ እስከሚወገድ *ይህን የዐመፃ ተግባር ከማድረግ አይገታም፡፡* እርሱ የፍቅርን *ሥ*ልጣን ወደ የ*ሥ*ልጣን ፍቅር ገለበጠው፡፡ የሱስ የነበረውን *ሥ*ልጣንና ኃይል አብልጠው ይጠሉ የነበሩት የእስራኤል *ኃይማኖት መሪዎች መንገዳቸውን* አልለወጡም ነበር (ማቴ. 22፡29)፡፡

# የመወያያ ጥያቄዎች፡

❶ በፍቅርና በውዴታ ግዴታ ጽንሰ ሃሳብ ዙሪያ ጠለቅ ያለ ምልከታ አድርጉ፡፡ ኤለን ኋይት ፍቅርንና የውዴታ ግዴታን—መንትዮች ብላ በመጥራት “እንዳቸውም በተናጥል መልካም የማድረግ ችሎታ የላቸውም” ስትል ምን ማለቷ ነው? ፍቅር ያለ ውዴታ ግዴታ ምን ሊመስል ይችላል? የውዴታ ግዴታስ ያለ ፍቅር ምን ዓይነት ገጽታ አለው? ሁለቱ መነጣጠል የሌለባቸው ለምንድን ነው?

❷ የዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን መሪ ጥቅስ እንዲህ ይላል፡ “በቁጣ ቀን ሀብት ፋይዳ የለውም፤ ጽድቅ ግን ከሞት ትታደጋለች፡፡… በሀብቱ የሚታመን ሁሉ ይወድቃል፤ ጻድቃን ግን እንደ አረንጓዴ ቅጠል ይለመልማሉ፡፡” (ምሳ. 11፡4፣ 28)፡፡ የዚህ ጥቅስ ፍቺ ምንድን ነው? ስለ ሀብት ምን እያለ ነው? የማይለውስ ምንድን ነው?

❸ በሰሎሞን ህይወት ዙሪያ ተወያዩ፡፡ ከአምላካዊው መንገድ ምን ያህል ጭልጥ ብሎ መሄድ ይችል እንደ ነበር ተጠያየቁ፡፡ በምድራዊው የተትረፈረፈ ሀብት ከንቱነትና ባዶነት ዙሪያ በመጽሐፈ መክብብ የተጻፉ ጥቅሶችን ተመልከቱ፡፡ ትክክለኛውን መንፈሳዊ አካሄድ ጠብቀን ለመጓዝ ስለሚያስችለን ማለትም—ስለ ጸሎት፣ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ከክርስቶስ ጋር ሊኖረን ስለሚገባ ግንኙነት በዚህ ሳምንት ያገኘነው ትምህርት ምንድን ነው?

❹ ሰዎች እዚህ ግባ የማይባል ሀብት ወይም ንብረት ሳይኖራቸውም ሰይጣን በሚያዘጋጅላቸው ወጥመድ የሚወድቁት ለምንድን ነው?

❺ በረቡዕ ትምህርት መጨረሻ ለየት ስላለው ጥበብ ለቀረበው ጥያቄ መልስዎ ምንድን ነው?

# አምስተኛ ትምህርት

ከጥር 19 – 25

# መጋቢነት በድኅረ ኤደን

**ሰንበት ከሰዓት**

**ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡** ኢሳ. 22:14–18፣ 1ቆሮ. 4:1-2፣ ቆለ. 2:2-3፣ ኤፌ. 6:13–17፣ 2ቆሮ. 5:10፡፡

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡-**

*“ነገር ግን ወንጌልን በዐደራ ለመቀበል እግዚአብሔር ብቁ አድርጎ እንደ ቆጠራቸው ሰዎች ሆነን እንናገራለን፡፡ ይህንም የምናደርገው ልባችንን የሚመረምረውን እግዚአብሔርን እንጂ ሰዎችን ደስ ለማሰኘት ብለን አይደለም፡፡” (1ተሰ. 2:4)፡፡*

የአዳምና ሔዋን የመጀመሪያ ሥራ መጋቢነትን ያካተተ ነበር፡፡ የኤደን አትክልት ስፍራና በውስጧ የነበሩ ፍጥረታት የጥንዶቹ የእጅ ሥራ አንጡራ ሀብት ባይሆኑም ነገር ግን እንዲጠብቋቸው፣ ሐሴት እንዲያረጉባቸውና እንዲንከባከቧቸው ኃላፊነት ተሰጣቸው (ዘፍ. 2:15)፡፡ አዳምና ሔዋን የጌታን አደራ የተቀበሉ መጋቢዎች ነበሩ፡፡

በዚህ ሳምንት የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን ከወደቁና ከኤደን የአትክልት ስፍራ ከተባረሩ በኋላ ባለው የመጋቢነት ፍቺ ዙሪያ ጠለቅ ያለ ምልከታ እናደርጋለን፡፡ እኛም እንደ እነሱ መጋቢዎች ብንሆንም ነገር ግን የእኛ መጋቢነት እነርሱ ከኖሩበት ሁኔታ አኳያ ሲታይ በጣም የተለየ ነው፡፡

ለመሆኑ መጋቢነት ምንድን ነው? የመጋቢነት ምንነት በመጽሐፍ ቅዱስ በተጠቀሱ አንዳንድ ሰዎች ህይወት የተገለጠው እንዴት እንደኖሩ በማሳየት ነው፡፡ የእግዚአብሔር መጋቢዎች ስንሆን በምድርና ቁሳዊ እሴቶች ላይ የሚኖረን ትኩረት ሁሉን ወደ ፈጠረውና ወደ አምላካዊው ተልዕኮ ይቀየራል፡፡ ልክ እንደ አዳምና ሔዋን ሁሉ እግዚአብሔር እነዚያን ቀደምት መለኮታዊ ዐደራዎች ለእኛም ሰጥቶናል፡፡ ሆኖም ከኤደን ውድቀት ወዲህ የመጋቢነት ኃላፊነት ተለውጧል፡፡ ለቁሳዊው ዓለም ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ ከማድረግ ኃላፊነት በተጓዳኝ ለመንፈሳዊው እውነትም መልካም መጋቢዎች እንድንሆን ዐደራ ተጥሎብናል፡፡

**እሁድ** **ጥር 20**

# መጋቢዎች በብሉይ ኪዳን

“መጋቢ” የተሰኘው ቃል በብሉይ ኪዳን ተተርጉሞ የምናገኘው በጥቂት ስፍራዎች ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ መጋቢነት በአብዛኛው የተገለጸው “የቤቱ አዛዥ” በሚሉ የማስተዳደር ኃላፊነትን ያካተቱ ቃላቶች ነው (ዘፍ. 43፡19፤ 44፡1፤ 4፤ 1ነገሥ. 16፡9)፡፡ በቤቱ ላይ በመጋቢነት የተሾሙ ኃላፊዎች የቤቱን ጉዳይና የጌታቸውን ሀብት በተጠየቁት ሁኔታ የማስተዳደር ዐደራ ተቀብለው ነበር፡፡ የመጋቢነትን ባህሪያት ለይቶ በማወቅ በብሉይ ኪዳን የነበረውን የመጋቢነት ፍቺ ማግኘት ይቻላል፡፡ መጋቢዎች ማንነታቸውን ገልጾ ከሚያሳየው የመጋቢነት ኃላፊነት ተለይተው መታየት አይችሉም፡፡

የመጋቢነት አንዳንድ ባህሪዎች በብሉይ ኪዳን በግልጽ ተቀምጠዋል፡፡ መጋቢነት በጊዜው ከነበሩ ታላላቅ ኃላፊነቶች አንዱ መሆኑ--በቅድሚያ ሊታይ የሚገባው ነጥብ ነው (ዘፍ. 39፡4)፡፡ መጋቢዎች በነበራቸው ችሎታ ምክንያት ይመረጡ የነበረ ሲሆን፤ ሥራውን በአግባቡ በመሥራታቸው ከአሳዳሪዎቻቸው ከበሬታና አመኔታ ያገኙ ነበር፡፡ ሁለተኛው ነጥብ--መጋቢዎች እንዲያስተዳድሩት በኃላፊነት የተሰጣቸው ንብረት የጌታቸው መሆኑን ያውቁ ነበር (ዘፍ. 24፡34-38)፡፡ ይህ እንግዲህ በአንድ መጋቢና ባለቤት መሃል የነበረው ከፍተኛ ልዩነት ነው፡፡ መጋቢዎች የተሰጣቸውን ዐደራ ክብደት ጠንቅቀው ያስተውሉ ነበር፡፡ መጋቢዎች

በዐደራ ከተቀበሉት ንብረት ላይ ለግል ጥቅማቸው ካዋሉ በእነርሱና በአሳዳሪያቸው መካከል የነበረው የመተማመን ግንኙነት ስለሚበጠስ ከኃላፊነታቸው ይሰናበታሉ (ዘፍ. 3፡23፣ ሆሴዕ 6፡7)፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ--ኢሳ. 22፡14-18፡፡ በሕዝቅያስ የግዛት ዘመን ሳምናስ በጣም ቁልፍ የሆኑ ሥልጣኖችን ማለትም የመጋቢነትና የገንዘብ ያዥነት ሹመት ተቀብሎ ነበር፡፡ ሳምናስ የተቀበለውን አደራ አላግባብ ሲጠቀም ምን ተከሰተ?**

------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------

“አንድ መጋቢ ራሱን ከጌታው ጋር አንድ አድርጎ ያያል፡፡ የመጋቢነት ኃላፊነቶችን በመቀበል ለጌታው ተጠሪ ሆኖ ልክ እንደ ጌታው ይሠራል፡፡ የጌታው ፍላጎት የእርሱ ይሆናል፡፡ መጋቢው ከአሳዳሪው አመኔታ ማግኘቱ--የመጋቢነትን ዐደራ እጅግ የከበረ ያደርገዋል፡፡ ሆኖም በራስ ወዳድነት ስሜት ተገፋፍቶ በኃላፊነት የተቀበለውን የጌታውን ንብረት ለግል ጥቅሙ ካዋለ አደራ በላ ይሆናል”—Ellen G. White, *Testimonies for the Church*, vol. 9, p. 246.

**በምድራዊው ህይወታችን ባፈራነው ነገር መጋቢ የመሆናችንን አስፈላጊ ጽንሰ ሃሳብ እንዴት በተሻለ መገንዘብ እችላለን? ይህ ግንዛቤአችን በምናደርገው እያንዳንዱ ነገር ላይ ተጽእኖ ሊኖረው የሚችለው እንዴት ነው?**

**ሰኞ** **ጥር 21**

# መጋቢዎች በአዲስ ኪዳን

በአዲስ ኪዳን “መጋቢ” በሚል ጥቅም ላይ ለዋለው ቃል ግሪክኛው ሁለት መሰረታዊ ቃላቶችን የያዘ ሲሆን እነርሱም *ኤፒትሮፖስ* (3 ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ) እና *ኦይኮኖምስ* (10 ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ) ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለቱም ቃላት መጋቢው የባለጠጋውን ንብረት በአደራ እንዲያስተዳድርና እንዲጠብቅ መሾሙን ይገልጻሉ፡፡

በአዲስ ኪዳንም ሆነ በብሉይ ኪዳን መጋቢዎች በሚሠሩት ነገር ይወሰናሉ፡፡ አዲስ ኪዳን መጋቢው ያለበትን ተጠያቂነት (ሉቃ. 12፡48) እና ዐደራ (1ቆሮ. 4፡2) ልዩ በሆነ መንገድ ይገልጻል፡፡ ነገር ግን ብሉይ ኪዳን እኛን እንደ መጋቢ በቀጥታ ከመግለጽ ይልቅ የእግዚአብሔርን ባለቤትነት በማወጅ ላይ ያተኩራል፡፡ ስለዚህ የመጋቢነት ጽንሰ ሃሳብ በሁለቱም ኪዳኖች ተመሳሳይ ሲሆን--አዲስ ኪዳን ግን ጽንሰ ሃሳቡን ከቤተሰብ አስተዳደር በሻገር አስፋፍቶ ያቀርበዋል፡፡

የሱስ ስለ ብልሁ አጭበርባሪ መጋቢ በተናገረው ምሳሌያዊ ታሪክ (ሉቃ. 16፡1-15) የመጋቢነትን ፍቺ ሰፋ አድርጎ አስቀምጧል፡፡ በመሆኑም የእርሱ ትምህርት መጋቢው ከገንዘብ ቀውስ ለመውጣት ከቀየሰው ዘዴ የላቀ አንደምታ አለው፡፡ በተጨማሪ እምነታቸውን ብልህ በሆነ አካሄድ እየገለጹ ከመንፈሳዊ ውድቀት ለሚያመልጡ ገጣሚ ነው፡፡ ብልህ መጋቢ ዛሬን አልፎ ገቢራዊ ለሚሆነው የየሱስ ዳግም ምጽአት ይዘጋጃል (ማቴ. 25፡31)፡፡

**የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ 1ቆሮ. 4፡1-2፣ ቲቶ 1፡7፣ 1ጴጥ. 4፡10፡፡ ጥቅሶቹ ስለ መጋቢዎችና መጋቢነት ምን ይላሉ?**

------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------

“እግዚአብሔር በዐደራ የሰጠኝ እያንዳንዱ ኃይልና ጉልበት መነሳሳት ያገኝ ዘንድ ልቤን ለመንፈስ ቅዱስ ልክፈት? እኔ የክርስቶስ ንብረት በመሆኔ የአገልግሎቱ ተቀጣሪ፣ የጸጋውም መጋቢ ነኝ፡፡” —Ellen G. White, *Fundamentals of Christian Education*, p. 301.

በሉቃ. 12፡35-48 እንደምንመለከተው የሱስ “መጋቢ” የተሰኘውን ቃል ዘይቤአዊ በሆነ መንገድ ሲጠቀም ይስተዋላል፡፡ ታማኙና ብልሁ መጋቢ የሰው ልጅ ሲገለጥ ዝግጁ ሆኖ እንደሚገኝ--ታማኝ ያልሆነው መጋቢ ግን ጌታዬ ቶሎ አይመጣም፣ ይዘገያል ብሎ በማሰብ የተቀበለውን ዐደራ ሳይወጣ እንደቀረ ይነግረናል፡፡ ታማኝ

ያልሆነው መጋቢ በዐደራ የተሰጡትን ወገኖች የሚጨቁንና በዙሪያው ባሉ ላይ ግፍ የሚሠራ ሆነ፡፡ ስለዚህ ይህ ሰው ከዚህ በኋላ የመልካም ተግባር ምሳሌ ወይም የጸጋ ሥራ መሪ አይደለም፡፡

ክርስቶስን የግል አዳኛችን አድርገን ስንቀበል የእግዚአብሔርን ሀብት ለመቆጣጠር የተሾምን መጋቢዎች እንሆናለን፡፡ ከዚያ በላይ ግን--ለሰማይ ገጣሚ አድርጎ የሚያዘጋጀውን የክርስትናን ተጨባጭ መንፈሳዊ ህይወት የመምራት ኃላፊነት አለብን፡፡

**ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡ ሉቃ. 12:45፡፡ ክርስቶስ "ዘግይቷል" የሚል ስሜት የምንጋራ አንዳንዶቻችን እንዲህ ባለው ማታለያ እንዳንወድቅ መጠንቀቅ ያለብን ለምንድን ነው?**

## ማክሰኞ ጥር 22

# የምስጢራዊው አምላክ መጋቢዎች

እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ቆለ. **2:2-3፣ 1ጢሞቴ. 3:16፡፡ ጥቅሶቹ "ምስጢር" ብለው ያስቀመጡት ምንድን ነው? "ምስጢር" የሚለው አባባል ይህን ለማስተዋል ያለን ዕውቀት የተገደበ ስለመሆኑ ምን ይነግረና**?

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

ነዕማታዊው ሶፋር ኢዮብን "የእግዚአብሔርን ጥልቅ ምስጢር ልትለካ ትችላለህን?" (ኢዮብ 11:7) ብሎት ነበር፡፡ "ምስጠር" የሚባለው ቃል--እንቆቅልሽ፣ የተሰወረ፣ የማይታወቅ፣ ያልተብራራ ወይም ለመረዳት የማይቻል የሚል ፍቺ አለው፡፡ ምንም እንኳ አምላካዊውን ቃል ሙሉ ለሙሉ መረዳት አሁንም ከአቅማችን በላይ ቢሆንብንም፣ የእግዚአብሔር ምስጢራት ግን በመጽሐፍ ቅዱስ

ሰፍረዋል፡፡ ምስጢር የሆኑትም ለዚህ ነው፡፡ ሁኔታው አጠገባችን ያለውን የቅርብ ሩቅ ማየት ሳንችል--ሰማይ ላይ ያሉትን ጥቃቅን ነገሮች ለማየት ተስፋ እንደማድረግ ነው፡፡ እግዚአብሔር ካልገለጠልን በቀር ያን ያህል አርቀን ማየት አንችልም፡፡

**ለእኛ ስለተገለጠው ነገር ዘዳ. 29፡29 ምን ይላል?**

እኛ ሙሉ ለሙሉ ለማናስተውላቸው ነገሮች መጋቢዎች ነን፡፡ የእኛ የዕውቀት አድማስ በራዕይና በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጠውን ያህል ብቻ ነው፡፡ ከፍ ያለው የመጋቢነት ኃላፊነታችን "እንደ ክርስቶስ አገልጋዮችና እንደ እግዚአብሔር ምስጢር ባለ *ዐ*ደራዎች" (1ቆሮ. 4፡1) መኖር ነው፡፡

እግዚአብሔር እንደ መጋቢነታችን የገለጠልንን መለኮታዊ እውነት ጠብቀን እንድናቆይ፣ እንድናስተምርና እንድንንከባከብ ይፈልጋል፡፡ ይህ የመጨረሻው የመጋቢነት ሥራ ሲሆን ይኸውም "የእምነትንም ጥልቅ ምስጢር በንጹህ ኅሊና መጠበቅ" መቻል ነው (1ጢሞቴ. 3፡9)፡፡

"የክብር ተስፋ" የሆነውን ክርስቶስ መለማመድ መቻላችን ከምስጢር ሁሉ እጅግ የላቀው ምስጢር ነው፡፡ የደኅንነት ዕቅድ ከሰብዓዊው አስተሳሰብ አድማስ እጅግ የገዘፈ እንደመሆኑ ሙሉ ለሙሉ መረዳት አዳጋች ነው፡፡ ሁሉ ነገር በእርሱ የተፈጠረውና ከፍጥረት ሥራ አንዳችም ከእርሱ ውጪ ያልሆነው (ዮሐ. 1፡1-3)፤ ፈጣሪ ራሱ ወደዚህ ምድር ወርዶ "በሥጋ መገለጡ" (Ellen G. White, *Manuscript Releases,* vol. 6, p. 112) እና ራሱን ለሰብዓዊው ዘር ኃጢአት መሥዋዕት አድርጎ መስጠቱ--የያዘው ምስጢር ፍጡራን ሙሉ ለሙሉ ሊያስተውሉ የማይችሉት ዓይነት ነው፡፡ መላእክት ሳይቀሩ የሱስ ወደዚህ ምድር የመጣበትን ምስጢር ለመረዳት ይማራሉ (1ጴጥ. 1፡12)፡፡ ሆኖም እነርሱ የሚያውቁት ነገር እግዚአብሔርን ስለ ክብሩና ስለ በጎነቱ እንድናወድስ ያደርገናል (ራእ. 5፡13)፡፡

**እርስዎ የወንጌል መጋቢ ሆነው ተጠርተዋል፡፡ *ዐ*ደራው የያዛቸው ኃላፊነቶች ሲነሱ ከፊትዎ ድቅን የሚለው ምንድን ነው?**

**ረቡዕ** **ጥር 23**

# የመንፈሳዊው እውነት መጋቢዎች

ስለ መጋቢነት ዐደራ ስናስብ ተጨባጭና ተገቢነት ያላቸው ነገሮች ቶሎ ወደ አእምሮአችን ይመጣሉ፡፡ ነገር ግን አሁን እንደተመለከትነው መጋቢነት ከዚህ ባሻገር ይሄዳል፡፡ ልክ እንደ ተጨባጭ ንብረት ሁሉ የማይታዩ ስጦታዎችም ከእግዚአብሔር ይመጣሉ፡፡ በክርስቶስ የክርስትናን ጸባይ በማጎልበት በእርሱ መሆን የሚገባንን ሕዝቦች እንሆን ዘንድ እግዚአብሔር እነዚህን የማይታዩ መንፈሳዊ ሀብቶች ሰጥቶናል (1ጴጥ. 4፡10)፡፡ ሰለዚህ እነዚህን ስጦታዎች ከተጨባጮቹ ይበልጥ በጥንቃቄ ልንይዝና ልናስተዳድር ይገባል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ስጦታዎች አለቅጥ የላቀ ዋጋ ያላቸው ናቸው፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ኤፌ. 6፡13-17፡፡ መጋቢዎች እንሆን ዘንድ በእግዚአብሔር ምን ተሰጥቶናል? እነዚህን ነገሮች ባግባቡ ማስተዳደርና ጥቅም ላይ ማዋል ወሳኝ የሆነው ለምንድን ነው?**

------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------

“የእግዚአብሔር ስጦታ ግን በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ የዘላለም ሕይወት ነው” (ሮሜ 6፡23)፡፡ ዓለምና ሙላቷ በክርስቶስ ያገኘነውን ቤዛነት ልትሰጠን አትችልም፡፡ ከእግዚአብሔር በነፃ የተበረከተልን የቤዛነት ስጦታ እጅግ የከበረውና ከሁሉ የላቀው ሀብታችን ነው፡፡ ይህን የቤዛነት ተጨባጭ እውነታ ሁሌም ጠብቀን መጓዛችን እንደ አንድ መጋቢ በእግዚአብሔር የተሰጡንን ሌሎች ንብረቶች በአስተማማኝ እንድንጠብቅ ይረዳናል፡፡

“ከተፈጥሮ የሚገኘው ትምህርት ከቀራኒዮ በሚፈነጥቀው ብርሀን ብቻ በትክክል መነበብ ይችላል፡፡ መልካም የሆነው ነገር ክፉውን እንዴት ማሸነፍ እንደሚችል በቤተልሔም ብሎም በመስቀሉ ታሪክ ይፋ ይሁን፡፡ እያንዳንዱ ወደ እኛ

የሚወርደው በረከት የቤዛነት ስጦታ መሆኑ ይታይ፡፡"—Ellen G. White, *Education*, p. 101.

መቤዠታችን እውን ሆኗል ምክንያቱም የሱስ የመጨረሻውን ዋጋ ከፍሏል፡፡ "በእርሱም እንደ እግዚአብሔር ጸጋ ባለጠግነት መጠን፣ በደሙ በተደረገልን ቤዛነት፣ የኃጢአትን ይቅርታ አገኘን" (ኤፌ. 1፡7)፡፡ በጥቅሱ "አገኘን" የሚለው ቃል *ዳንን* የሚል ፍቺ አለው፡፡ የደኅንነት ባለቤት መሆን የቻልነው እግዚአብሔር በስጦታ ስላበረከተልን ነው፡፡ ክፉው እንዳይነጥቀን "የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር ዕቃ" መልበሳችን (ኤፌ. 6፡11) እጅግ ወሳኝና አንገብጋቢ መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡ እርሱ ይህን ለማድረግ የሚያስችለው ብቸኛ መንገድ የእኛ ፈቃደኝነት ሲሆን ይኸውም "የእግዚአብሔር ቃል" (ኤፌ. 6፡17) በግልጽ ያስቀመጠልንን ካልታዘዝን ነው፡፡ ታላቁ ከለላችን የተሰጠንን ብርሃን በእምነት መጠበቃችንና መታዘዛችን ነው፡፡

**ይህን ጥቅስ ደግመው ያንብቡ፦ኤፌ. 6፡13-17፡፡ የእግዚአብሔርን ሙሉ የጦር ዕቃ የምንለብሰው እንዴት ነው? በተሰጠን ሙሉ የጦር ዕቃ መጋቢዎች መሆን የምንችለውስ እንዴት ነው?**

**ሐሙስ** **ጥር 24**

# እንደ መጋቢነት የተቀበልነው ኃላፊነት

ብልህ መጋቢዎች የግብረገብ መርኆዎችን ተቀብለው በሥራ ላይ ለማዋል ባላቸው ፈቃደኝነት ይገለጻሉ፡፡ ኃላፊነትን በግል መቀበል ምርጫ ነው፤ በተግባር የሚገለጽም ድርጊት ነው፡፡ በመንስዔና ውጤት መካከል ያለውን ግንኙነት ለይቶ ይገነዘባል፡፡ ዐደራን በግል ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን ቸል ሊባል የማይችል ቁልፍ ባህሪ መሆኑን የመጋቢነት ፍቺ ያስረዳል፡፡ መጋቢው እግዚአብሔር በልቡ ውስጥ ያስቀመጠውን ነገር በከፍተኛ ፍላጎትና ንቃት የሚጠብቅ መሆን አለበት፡፡ ስለዚህ

እንዲህ ያለው ፈቃደኝነት መጋቢው ከእግዚአብሔር ጋር እንዲኖረው የታለመውን ግንኙነት የሚገልጽ ምርጫ ነው፡፡

“እግዚአብሔር ሰዎችን ከራሱ ጋር ቀጥተኛ ወደ ሆነ ዝምድና ለማምጣት ይመኛል፡፡ ከሰብዓዊው ፍጡር ጋር ባለው ዘርፈ ብዙ ግንኙነት እያንዳንዱ ሰው በግል ዐደራ የመውሰዱን መርኅ ይቀበላል፡፡ ሰዎች ለየግላቸው መወሰን የሚያስችላቸው ነፃነትና ምሪት እንዲያገኙ የእርሱ ምኞት ነው፡፡ እርሱ ስጦታዎቹን ለእያንዳንዱ በግል ሰጥቶአል፡፡ እያንዳንዱ ሰው የተቀደሰው ዐደራ መጋቢ ተደርጎ ተወስዶአል፡፡ የሁሉ ባለቤት የሆነው አምላክ ያስቀመጠውን አቅጣጫ ተከትሎ እያንዳንዱ የመጋቢነት ችሮታ በታማኝነት ወደ እግዚአብሔር ይዘርጋ፡፡” —Ellen G. White, *Testimonies for the Church*, vol. 7, p. 176.

መጋቢዎች ስንሆን ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን ዐደራ ለግለሰብ ወይም ለድርጅት አናውለውም፡፡ የግል ኃላፊነታችንም ሆነ ተጠሪነታችን ለእግዚአብሔር እንደመሆኑ ይኸው ዐደራ በማናቸውም መልኩ በዙሪያችን ካሉ ጋር መስተጋብር ይፈጥራል (ዘፍ. 39፡9፣ ዳን. 3፡16)፡፡ የተሰጠንን ዐደራ በደስታ በመቀበል አቅማችን የፈቀደውን ምርጥ ሥራ እንሠራለን፡፡ በእግዚአብሔር ዐይን የስኬት መሠረቱ እምነታችንና ንጽህናችን እንጂ ዕውቀታችንና ችሎታችን አይደለም፡፡

**ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡--2ቆሮ 5፡10፡፡ ጥቅሱን ከብልሁ መጋቢ ዐውደ ሃሳብ ፍቺ አኳያ እንዴት እናስተውለዋለን?**

-----------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------

የነገረ መለኮት ምሁራንና ፈላስፎች በመምረጥ ነፃነት ዙሪያ ለበርካታ ምዕተ ዓመታት ሲሟገቱ ኖረዋል፡፡ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ዙሪያ ግልጽ አቋም አለው፡ እኛ እንደ ሰብዓዊ ፍጡርነታችን ነፃ ፈቃድ እና ነፃ የመምረጥ ችሎታ አለን፡፡ ይህ ካልሆነ እንደ ሥራችን ለፍርድ እንቀርባለን የሚለው ጽንሰ ሃሳብ

ትርጉሙ ቢስ ይሆናል፡፡ ስለዚህ እንደ እግዚአብሔር ጸጋ ጌታ ለሰጠን ንብረት ታማኝ መጋቢ መሆናችንን ጨምሮ ሁላችንም በየግላችን ትክክለኛውን ምርጫ የማድረግ ኃላፊነት አለብን፡፡

# አርብ ጥር 25

**<u>ተጨማሪ ሃሳብ</u>፡** በብሉይ ኪዳን *"መጋቢ"* በሚል ጥቅም ላይ የዋለውና በጥቂት ቦታዎች ብቻ የተጠቀሰው ይህ ቃል፤ የተተረጎመው ከአንድ ቃል ሳይሆን "የቤቱ አዛዥ" ከሚል ሀረግ ነው፡፡ ለምሳሌ ዘፍ. 43፡19 እንደሚከተለው መተርጎም ይችላል፡ *"ወደ መጋቢው የሴፍ ቀርበው፣ በቤቱ መግቢያ ላይ አነጋገሩት፡፡"* አንድ መጋቢ የመጋቢነት ዐደራ በወሰደበት ቤት ውስጥ የሚኖረው ቤተሰብ--የቤቱ አካል አድርጎ ከተቀበለው ከዚያቤት ይልቅ ለእርሱ የከበረ ዋጋ ያለው ምን ሊሆን ይችላል? ስለዚህ መጋቢው በጣም ውድ ነገር በዐደራ ተሰጠው እንጂ በእጁ እያስተዳደረ ያለው ንብረት አንጡራ ሀብቱ አይደለም፡፡ ይህ ደግሞ መጋቢው ለገዛ ንብረቱ ቢሆን ያደርግ ከነበረው ጥንቃቄ በላይ ኃላፊነት እንዲሰማው ያደርገዋል፡፡

ይኸው ተመሳሳይ ጽንሰ ሀሳብ በአዲስ ኪዳን መቀጠሉን እንመለከታለን፡፡ "አዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳን ጽንሰ ሀሳቦችን ወስዶ ከመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ጽንሰ ሀሳቦችና ቃላቶች ጋር በማገናኘት መጽሐፍ ቅዱስ በመጋቢነት ዙሪያ ያለው አስተምህሮ እንዲበለጽግና እንዲስፋፉ አድርጓል፡፡ ከመጋቢነት ጋር ዝምድና ኖሯቸው ጥቅም ላይ የዋሉት የተለመዱ የግሪክ ቃላት ምንጫቸው--*ኦይኮስ* እና *ኦይኪያ* ሲሆን 'ቤት' የሚል ፍቺ አካተዋል፡፡ *ኦይኮኖምሰ* ደግሞ ቤቱን የሚቆጣጠር፣ መጋቢ ወይም ባለ ዐደራ የሚል ትርጉም ይሰጠናል፡፡ ነገር ግን 'የቤቱ አዛዥ' በሚል የተተረጎመው *ኦይኮኖሚያ* ብዙውን ጊዜ ሰፊ ትርጉም አለው፡፡" — *Handbook of Seventh-day Adventist Theology* (Hagerstown, Md.: Review and Herald Publishing Association, 2000), p. 653.

## የመወያያ ጥያቄዎች:

❶ አዳም ስላደረገው ነገር እግዚአብሔር ሲጠይቀው የተከለከለውን ፍሬ ለመብላቱ ኃላፊነት በመወሰድ ፋንታ ምን አለ? (ዘፍ. 3:12)፡፡ እራስን ከጥፋተኝነት ገሸሽ አድርጎ በሌላው ላይ ማላከክ--ይህ ከኃጢአት በኋላ በተጨባጭ የታየ የቀደመው ሰው ምላሽ እጅግ አስደናቂ ነው፡፡ አዳም ለሠራው ነገር ኃላፊነቱን በግል ለመቀበል ስለነበረው ፈቃደኝነት የሰጠው ምላሽ ምን ይመስላል? ስለ ገዛ ፈቃደኝነታችንስ ምን ሊነግረን ይገባል? ራሳችን ለሠራነው ስህተት ሌሎችን ተጠያቂ የማድረግ ባህሪን ከእኛ ማራቅ መማር የምንችለው እንዴት ነው?

❷ በተጨባጩ ቁሳዊ ሳይሆን ተጨባጭ ባልሆነው መንፈሳዊ መጋቢነት ጽንሰ ሃሳብ ዙሪያ ተወያዩ፡፡ ለመሆኑ ይህ ምን ማለት ነው? እነዚህን ነገሮች "የምናስተዳድረው" እንዴት ነው?

❸ በራእይ 14፡6-12 ስለ ተጠቀሰው የሦስቱ መላእክት መልእክት ያስቡ፡፡ በተሰጠን የመጋቢነት ዐደራ ዙሪያ ምን ዓይነት አስፈላጊ እውነቶች ተገልጸዋል?

❹ ሙሉ ለሙሉ በማናስተውላቸው መንፈሳዊ ነገሮች ላይ መታመንና ማመን መማር ለእኛ አስስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

ስድስተኛ ትምህርት

ከጥር 26 - የካቲት 2

# የመጋቢው ምልክቶች

**ሰንበት ከሰዓት**

**ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ዕብ.** 11:8–12፤ ሮሜ. 4:13፤ 18–21፤ ማቴ. 6:24፤ ዕብ. 9:14፤ 1ዮሐ. 5:2-3፤ ሉቃ. 16:10–12፡፡

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡-**

"እንግዲህ ሰው ሁሉ እኛን እንደ ክርስቶስ አገልጋዮችና እንደ እግዚአብሔር ምስጢር ባለ ዐደራዎች ሊቆጥረን ይገባል፡፡ ባለ ዐደራዎችም ታማኝ ሆነው መገኘት አለባቸው" *(1ቆሮ. 4:1-2)፡፡*

የንግዱ ማኅበረሰብ አካላት በንግድ ምልክቶችና ስያሜዎች እንደሚታወቁ ሁሉ መጋቢዎችም በምልክቶቻቸው ወይም በልዩ መለያዎቻቸው ይታወቃሉ፡፡ እንዲያውም ብዙዎች የገበያ ዕቃዎችን በማስተዋወቅ ዝነኞች እየሆኑ መጥተዋል፡፡

የክርስቲያን መጋቢ መለያ ምልክት ወይም አርማ የክርስቶስ ፍቅር ነጸብራቅ ነው፡፡ ይህ ነጸብራቅ መጋቢው ከሌሎች ጋር ባለው ግንኙነት ጎልቶ ይታያል፡፡ የክርስቶስን ባህሪ ስንለማመድና ስንኖርበት ህይወታችን የክርስትናን ምልክቶች ገልጦ ያሳያል፡፡ የእኛ ምልክት የእርሱ አርማ ነው፡፡ የእኛ ማንነት ከእርሱ የተዋሃደ ነው (1ቆሮ. 6:17)፡፡

በዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን ለእግዚአብሔር መጋቢዎች ልዩ መለያ ያሰጧቸውን ባህሪያት ለይተን እንመለከታለን፡፡ እነዚህ ባህሪያት ወደ የሱስ ዳግም ምጽአት እንድንመለከትና ለአምላካዊው እውነት ታማኝ ሆነን በዐደራ የተሰጠንን የመጋቢነት ሥራ እንድንሠራ ያበረታቱናል፡፡ እያንዳንዱ ባህሪ የጠፋውን ለመፈለግና ለማዳን ከመጣው ጋር ልንመሠርት ስለሚገባው ጥልቅ ግንኙነት ይገልጻል፡፡ እነዚህ ባህሪያት አብልጠው በተጠኑ ቁጥር በሕይወታችን ውስጥ ሥር እየሰደዱ ይሄዳሉ፡፡ ሁሌም ታታሪው የእግዚአብሔር የፍቅር ባህሪ የእኛ ምልክትና አርማ በመሆን ከዛሬ አንስቶ እስከ ዘላለም እያንዳንዱን የሕይወታችንን ክፍል የሚያነሳሳ ይሆናል፡፡

## እሁድ ጥር 27

# እውነተኛና የሚታመን

“ባለ ዐደራዎችም ታማኝ ሆነው መገኘት አለባው” (1ቆሮ. 4፡2)፡፡ ለታማኝ መጋቢ “መልካሙን የእምነት ገድል” (1ጢሞቴ. 6፡12) መዋጋትና ማሸነፍ እጅግ ወሳኝ ነው፡፡ “ታማኝ” እግዚአብሔር ሲሆን፤ በእኛ ውስጥ በሚሠራው በእርሱ የዚህ ባህሪ ባለቤት ማለትም ታማኞች እንሆናለን፡፡ ታማኝ መሆን ማለት ትክክል መሆኑን ለምናውቀው ነገር እውነተኛ ሆኖ መገኘት ነው፡፡ በተለይ በልባችን ውስጥ ለሚካሄደው መንፈሳዊ ውጊያ ታማኝ መሆን ይጠበቅብናል፡፡

ትክክል በሆነውና በተሳሳተው እንዲሁም በበጎውና በክፉው መሃል መንፈሳዊ ግጭቶች መምጣታቸው አይቀሬ ነው፡፡ እነዚህ ግጭቶች የእምነት ውጊያ አካል ናቸው፡፡ መጋቢዎችን በእያንዳንዱ ሁኔታ ከሌሎች የሚለያቸው ታማኝ ለመሆን መምረጣቸው ነው፡፡ እርስዎ ባለሀብት ለመሆን የሚወጥኑ፣ ሀብትንም የሚወዱ ከሆነ፤ ለእግዚአብሔር ያለዎት ታማኝነት በጽናት ለመቀጠሉና አፍቅሮተ ንዋይ ሊያስከትል ስለሚችለው አደጋ ጌታ የተናገረውን ሁሌም በልብዎ መያዝዎን እርግጠኛ ይሁኑ፡፡ ዝነኛ የመሆን ብርቱ መሻት ካለዎት የእግዚአብሔር ቃል ስለ ትህትና ለሰጠው መልእክት ታማኝ ይሁኑ፡፡ የፍትዎት ሃሳብ ወደ አእምሮዎ

እየመጣ እረፍት ከነሳዎት ስለ ቅድስና ለተሰጡት ተስፋዎች ታማኝ ይሁኑ፡፡ ለሥልጣን መሰላል የተለየ ፍላጎት ካለዎት እግዚአብሔር የሁሉም አገልጋይ ስለመሆን ለተናገረው ቃል ታማኝ ይሁኑ፡፡ ታማኝ ለመሆን ወይም ላለመሆን ምርጫው ግማሽ ሰከንድ እንኳ የማይፈጅ--ውጤቱ ግን ዘላለማዊ ነው፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡--ዕብ. 11:8–12፣ 17–19፣ ሮሜ 4:13፣ 18–21፡፡ ጥቅሶቹ ታማኝ ስለመሆን ምን ያስተምሩናል?**

-------------------------------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------

በዕብራውያን ቋንቋ "ታማኝነት"--እምነት የሚጣልበት የሚል ፍቺ አለው፡፡ "አሜን"--ተመሳሳይ መሰረት የሚጋራ የዕብራውያን ቃል ሲሆን "ጠንካራ" ወይም "ጥብቅ" የሚል ፍቺ አለው፡፡ ታማኝነት--ተፈትኖና ተሞክሮ ለእግዚአብሔር ዕቅድ በጽናት መቆምን ያሳያል፡፡

የተሐድሶ አራማጅ የነበረው ማርቲን ሉተር በንጉሠ ነገሥቱ ፊት ለመናገር እየተዘጋጀ "ከእግዚአብሔር ቃል አንብቦ ሲያበቃ ወዳዘጋጃቸው ጽሑፎች መልከት አደረገና መልሱን በሚስማማ መልኩ ለማቅረብ ሞከረ... ሉተር ወደ ቅዱሳን መጻሕፍት ቀረበና... በስሜት ውስጥ ሆኖ ግራ እጁን በቅዱሱ መጽሐፍ ገጾች ላይ እንዳሳረፈ ቀኝ እጁን ወደ ሰማይ ከፍ አድርጎ--ምስክርነቱን በደሙ ለማተም እንኳ ዝግጁነቱን በመግለጽ--ለወንጌል ታማኝ ለመሆንና ያመነበትን እውነት በነፃ ለመመስከር ማለ፡፡" —J. H. Merle d'Aubigné, *History of the Reformation* (New York: The American Tract Society, 1846), vol. 2, book 7, p. 260.

**በራእ. 2፡10 " 'እስከ ሞት ድረስ ታማኝ ሁን' " የሚሉት ቃላት በየቀኑ ከጌታ ጋር ለምናደርገው ጉዞ ፍቺያቸው ምንድን ነው?**

**ሰኞ** **ጥር 28**

# ታማኝነት

**" 'አንድ ሰው ሁለት ጌቶችን ማገልገል አይችልም፤ አንዱን ጠልቶ ሌላውን ይወዳል፤ ወይም አንዱን አክብሮ ሌላውን ይንቃል፡፡ እግዚአብሔርንና ገንዘብን በአንድነት ማገልገል አይቻልም፡፡' " (ማቴ. 6:24)፡፡ በከፍተኛ ደረጃ ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን እንዳለብን አስመልክቶ ጥቅሱ ምን ያስተምረናል?**

-----------------------------------------------------------------------------------------

"ቀናተኛ" (ዘፀ. 34:14) የእግዚአብሔር የስሙ ፍቺ መሆኑን ማወቃችን ለታማኝነት ብርቱ ጥሪ ሊያቀርብልን ይገባል፡፡ ለ "ቀናተኛው" አምላክ ታማኝ መሆን ለፍቅር ታማኝ መሆን ነው፡፡ ታማኝነት--በእምነት ተጋድሎአችን ማንነታችንን እንድንገልጽና ውጊያውን በጽናት እንድንቀጥል ያበረታታናል፡፡

ታማኝ መሆናችን ለእግዚአብሔር አስፈላጊ ነው (1ነገሥ. 8:61)፡፡ ታማኝነት የደንቦች ዝርዝር ሳይሆን የግል እምነታችን፣ እውነታችንና መሰጠታችን ነው፡፡

**ይህን ጥቅስ ያንብቡ ዘዳ 28:9፡፡ ጥቅሱ ስለ ታማኝነት አስፈላጊነት ምን ያስተምረናል?**

-----------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------

ታማኝነት ባለበት ክህደት ሊኖር የሚችልበት አጋጣሚ መኖሩ መዘንጋት የለበትም፡፡ ታማኝነት እንደ ፍቅር ሁሉ ያለ አንዳች ተጽእኖ በነፃነት መበርከት ካልቻለ እውነተኛ መባል አይችልም፡፡ ወታደሮች በጦር ግንባር ከፊተኛው ረድፍ ተሰልፈው ከባላንጣዎቻቸው ጋር በሚፋለሙበት ወቅት እስከ መጨረሻው በጽናት

ከመዋጋት ውጪ ሌላ አማራጭ የላቸውም፡፡ ወደ ኋላ አፈገፍጋለሁ ቢሉ ከጀርባቸው በአዛዦቻቸው ጥይት ሊመቱ ይችላሉ፡፡ ታዲያ እነዚህ ወታደሮች ግዳጃቸውን እየተወጡ ቢሆንም ከታማኝነት የተነሳ ነው ሊባል ግን አይችልም፡፡ እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው ይህ ዓይነቱን ታማኝነት አይደለም፡፡

የኢዮብን ታሪክ ለመቃኘት ብንሞክር--ኢዮብ ቤተሰቡን፣ ንብረቱንና ጤንነቱን ሊያወድም ያለውን አስፈሪ ክስተት አስቀድሞ አልተመለከተም፡፡ ምንም እንኳ የደረሰበት ነገር በእግዚአብሔር ላይ የነበረውን መታመን፣ ፍቅርና ቁርጠኝነት እርግፍ አድርጎ እንዲተው የማድረግ ኃይል ቢኖረውም--ኢዮብ ግን በእግዚአብሔር ላይ የማይናወጥ ግብረገባዊ ምርጫ ነበረው፡፡ ታማኙና እግዚአብሔርን በይፋ ለማመስገን ፍርሃት ያልነበረው ኢዮብ "ቢገድለኝም እንኳ በእርሱ ተስፋ አደርጋለሁ" (ኢዮ. 13፡15) ሲል ዝነኞቹን ቃላት ተናገረ፡፡ ኢዮብ ብርቱ አደጋ እየተጋፈጠ በነበረበት በዚያ ወቅት ያሳየው ታማኝነት እጅግ የረቀቀውንና ውበት የተላበሰውን ታማኝ መጋቢ ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ ሆነ፡፡

***እስቲ ራስዎን እንዲህ ብለው ይጠይቁ፡ ህይወቱን ለእኔ ለሰጠው ጌታ ምን ያህል ታማኝ ነኝ? ያን ታማኝነት በተሻለ መግለጽ የምችለውስ እንዴት ነው?***

## ማክሰኞ ጥር 29

# ንጹህ ኅሊና

አንጡራ ሀብታችን ልናደርጋቸው የምንችላቸው አያሌ የከበሩ ነገሮች አሉ፡፡ ጤና፣ ፍቅር፣ ጓደኛ፣ ቤተሰብ--እነዚህ ሁሉ በረከቶች ናቸው፡፡ ነገር ግን ከእነዚህም በላቀ ከሚያስፈልገው አንዱ ንጹህ ኅሊና ነው፡፡

**እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ዕብ. 10፡19-22፣ 1ጢሞቴ. 4፡1-2፡፡ ሐዋርያው "ክፉ ኅሊና" እና "ኅሊናቸው በጋለ ብረት የተጠበሰ" ሲል ምን ማለቱ ነው?**

-----------------------------------------------------------------------------------------

ኅሊናችን ውጪያዊውን የሕይወታችንን ክፍል የሚቆጣጠር ውስጣዊ መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ኅሊና ራሱን ከፍ ካለውና ፍጹም ከሆነው ከፍታ--ይኸውም ከአምላካዊው ሕግ ጋር ራሱን ማስተሳሰር ይኖርበታል፡፡ እግዚአብሔር ሕጉን በአዳም ልብ ውስጥ ጽፎ የነበረ ቢሆንም ነገር ግን ኃጢአት እርሱን ብቻ ሳይሆን የእርሱን ትውልዶች ጭምር ጋርዶ ነበር፡፡ ስለዚህ ጥቂት የተሸራረፉ ሕጎች ብቻ ቀርተው ነበር፡፡ አሕዛብ "ኅሊናቸው ስለሚመሰክር፣ ሐሳባቸው ስለሚከሳቸው፣ ደግሞም ስለሚከላከልላቸው የሕግ ትእዛዝ በልባቸው የተጻፈ መሆኑን ያሳያሉ፡፡" (ሮሜ. 2፡15)፡፡ የእግዚአብሔር ሕግ በየሱስ ልብ ውስጥ በመኖሩ (መዝ. 40፡8) አዳም ሲወድቅ የሱስ ግን የስኬት ባለቤት ሆነ፡፡

**ለመጥፎው ኅሊና ብቸኛው መፍትሔ ምን እንደሆነ አስመልክቶ ጳውሎስ ምን ይላል? ዕብ. 9፡14፡፡**

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

"ድር ያደራበት የህሊና ጓዳ አገልግሎት ሊሰጥ ይገባል፡፡ ብሩህዎቹ የጽድቅ ጨረሮች ያለ አንዳች መከልከል መፈንጠቅ ይችሉ ዘንድ ወደ ምድር አቅጣጫ የሚከፈቱት የነፍስ መስኮቶች ሊዘጉ--ወደ ሰማይ አቅጣጫ ያሉት ደግሞ ወለል ብለው ሊከፈቱ የግድ ነው፡፡ አእምሮ በመልካምና በክፉ መሃል ያለውን ልዩነት በሚገባ መገንዘብ እንዲችል ንጹህና የጠራ ሊሆን የተገባ ነው፡፡" —Ellen G. White, *Mind, Character, and Personality*, vol. 1, pp. 327, 328. የእግዚአብሔር ሕግ በአማኙ ልብ ሲጻፍና (ዕብ. 8፡10) በእምነት የዳነው አማኝ ሕጉን የመከተል መሻት ሲያድርበት--በውጤቱ ንጹህ ኅሊና ይወለዳል፡፡

**በጥፋተኝነት ስሜት ግብግብ ውስጥ ካለፉ ጉዳዩ ምን ያህል አሰቃቂ እንደሆነና ኅሊናን ያለማቋረጥ ሰላም እንደሚነሳ ያውቃሉ፡፡ ትኩረትዎን በየሱስና ስለ እርስዎ ኃጢአት በሞተበት መስቀሉ ላይ ማድረግዎ ከጥፋተኝነት ርግማን ነፃ ሊያደርግዎ የሚችለው እንዴት ነው?**

**ረቡዕ** ጥር 30

# መታዘዝ

አቤል በመታዘዝ መንፈስ እግዚአብሔር ያዘዘውን የበግ ጠቦት ይዞ በመሠዊያው ፊት ተንበረከከ፡፡ በሌላ በኩል ቃየን በቁጣ፣ ከምድር ፍሬ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ይዞ በሠራው መሠዊያው ፊት ተንበረከከ፡፡ ምንም እንኳ ሁለቱም ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ቢያቀርቡም--ከወንድማማቾቹ መሃል የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የተከተለው አንደኛው ብቻ ነበር፡፡ የታረደው ጠቦት ተቀባይነት ሲያገኝ ከምድር ፍሬ የቀረበው መሥዋዕት ግን ተቃውሞ ገጠመው፡፡ ምንም እንኳ ሁለቱም ወንድማማቾች ስለሚቀርበው መሥዋዕት ትርጉምና መመሪያ ጠንቅቀው ያውቁ የነበረ ቢሆንም ነገር ግን እንደ ጌታ ፈቃድ የታዘዘው አንደኛው ብቻ ነበር (ዘፍ. 4፡1-5)፡፡

"ቃየን በየሱስ ክርስቶስ ደም የሚድንበትንና ወደ ክርስቶስ ያመላክት የነበረውን የመሥዋዕት ምሳሌ በመታዘዝ አምላካዊውን ዕቅድ ለመቀበል የመቃወሙ ውጤት የአቤልን ሞት አስከተለ፡፡ ቃየን ለዓለም የሚፈሰው የየሱስ ደም ምሳሌ እንዳይፈስ ተቃወመ፡፡" —Ellen G. White Comments, *The SDA Bible Commentary*, vol. 6, p. 1109.

ታዛዥነት በአእምሮ ውስጥ ይጀምራል፡፡ መታዘዝ ከፍ ካለው የሥልጣን እርከን የሚወርደውን ትእዛዝ ለመፈጸም ኃላፊነትን በአእምሮ የመቀበል ሂደት ያካትታል፡፡ ታዛዥነት ከአንድ ከፍ ያለ አካል ጋር ዝምድና መኖሩን ተከትሎ የሚመጣና ያን አካል ለመታዘዝ በሚኖር ፈቃደኝነት ላይ የተገነባ ነው፡፡ እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ካለን ዝምድና አኳያ በፈቃደኝነትና በፍቅር ላይ የተመሰረተው መታዘዛችን ግብረገባዊ ባህሪያችንን ይቀርጻል፡፡ እግዚአብሔርን የምንታዘዘው እኛ እንደምናስበውና እንደምንመኘው ብቻ ሳይሆን ልክ እርሱ በሚያዘው መሰረት ሊሆን ይገባል፡፡ የቃየን ሁኔታ እግዚአብሔር የሚጠይቀውን ከመፈጸም ይልቅ የራሱን ነገር እያደረገ ላለው ፍጹም ምሳሌ ነው፡፡

**የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ 1ዮሐ 5:2-3፣ ሮሜ 1:5፣ 10:16-17፡፡ መታዘዝ በሥራ ሳይሆን በእምነት ለዳነው ክርስቲያን ምን ማለት እንደሆነ ጥቅሶቹ ምን ያስተምሩናል?**

----------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------

እግዚአብሔርን የምንታዘዘው ለመዳን አይደለም፡፡ ይልቁንም ስለዳን እንታዘዘዋለን፡፡ መታዘዝ ማመናችንን በተግባር የምንገልጥበት ግብረገባዊ መንገድ ነው፡፡ ሳሙኤል ሳኦልን እንዲህ ብሎት ነበር "ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ ደስ የሚለውን ያህል፣ እግዚአብሔር፣ በሚቃጠል ቁርባንና መሥዋዕት ደስ ይለዋልን? እነሆ መታዘዝ ከመሥዋዕት፣ ማዳመጥም ከአውራ በግ ሥብ ይበልጣል" (1ሳሙ. 15፡22)፡፡

**መታዘዝ ከመሥዋዕት ይበልጣል ሲል ሳሙኤል ምን ማለቱ ነው? እንደ ክርስቲያን በተሳሳተው ርካሽ የጸጋ አስተምህሮ እንዳንወድቅ ይህ ምን ሊነግረን ይችላል?**

## ሐሙስ የካቲት 1

# እምነት የሚጣልበት / የሚጣልባት

**በሉቃ. 16፡10-12 የቀረበው መልእክት ስለ ታማኝነት ምን ያስተምረናል? ይህ ባህሪ ለአንድ ታማኝ መጋቢ በጣም አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?**

----------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------

ይህ የታማኝነት መርኅ በመላው የመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች ይስተዋላል፡፡ ለምሳሌ በአንድ ታሪክ--አራቱ ሌዋውያን የበር ጠባቂ አለቆች የብሉይ ኪዳኑን መቅደስ ክፍሎችና ግምጃ ቤቶች በሌሊት የመጠበቅ ዐደራ ተቀብለው ነበር፡፡ የጥበቃውን ሥራ የሚያከናውኑት እነርሱ በመሆናቸው የሚያድሩትም በዚያው በቤተ መቅደሱ አካባቢ ነበረ፡፡ ቁልፉ በእጃቸው በመሆኑ ጠዋት ላይ ደጆቹን የሚከፍቱት እነርሱ ነበሩ (1ነገሥ. 9፡26-27)፡፡ እነዚህ ሰዎች ኃላፊነት የሚጣልባቸው ሆነው በመገኘታቸው ዐደራው ተሰጥቶአቸው ነበር፡፡

እምነት የሚጣልበት ሰው መሆን የመልካም መጋቢ ጸባይ ነው፡፡ ይህ ማለት ታማኝ መጋቢዎች የእነርሱ ሚና ጥልቅ ጠቀሜታ እንዳለው ጠንቅቀው ይገነዘባሉ፡፡ እግዚአብሔር የሚታመን አምላክ መሆኑን የሚያስተውሉት እነዚህ ወገኖች እነርሱም እርሱን ለመምሰል ያልማሉ፡፡ (ዘዳ. 32፡4፣ ነገሥ፣ 8፡56)፡፡

እምነት የሚጣልበት ሰው መሆን የበሳል ባህሪ ባለቤትነትን ያመላክታል፡፡ ስለዚህ አንድ ግለሰብ ይህን ባህሪ ሲቀዳጅ በተመልካቾች ዐይን ከፍተኛ የጠባይ ብቃት ደረጃ ላይ መድረሱን ያሳያል፡፡ በማናቸውም ዓይነት አስቸጋሪ ሁናቴ ላይ ሊገኙ ቢችሉ እንኳ ለተናገሩት ቃል ታማኝ መሆን የእግዚአብሔርን ጸባይ ማንጸባረቅ ማለት ነው--(2ነገሥ. 12፡15)፡፡

ዳንኤል በሁለቱ የዓለም ልዕለ ኃያላን አገሮች ነገሥታት ፊት እምነት የሚጣልበት ሰው መሆኑ ተመስክሮለት ነበር፡፡ ዳንኤል ያለ አንዳች ፍርሀት ጥበብ እና እውነትን በቀጥታ ለነገሥታት በማቅረብ--በታማኝ የአማካሪነት ህይወቱ ያተረፈው ዝና፤ በሚርተኞችና ጠንቋዮች ጉባዔ ቀጥተኛ ተቃውሞ ይገጥመው ነበር፡፡ ታማኝነት የሥነ ምግባር ዘውድ እንደመሆኑ የአንድን ሰው ግብረገባዊ መርኅዎች ከነንጽህናቸው ፍንትው አድርጎ ያሳያል፡፡ የመጋቢነት ብቃት በአንድ ሌሊት የሚቀዳጁት ሳይሆን--ለትናንሾቹ ነገሮች ታማኝ በመሆን የሚመጣ ነው፡፡

ሰዎች ምን ያህል ታማኝ እንደሆንን ይመለከታሉ፡፡ በቀላሉ በሌሎች ተጽእኖ ስር ወድቀን የማናረግድ፣ ወረት የማያጠቃን ወይም ሸንገላ የማይቃጣን ሆነን ስንገኝ ሰዎች ያከብሩናል፣ ይተማመኑብናል፡፡ እምነት የሚጣልበት ሰው መሆን--

በእያንዳንዱ ምድራዊ ህይወት ለተሸከምነው ኃላፊነት የጸባይ ብቃታችንን ገልጦ ማሳየት እና ሰማይን በተጨባጭ መመስከር ነው፡፡ "ዓለማዊ ጥበብ ያላቸው ሰዎች--የእውነተኛ ባለጠግነት፣ የመልካምነት፣ የምኅረት፣ የርኅራኄና የመልካም ምግባር ባለቤት ሆነው የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች ይሆኑ ዘንድ፤ ታማኝና እምነት የሚጣልባቸው የክርስቶስ መንግሥት ሕዝቦች ሆነን ተጠርተናል፡፡" —Ellen G. White, *Testimonies for the Church*, vol. 6, p. 190.

**በግል ስለሚያውቁት እምነት ሊጣልበት የሚችል ሰው አሰብ ያድርጉ፡፡ እርስዎ ይበልጥ እምነት የሚጣልበት ሰው መሆን ይችሉ ዘንድ ከዚያ ሰው ምን መማር ይችላሉ?**

## **አርብ** የካቲት 2

**ተጨማሪ ሃሳብ፡** ሌላው የመልካም መጋቢነት ምልክት ግለሰባዊ ተጠያቂነት ነው፡፡ "በየሱስ ላይ ሊሆን የተገባውን የሕዝቡን አስተሳሰብ ወደ ሰው በማዞር ግለሰባዊ ተጠያቂነትን ማጥፋት የቀደመው የሰይጣን አሠራር ሆኖ ቆይቷል፡፡ ሰይጣን የእግዚአብሔርን ልጅ በፈተነው ጊዜ ይህ ዓላማው ቢከሽፍበትም፤ ነገር ግን በኃጢአት ወደ ወደቀው ሰብዓዊ ፍጡር ሲመጣ በተሻለ ስኬት ማግኘት ቻለ፡፡ ይህን ተከትሎ ክርስትና በብልሹ አሠራር ተዋጠ፡፡" —Ellen G. White, *Early Writings*, p. 213.

ክርስቶስ የስብዕናችን ማዕከል መሆን ከቻለ ለአምላካዊው ምሪት ክፍት እንሆናለን፡፡ በውጤቱም በእኛ ውስጥ ያለው እምነት፣ ታማኝነት፣ የንጹህ ኅሊና ባለቤትነት፣ እምነት የሚጣልበት ሰው መሆናችንና የግል ተጠያቂነታችን በህይወታችን ይገለጣል፡፡ በመሆኑም እኛ እንደ መጋቢዎች ፍጹም ሆነን በእግዚአብሔር እጆች ተሠርተናል (መዝ. 139፡ 23-24)፡፡

ግለሰባዊ ተጠያቂነት በእጅጉ አስፈላጊ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርኅ ነው፡፡ የሱስ በምድር በነበረበት ጊዜ ግለሰባዊ ተጠያቂነቱ ለአብ ነበር (ዮሐ. 8፡28)፡፡ ከአንደበታችን ለሚወጣው ለእያንዳንዱ ከንቱ ቃል ተጠያቂዎች ነን (ማቴ.

12፡48)፡፡ “ብዙ ዐደራ ከተቀበለም ብዙ ይጠበቅበታል” (ሉቃ. 12፡48)፡፡ የግለሰባዊ ተጠያቂነት ትልቁ ሥጋት የግል ኃላፊነቶቻችንን ወደ ሌላው የማስተላለፍ ዝንባሌአችን ነው፡፡ “በእጃችን ያለው መዋዕለ ንዋይ የግላችን ሳይሆን በአደራ የተሰጠን መሆኑን ልብ እንበል፡፡ እንዲያማ ባይሆን በራሳችን ውሳኔ የመስጠት ኃይል እንዳለን በማወጅ--ኃላፊነታችንን ወደ ሌሎች ገሸሽ እያደረግን መጋቢነታችንን ለእነርሱ በተውነው ነበር፡፡ ነገር ግን ይህ ሊሆን አይችልም ምክንያቱም ጌታ እያንዳንዳችንን በግል መጋቢዎቹ አድርጎ ፈጥሮናል፡፡” —Ellen G. White, *Testimonies for the Church*, vol. 7, p. 177.

## *መወያያ ጥያቄዎች:*

❶ ***በዚህ ሳምንት ያጠናናቸውን የመጋቢነት ምልክት የሆኑትን፡ ግለሰባዊ ተጠያቂነት፣ እምነት የሚጣልበት መሆን፣ ታዛዥነት፣ ታማኝነት እና ንጹህ ኅሊና ቃኘት ያድርጉ፡፡ ፡፡ ምልክቶቹ እርስ በርስ ያላቸው ዝምድና ምን ይመስላል? በአንዱ አካባቢ ሊኖር የሚችል መሳሳት በሌሎቹም ላይ ተጽእኖ ማምጣት የሚችለው እንዴት ነው? ወይም በአንዱ ላይ የሚኖረን ጥብቅነት በሌሎቹም ላይ ተመሳሳይ አቅም እንድንፈጥር የሚያስችለን እንዴት ነው?***

❷ ***የወንጌል ተስፋ ከጥፋተኝነት ስሜት ጋር እየታገሉ ያሉ ወገኖችን እንዴት ሊረዳ እንደሚችል ጠለቅ አድርጋችሁ ለመመልከት ሞክሩ፡፡ ምን ዓይነት ተስፋዎችን በየግል የመጠየቅ መብት ተሰጥቶአቸዋል?***

❸ ***ብዙውን ጊዜ “ታማኝነት” የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ በራሳችን እንደ መልካም ነገር እናየዋለን፡፡ ነገሩ ሁሌም እንደዚያ ነው? መልካም ላልሆነ ሰው ወይም ሁኔታ ታማኝ መሆን የሚቻለው እንዴት ነው? የ “ታማኝነት” ጽንሰ ሃሳብ ሁሌም ከዋለበት ዐውድ አኳያ ማለትም በመልካም ወይም በተሳሳተ--በየትኛው ውሎ እንደሆን ሊስተዋል የሚገባው ለምንድን ነው?***

# ሰባተኛ ትምህርት

ከየካቲት 3 - 9

# ከእግዚአብሔር ጋር በታማኝነት መመላለስ

**ሰንበት ከሰዓት**

***ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡*** ሉቃ. 16፡10፤ ሌዋ. 27፡30፤ ዘፍ. 22፡1–12፤ ዕብ. 12፡2፤ ሉቃ. 11፡42፤ ዕብ. 7፡2–10፤ ነኅ. 13፡፡

**የመታሰቢያ ጥቅስ፡-**

*“ ‘በመልካም መሬት ላይ የወደቀውም ቃሉን ቅንና በጎ በሆነ ልብ ሰምተው የሚጠብቁ፣ ታግሠውም በመጽናት ፍሬ የሚያፈሩ ናቸው፡፡ ’ ” (ሉቃ. 8፡15)፡፡*

***ለመሆኑ ቅንና በጎ ልብ ስንል ምን ማለታችን ነው? እንዴትስ ይገለጣል?***

*ዘመናዊው ባህል ብዙውን ጊዜ ሐቀኝነትን እንደው በደምሳሳው በአንጻራዊ የግበረገብ ሕግነት ብቻ ይመለከተዋል፡፡ አብዛኛው ሰው አልፎ አልፎ ታማኝነት ቢጎድለውም ነገር ግን ጥሰቱ የበዛ እስካልሆነ ድረስ ተቀባይነት እንዳለው ተደርጎ ይታመናል፡፡ በተጨማሪ የታማኝነትን መጓደል ያሳያሉ ተብለው የተቀመጡ ልዩ ልዩ ሁናቴዎች አሉ፡፡*

እውነትና ታማኝነት ሁሌም አይነጣጠሉም፡፡ በእርግጥ እኛ ታማኞች እንድንሆን በሚያስችለን ዝንባሌ አልተወለድንም፡፡ ሐቀኝነት እያደር የምናስተውለው ግብረገባዊ ምግባርና የአንድ መጋቢ ሥነ ምግባር እምቡጥ ባህሪ ነው፡፡

ታማኝነትን ስንለማመድ መልካም ነገሮች ከውስጣችን መውጣት ይጀምራሉ፡፡ ለምሳሌ ሐሰት ስንናገር ቢነቃብንስ? በሚል ወይም ያንን ለመሸፋፈን በሚደረግ ሥጋት ውስጣችን አይጨናነቅም፡፡ በዚህና በሌሎች ተጨማሪ ምክንያቶች የተነሳ ሐቀኝነት የከበረ ዋጋ የተላበሰ ግላዊ ባህሪ ነው--በተለይ በአስቸጋሪ ሁናቴዎች ውስጥ ወድቀን ፈተና በቀላሉ ወደ ታማኝነታችን የሚያመራ ሲመስል፡፡

በዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን አሥራትን መመለስ በመለማመድ የታማኝነትን መንፈሳዊ ጽንሰ-ሃሳብ እንመለከታለን፡፡ በተጨማሪ አሥራት ለመጋቢው ብሎም ለመጋቢነት ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡

## **እሁድ** የካቲት 4

# በትንሽ ነገር ታማኝ የመሆን ጉዳይ

ታማኝነትን ማጉደል--አብዛኞቻችን በጋራ የማንወደው ነገር ነው፡፡ በተለይ በሌሎች ተገልጦ መመልከቱን አንወደውም፡፡ በእርግጥ በራሳችን ደርሶ መመልከቱ ቀላል ባይሆንም--ከሆነ ግን--ምክንያት ደርድረን የተሠራውን ስህተት ማቃለልና ነገሩ የሚያስከትለውን ጉዳት ዝቅ አድርጎ ማቅረብ ይቀናናል፡፡ *ይሄ እንኳ ያን ያህል የከፋ አይደለም . . . ምን አለው በጣም ትንሽ ነገር አይደል እንዴ?...* ምንም እንኳ ብዙ ጊዜ ራሳችንን ብናታልልም እግዚአብሔርን ግን ፈጽሞ ማሞኘት አንችልም፡፡

“ታማኝ አለመሆን በሁሉም ደረጃ እየተስተዋለ ያለ ልምድ መሆኑ እውነትን አምኜ ተቀብያለሁ ያለው ወገን በለብታ ውስጥ ለመመላለሱ ምክንያት ሆኗል፡፡ ከክርስቶስ ጋር ትስስር ሳይፈጥሩ የገዛ ነፍሳቸውን በከንቱ ይሸነግላሉ፡፡” —Ellen G. White, *Testimonies for the Church*, vol. 4, p. 310.

**“በትንሽ ነገር” እንኳ ታማኝ መሆን ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ አስመልክቶ የሱስ በሉቃ. 16፡10 የሚገልጸው መርኅ ምን ያህል ወሳኝ ነው?**

---------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------

ይሁን እንጂ በተለይ ባፈራነው ሀብት ዙሪያ እንዴት በቀላሉ ታማኝነታችንን ማጉደል እንደምንችል እግዚአብሔር ያውቃል፡፡ በዚህ ምክንያት ቢያንስ ከሐብት ንብረታችን ጋር በተያያዘ ለምናሳድለው ታማኝነትና ለራስ ወዳድነት ብርቱ ማርከሻ ሰጥቶናል፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዘሌዋ. 27፡30፣ ሚልክ. 3፡8፡፡ እነዚህ ጥቅሶች ምን ሊያስተምሩን ይችላሉ? ይህ የሚናገሩለት ነገር ታማኝ እንድንሆን ምን ያህል ሊረዳን ይችላል?**

---------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------

“ለምስጋና ወይም ለለጋስነት ምንም ዓይነት ተማጽኖ ሊቀርብ አይገባም፡፡ ምክንያቱም ጉዳዩ ሌላ ሳይሆን ከታማኝነት ጋር ብቻ የተቆራኘ ነው፡፡ አሥራት የጌታ እንደመሆኑ የራሱ የሆነውን እንድንመልስ ይናገረናል. . . ታማኝነት የንግዱ ዓለም ወሳኝ መርኅ ነው ከተባለ ለእግዚአብሔር ላለብን ግዴታ ዕውቅና መቸር የለብንምን?

***አሥራት መመለስዎ እርስዎ ያለዎት ሁሉ የማን መሆኑን እንዲያስታውሱ እንዴት ይረዳዎታል? አለን የምንለው ነገር የማን መሆኑን ፈጽሞ መዘንጋት የሌለብን ለምንድን ነው?***

**ሰኞ** **የካቲት 5**

# የእምነት ሕይወት

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዘፍ. 22፡1-12፡፡ ታሪኩ ስለ አብርሃም እምነት ተጨባጭ እውነታ ምን ይነግረናል?**

---------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------

የእምነት ሕይወት የአንድ ጊዜ ክስተት አይደለም፡፡ እምነት በእርግጠኝነት በጸጋው የምንኖርና በክርስቶስ ደም የተሸፈን ታማኝ ክርስቲያን መሆናችንን በአንድ ወቅት ብቻ በብርቱ ገልጸን የምናልፈው ጉዳይ አይደለም፡፡

ለአብነት ያህል የእምነቱ ዓለም ከሺዎች ዓመታት አስቀድሞ አብርሃም ይስሐቅን ይዞ በሞሪያ ተራራ ካሳየው እምነት ጋር ዛሬም እንደተደመመ ይገኛል (ዘፍ. 22)፡፡ ሆኖም እንደዚያ ዓይነቱ እምነት አብርሃም በምትሃት የሚያገኘው ክስተት አልነበረም፡፡ አብርሃም ያን ለማድረግ ያስቻለው ቁልፍ ነገር በእርሱ ዘንድ አስቀድሞ የነበረው የታማኝነትና የመታዘዝ ህይወት ነበር፡፡ አብርሃም ቀደም ባለው ሕይወቱ ታማኝነት የጎደለው ሰው ቢሆን ኖሮ ያን የቀረበለትን ፈተና ማለፍ በተሳነው ነበር፡፡ በእንደዚያ ዓይነት እምነት ያለፈ ሰው ይህ ዓይነቱን አጋጣሚ ተከትሎ እምነቱን መግለጽ መቻሉ እምብዛም አያጠያይቅም፡፡

ዋናው ነጥብ ያለው የመጋቢው ህይወት በአንድ ጊዜ ተግባር ቦግ ብሎ የሚጠፋ አለመሆኑ ላይ ነው፡፡ አማኙ እምነቱን የሚለማመድበትን አካሄድ ተከትሎ--በጊዜ ሂደት እያደገ፣ ሥር እየሰደደና እየተጠናከረ ይሄዳል ወይም ጥልቀት የጎደለውና ልፍስፍስ ይሆናል፡፡

**ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡ ዕብ. 12፡2፡፡ መልእክቱ ስለ እምነታችን ምንጭ እና እምነታችን እንዴት ሊጎለብት እንደሚገባ ምን ይነግረናል?**

------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------

እንደ ታማኝ መጋቢነታችን ብቸኛው ረዳታችን “የእምነታችን ጀማሪና ፍጹም አድራጊ የሆነውን ኢየሱስን እንመልከት፤ እርሱ በፊቱ ስላለው ደስታ መስቀሉን ታግሦ፣ የመስቀሉንም ውርደት ንቆ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአል” (ዕብ. 12፡2)፡፡ በጥቅሱ “ፍጹም አድራጊ” (አዲሱ መደበኛ ትርጉም) በሚል ጥቅም ላይ የዋለው ቃል “ፈጻሚ” (1962 ትርጉም) ተብሎም ተተርጉሟል፡፡ ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ይህን ፍቺ ይዞ የቀረበው እዚህ ቦታ ላይ ብቻ ሲሆን፤ በተጨማሪ “ፍጹም አድራጊ” የሚል ትርጉም አለው፡፡ አባባሉ የሱስ እምነታችንን ወደ ብስለትና ሙላት የማምጣት ፍላጎት አለው የሚል አንደምታ አለው (ዕብ. 6፡1-2)፡፡ በመሆኑም የእምነት ሕይወት ሁሌም የሚያድግ፣ የሚበስልና እየተስፋፋ የሚሄድ በኃይል የተሞላ ተሞክሮ ነው፡፡

**እምነትዎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና እየበሰለ መሄዱን ያዩባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው?**

**ማክሰኞ** **የካቲት 6**

# የእምነት መገለጫ መንገድ

በትናንቱ ጥናታችን እንደተመለከትነው እምነት የማያቋርጥ ሂደት ሲሆን ዘወትር እያደገና በሳል እየሆነ የሚሄድ ተሞክሮ ነው፡፡ እግዚአብሔር እምነታችንን ወደ ፍጹምነት ወይም ወደ ሙላት ከሚያመጣባቸው መንገዶች አንዱ አሥራት ነው፡፡ አሥራትን ወደ እግዚአብሔር መመለስ ሕግን ጠብቆ ለመዳን የሚደረግ አካሄድ አለመሆኑ በትክክል ሊስተዋል ይገባል፡፡ አሥራት ስንመልስ በራሳችን መንገድ ወደ

ሰማይ ለመሄድ እየተመኘን ወይም እየሠራን አይደለም፡፡ ይልቁንም አሥራት የእምነታችን መገለጫ መንገድ ነው፡፡ ግላዊውን እምነታችንን በተጨባጭና በሚታይ ውጪያዊ አኳኋን የምንገልጽበት መንገድ ነው፡፡

ደግሞም ማንም ሰው እምነት እንዳለው፣ በእግዚአብሔር እንደሚያምንና የሱስንም እንደሚቀበል ሊናገር ይችላል፡፡ እንደምናውቀው "አጋንንትም ይህንኑ ያምናሉ" (ያዕ. 2፡19)፡፡ ነገር ግን ከገቢዎ ላይ 10 በመቶውን አንስተው ወደ እግዚአብሔር መመለስ? *ይህ የእምነት ተግባር ነው፡፡*

**ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡ ሉቃ. 11፡42፡፡ *አሥራታችንን ሳንመልስ መቅረት እንደሌለብን* አስመልክቶ የየሱስ ንግግር አንደምታ ምን ይመስላል? *አሥራት* ክብደት ካላቸው የሕጉ ጉዳዮች ጋር እንዴት ይዛመዳል?**

-----------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------

አሥራት በእግዚአብሔር የምንመካ መሆናችንን እና በየሱስ ቤዛችን መታመናችንን በትህትና የምንገልጽበት መንገድ ነው፡፡ እግዚአብሔር "በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ በክርስቶስ የባረከን" (ኤፌ. 1፡3) እና የላቀ ተስፋ የሰጠን ለመሆኑ እውቅና የምንቸርበት መንገድ ነው፡፡

በዘፍ. 28፡14-22 እንደምናነበው እግዚአብሔር ለያዕቆብ ለሰጠው የተስፋ ቃል ምላሹ ምን ነበር?

-----------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------

"ያልተወሳሰበውና በእኩልነት ላይ የተመሰረተው እግዚአብሔር በአሥራት ዙሪያ የዘረጋው እቅድ እጅግ ውብ ነው፡፡ ሁሉም ሰው ይህን ቀደም ብሎ በመለኮት

የተጠነሰሰ ዕቅድ በእምነትና በጀግንነት አጥብቆ እንዲይዝ ይጠየቃል፡፡ በአሥራት ዕቅድ ውስጥ ቀናነትና ጠቃሚነት በአንድ በመጣመራቸው ኃሳቡን አስተውሎ ወደ ትግበራው ለማምራት ጥልቀት ያለው አስተምህሮ አይጠይቅም፡፡ ወንዶች፣ ሴቶችም ሆኑ ወጣቶች የጌታ ግምጃ ቤት ኃላፊዎችና የግምጃ ቤቱን ጥያቄ የሚያሟሉ ወኪሎች መሆን ይችላሉ፡፡" —Ellen G. White, *Counsels on Stewardship*, p. 73.

**አሥራት በመመለስ የሚመጡ እውነተኛ መንፈሳዊ በረከቶችን በግልዎ ያስተዋሉት እንዴት ነው? አሥራት መመለስዎ እምነትዎ እንዲያድግ ያደረገው አስተዋጽኦ ምን ይመስላል?**

**ረቡዕ** የካቲት 7

# በአሥራት መታመን--ለጌታ መቀደስ

**ዘወትር አሥራት ስለ መስጠት እናወራለን፡፡ ነገር ግን አስቀድሞውኑ የእርሱ የሆነውን ነገር ለእግዚአብሔር የምንሰጠው እንዴት ነው?**

**ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡ ዘሌዋ. 27፡30፡፡ ከአሥራት ጋር በተያያዘ በመልእክቱ የምናገኛቸው ሁለት ዋና ዋና ነጥቦች ምንድን ናቸው?**

------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------

"አሥራት የጌታ በመሆኑ ቅዱስ ነው፡፡ ቅድስናው በስለት ወይም በመለየቱ ሳይሆን በራሱ ልዩ ባህሪ ይኸውም የጌታ በመሆኑ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር በቀር ማንም ሰው በአሥራት ላይ ሥልጣን የለውም፡፡ ማንም ቢሆን አሥራትን ለጌታ መቀደስ አይችልም፤ ምክንያቱም አሥራት የየትኛውም ሰው ንብረት አካል አይደለም፡፡" —Ángel Manuel Rodríguez, *Stewardship Roots* (Silver Spring, Md.: Stewardship Ministries Department, 1994), p. 52.

አሥራትን የተቀደሰ ማድረግ አንችልም፡፡ እግዚአብሔር ግን በሥልጣኑ ያደርገዋል፡፡ እርሱ ያን የማድረግ መብት አለው፡፡ እኛ እንደ መጋቢነታችን የእርሱ

የሆነውን ለእርሱ እንመልሳለን፡፡ አሥራት የተለየ ተግባር ላለው የእግዚአብሔር ሥራ የሚውል ነው፡፡ አሥራትን ከዚህ ውጪ በሌላ ማንኛውም ነገር ለማዋል መያዝ ታማኝነትን ማጉደል ይሆናል፡፡ ቅዱስ የሆነውን አሥራት የመመለስ ኪዳን ፈጽሞ ሊበጠስ አይገባም፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዕብ. 7፡2-10፡፡ አብርሃም ለመልከጼዴቅ አሥራት ማውጣቱን አስመልክቶ ጳውሎስ ያነሳቸው ነጥቦች በአሥራት ዙሪያ ያለውን ጥልቅ አንደምታ እንዴት ይገልጻሉ? አብርሃም በእርግጥ አሥራት ያወጣው ለማን ነበር?**

--------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------

ስለዚህ ሰንበት ቅዱስ እንደሆነ ሁሉ አሥራትም ቅዱስ ነው፡፡ “ቅዱስ” የሚለው ቃል “ለመንፈሳዊ አገልግሎት የተለየ” የሚል ፍቺ አለው፡፡ ሰንበትና አሥራት በዚህ መልኩ የተሳሰሩ ናቸው፡፡ ሰባተኛውን ቀን ሰንበት ከሌሎቹ የሳምንቱ ቀናት የተቀደሰ አድርገን እንደምንለየው ሁሉ፤ ቅዱስ የሆነውን አሥራትንም እንደ ተቀደሰ የእግዚአብሔር ንብረት እንለየዋለን፡፡

“እግዚአብሔር ሰባተኛውን ቀን ቀደሰው፡፡ ያ ኃይማኖታዊ አምልኮ ይደረግበት ዘንድ በራሱ በእግዚአብሔር የተለየው፤ የተወሰነ የጊዜ ክፍል መጀመሪያ በፈጣሪያችን ያገኘው ቅድስና እነሆ ዛሬ ድረስ ጸንቶአል፡፡

“በተመሳሳይ የገቢያችን አንድ አሥረኛው አሥራት ‘ለጌታ ቅዱስ ነው፡፡’ አዲስ ኪዳን እንደ ሰንበት ሁሉ በአሥራት ዙሪያ ያጸደቀው ሌላ ሕግ የለም፡፡ የሁለቱም ተገቢነት ጥቅም ላይ ውሏል--የያዙት ጥልቅ መንፈሳዊ ይዘትም ተብራርቷል. . . እኛ እንደ ሕዝብ እግዚአብሔር ለራሱ የመደበውን ጊዜ በታማኝነት ለእርሱ ለማዋል እንደምንተጋ ሁሉ፤ ለእኔ የተገባ ነው የሚለንን መጠን አንመልስለትምን?” —Ellen G. White, *Counsels on Stewardship*, p. 66.

**አሥራትዎ በእርግጥ “ቅዱስ” የመሆኑን ግንዛቤ በልብዎና በአእምሮዎ ህያው አድርገው እንደጠበቁ ለመጓዝ ይረዳዎ ዘንድ ምን ማድረግ ይችላሉ?**

**ሐሙስ** **የካቲት 8**

# መነቃቃት፣ ተሐድሶ እና እሥራት

ረጅም ዓመታት ያስቆጠረው የሕዝቅያስ የንግሥና ዘመን የይሁዳ ነገድ ከፍ ያለ ደረጃ ላይ የደረሰበት ጊዜ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ከንጉሥ ዳዊት እና ሰሎሞን አንስቶ እስከዚያ ዘመን ድረስ እስራኤላውያን በከፍተኛ መጠን የእግዚአብሔርን በረከት አላገኙም ነበር፡፡ በ2ኛ ዜና 29-31 የሕዝቅያስ መነቃቃትና ተሐድሶ እንዲህ ሰፍሮአል፡ "እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ቅን ነገር አደረገ" (2ዜና 29፡2)፡፡ "የእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት እንደገና ተደራጀ" (2ዜና 29፡2)፡፡ ፋሲካም መጠበቅ ጀመረ (2ዜና 30፡5)፡፡ "በኢየሩሳሌም እንዲህ ያለ በዓል ተደርጎ" አያውቅም (2ኛ ዜና 30፡26)፡፡ የአረማውያን ምስሎች፣ መሠዊያዎችና ኮረብታማ መስገጃዎች እንዲወድሙ ተደረገ (2ኛ ዜና 31፡1)፡፡ በህዝቡ ልብ ድንገተኛ መነቃቃትና ተሐድሶ መፈጠሩ የተትረፈረፈ አሥራትና ስጦታ ይዘው እንዲቀርቡ መንስዔ ሆነ (2ኛ ዜና 31፡4-5፣ 12)፡፡

**መጽሐፈ ነህምያ ስለ መነቃቃት፣ ተሐድሶና አሥራት ሌላ ምሳሌ ይሰጠናል፡፡ ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡ ነህ. 9፡2-3፡፡ በወቅቱ የተስተዋለው የልብ መነቃቃት ትርጉም ምን ነበር?--ነህ. 13፡፡ ነህምያ "በእግዚአብሔር ቤት" ተሐድሶ ካመጣ በኋላ (ነህ. 13፡14) የይሁዳ ሕዝቦች ምን ይዘው ቀረቡ? (ነህ. 13፡12)፡፡**

---

"መነቃቃትና ተሐድሶ ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ ለመንፈሳዊው ህይወት መታደስ አጽንኦት የሚሰጠው መነቃቃት በአእምሮና ልብ ውስጥ ታምቆ የተቀመጠውን ኃይል በመቀስቀስ ለመንፈሳዊው ሞት ትንሳዔ ያመጣል፡፡ ተሐድሶ--እንደገና ማደራጀት፣ የጽንሰ ሃሳብ፣ የንድፈ ሃሳብ፣ የልማድና የተግባር ለውጥ ማድረግን ያመላክታል፡፡" —Ellen G. White, *Christian Service*, p. 42.

በመነቃቃት፣ በተሐድሶ እና በአሥራት መካከል ያለው ግንኙነት እርስ በርሱ የተሳሰረ ነው፡፡ አሥራት መመለስን ያላካተተ መነቃቃትና ተሐድሶ--መነቃቃት

ከተባለ፤ በለብታ ከመመላለስ ውጪ ሌላ ፍቺ የለውም፡፡ ብዙውን ጊዜ እኛ ክርስቲያኖች የጌታን ሥራ በንቃት መካፈል ሲገባን እንዲያው በከንቱ ጥግ ጥጉን ይዘን ስንቆዝም እንስተዋላለን፡፡ መነቃቃትና ተሐድሶ ቁርጠኝነት እንደሚጠይቅ ሁሉ አሥራትም የዚህ ተመሳሳይ ቁርጠኝነት አካል ነው፡፡ እግዚአብሔር እንድንመልስ የሚጠይቀንን ለራሳችን እያስቀረን ይህን አድርግልኝ ብለን መለመናችን--ወርቅ ላበደረ ጠጠር፣ እህል ላበደረ ዐፈር--አይሆንብንም?

ልዩነት የሚያመጣው ድርጊት ሳይሆን ተነሳሽነትንና ቁርጠኝነትን ገላጩ የአእምሮና የውስጣዊ ስሜት ውሳኔ ነው፡፡ ይህን ተከትሎ የሚመጡት ውጤቶች፡ የእምነት መጨመር፣ የሰላ መንፈሳዊ ዕይታና መታደስ ያገኘ ታማኝነት ይሆናሉ፡፡

## አርብ የካቲት 9

**<u>ተጨማሪ ሃሳብ</u>፡** በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱትን ኪዳኖች ሁሉ የወጠነው እግዚአብሔር ሕዝቦቹን ወደነዚህ ኪዳኖች በመምራቱ ረገድ ቀዳሚነቱን ወስዷል (ዕብ. 8፡10)፡፡ የኪዳኑ ተስፋዎች የእርሱን ጸጋ፣ ፍቅር እና እኛን ለማዳን ያለውን ምኞት ያንጸባርቃሉ፡፡

ብዙ ነገሮችን የሚያካትተው ከእግዚአብሔር ጋር የሚገባው ኪዳን እንደሚከተለው ቀርቧል፡ ራሱን እግዚአብሔርን፣ ኪዳን ተቀባዩን፣ የኪዳኑን ሁኔታዎች፣ ሁለቱም አካሎች ለሁኔታዎች ያሏቸው ቁርጠኝነት፣ ኪዳኑን ያፈረሰ አካል የሚጣልበት የቅጣት ዓይነት እንዲሁም ኪዳኑ ያስገኛል ተብለው የሚጠበቁ ውጤቶች ናቸው፡፡ በሚልክ. 3፡9-10 የቀረበው የአሥራት ጽንሰ ሃሳብ እነዚህን ክፍሎች ያንጸባርቃል፡፡ ጥቅሱ በእግዚአብሔርና በመጋቢዎቹ መሃል ያለውን በዓይነቱ የተለየ የአሥራት ኪዳን ያጠናክራል፡፡ የእንዲህ ዓይነቱ ኪዳን አካል ስንሆን ብልጭልጩን የፍጆታ ወጪ መርኅ እንቃወማለን፡፡ በተለወጠው ኃጢአተኛ ልብ አንዳች በጎ ነገር ሊመጣ ይችላል ብለን ማመናችንንም እንመሰክራለን፡፡

"ለራስ ወዳድነት ቅርብ የሆነው መንፈስ ሰዎች የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር እንዳይመልሱ የማገድ ባህሪ አለው፡፡ ሕዝቦቹ ለክርስቶስ መንግሥት መፋጠን ቁልፍ ሚና የሚጫወተውንና በእርሱ የተወሰነውን አሥራት በቋሚነት ወደ ቤቱ

የሚመልሱ ከሆነ ማስቀመጫ ቦታ እስኪያጡ ጌታ እንደሚባርካቸው በመንገር ከእነርሱ ጋር የተለየ ኪዳን ገብቷል፡፡ ነገር ግን ሰዎች የእግዚአብሔር የሆነውን ለራሳቸው የሚያስቀሩ ከሆነ ጌታ 'የተረገማችሁ ናችሁ' ሲል በግልጽ ይናገራል' " —Ellen G. White, *Counsels on Stewardship*, p. 77.

ከእግዚአብሔር ጋር በኪዳን ተሳስሮ መኖር የራሱ ኃላፊነቶች አሉት፡፡ ከእርሱ ጋር በገባነው ውል ደስተኞች ብንሆንም ነገር ግን ትእዛዞቹንና ኃላፊነቶቹን እምብዛም ስንወዳቸው አንስተዋልም፡፡ በዐውደ ጽሑፉ መሰረት ኪዳን የሁለት ወገን ስምምነት ሲሆን፤ አሥራት ደግሞ ለቃል ኪዳኑ ከምንገዛባቸው ደንቦች መሃል አንደኛው ክፍል ነው፡፡

## መወያያ ጥያቄዎች፡

**❶ የእኛ ድርሻ የሆነው አሥራት የመመለስ ኃላፊነት ወሳኝ የእምነታችን መገለጫ የሆነው ለምንድን ነው?**

**❷ "አሥራት የመመለስ አቅሙ የለኝም" ለሚል ሰው ምን ዓይነት ቃል ያጋራሉ? ራሱን በዚያ ሁኔታ ውስጥ የሚያየውን ሰው ሊረዱ የሚችሉት እንዴት ነው? ደግሞም ከቃላት ባለፈ እንደዚያ ዓይነቱን ሰው ለመርዳት ምን ተጨማሪ ነገር ሊደረግ ይገባል?**

**❸ በረቡዕ ትምህርት የመጨረሻ ጥያቄ ላይ--አሥራትዎ በእርግጥ "ቅዱስ" የመሆኑን ግንዛቤ በልብዎና በአእምሮዎ ህያው አድርገው እንደጠበቁ ለመጓዝ ይረዳዎ ዘንድ ምን ማድረግ ይችላሉ? የሚል ጥያቄ ቀርቦ ነበር፡፡ ከቀረቡት ምላሾች መሃል አንዳንዶቹ ምን ነበሩ? አሥራት ቅዱስ የመሆኑ ሐቅ ወደ እግዚአብሔር ቤት ለመመለስ ያለው ዝምድና ምንድን ነው?**

# ስምንተኛ ትምህርት

ከየካቲት 10 – 16

# የአሥራት ተጽእኖ

**ሰንበት ከሰዓት**

**ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡** ማር. 16:15፣ 1ጴጥ. 3:8-9፣ 1ቆሮ. 9:14፣ ሮሜ 3:19–24፡፡

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡-**

“በቤተ መቅደስ የሚያገለግሉ ምግባቸውን ከቤተ መቅደስ እንደሚያገኙ፣ በመሠዊያውም የሚያገለግሉ ከመሥዋዕቱ እንደሚካፈሉ አታውቁምን? እንደዚሁም ወንጌልን የሚሰብኩ ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ከወንጌል እንዲቀበሉ ጌታ አዞአል” *(1ቆሮ. 9፡13-14)፡፡*

አሥራት እጅግ አስፈላጊ የእምነታችን መገለጫ መንገድ መሆኑን ባለፈው ሳምንት ጥናታችን ተመልክተናል፡፡ አሥራት እምነታችንን በተጨባጭ የምንገልጥበት ወይም የምንፈትንበት አንዱ መንገድ ነው፡ “በእምነት መሆናችሁን ራሳችሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ፡፡ ከፈር የወጣችሁ ካልሆነ በስተቀር፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በውስጣችሁ እንዳለ አታውቁምን? (2ቆሮ. 13፡5)፡፡

ስለ አሥራት የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻ አብርሃም ለመልከጼዴቅ የሰጠው ነው (ዘፍ. 14፡18-21፣ ዕብ፣ 7፡4)፡፡ በተጨማሪ ሌዋውያን በቤተ መቅደስ ለሚሰጡት አገልግሎት አሥራት ያወጡ ነበር (2ዜና 31፡4-10)፡፡ ዛሬ አሥራት የወንጌል ሥራን ለመደገፍ ይውላል፡፡ አሥራት ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን መንፈሳዊ ግንኙነት የምንለካበት መዛሪያ በመሆን ያገለግላል፡፡

የአሥራት አወጣጥ፣ አጠቃቀም፣ አስፈላጊነትና የአሰረጫጨት ሥልት የእግዚአብሔርን ሥራ ለመደገፍ፣ መንፈሳዊ ህይወታችንን ለማጎልበትና ወንጌል የሚሰበክበትን አስተማማኝ የገንዘብ አቅም ለመፍጠር ታልሞ የተነደፈ ነው፡፡ ይህ የእግዚአብሔር ዕቅድ ሲሆን አንድ ታማኝ መጋቢ የሚወስደው የመጀመሪያ እርምጃ ተብሎ ይጠራል፡፡

በዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችን በአሥራት ዙሪያ በጀመርነው ምልከታ ቆይታ በማድረግ፡ የአሥራት ስርጭት በሌሎች ላይ ያለውን አንደምታና በህይወታችን ያለውን ተጽእኖ እንፈትሻለን፡፡

## እሁድ  የካቲት 11

# ኅብረት ፈጥሮ ተልዕኮውን በገንዘብ መደገፍ

የሱስ " 'ወንጌልን ስበኩ' " (ማር. 16፡5) " 'ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው' " "ያዘዝኋችሁን ሁሉ እንዲጠብቁ አስተምሯቸው" (ማቴ. 28፡19-20) ሲል ያዘናል፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር በዓለም እጅግ አስፈላጊ በሆነው ሥራ ላይ እንድንሰማራ ይፈልጋል፡፡ እግዚአብሔር ከሰጠን ሀብት ይህን ተልዕኮ መደገፍ የመጋቢነት ኃላፊነት ነው፡፡ የመጋቢነት ተሳትፎ ክርስቶስን ለሌሎች በማቅረቡ ረገድ የግል ቁርጠኝነት ጥልቀት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ እያንዳንዱ ደቀ መዝሙር፣ መጋቢና ሠራተኛ ከአሥራቱ ምንም ሳያስቀር ለዚህ የተቀደሰ ሥራ ማምጣት ይጠበቅበታል፡፡ ይህን ተልዕኮ በታማኝነት በገንዘባችን እየደገፍን ኅብረት እንዲኖረን ጌታን በጸሎት እንጠይቅ፡፡

**ይህንን ተልዕኮ ለመፈጸም እግዚአብሔር ያጸደቀው የገንዘብ ዕቅድ ምንድን ነው? "'አሥራቱን ሁሉ' " ማለት ምን ማለት ነው? (ሚልክ. 3፡10)፡፡ " 'በቤቴ መብል እንዲኖር' " የሚለው ሐረግ ፍቺስ ምን ይመስላል?**

-----------------------------------------------------------------------------------------

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ሰዎች ከአብርሃምና ያዕቆብ ዘመን አንስቶ--ምናልባት ከዚያም በፊት አሥራታቸውን እየመለሱ ይገኛሉ (ዘፍ. 14፡20፣ 28፡22)፡፡ አሥራት ከፍ ባለ የገንዘብ ምንጭነት የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ለመደገፍ የተዘረጋ በእጅጉ ተገቢና ትክክለኛ አሠራር አካል ነው፡፡

የዚህ ዘመን አብላጫ ሕዝበ ክርስቲያን ለአምላካዊው ተልዕኮ እየሰጠ የሚገኘው ድጋፍ በአንፃራዊነት ሲታይ እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፡፡ ነገር ግን እያንዳንዱ ክርስቲያን አሥራቱን በታማኝነት ሰጥቶ ቢሆን ውጤቱ "የማይገመት፣ አስደናቂና ከአእምሮ በላይ በሆነ ነበር" —Christian Smith and Michael O. Emerson, *Passing the Plate* (New York: Oxford University Press, 2008), p. 27.

በእያንዳንዱ ዘመን እግዚአብሔር አምላካዊውን ተልዕኮ በገንዘባቸው የሚደግፉ ሕዝቦች ነበሩት፡፡ እኛ ሁላችን ይህን ዓለማቀፋዊ ኃላፊነት በገንዘባችን እየደገፍን በማስተዋልና በኅብረት የመሥራት ዐደራ ተጥሎብናል፡፡ ተልዕኮውን በገንዘባችን የምንደግፈው ባልተቀናጀ፣ በቸልተኝነት ወይም በድንገትና ያለ ዕቅድ መሆን የለበትም፡፡ የእኛ ተግዳሮት የእስራኤል ሕዝብና ሌዋውያኑ "እኛም የአምላካችንን ቤት ቸል አንልም" (ነህ. 10፡39) በማለት ከተናገሩት በላይ ነው፡፡ በ 1800ዎቹ ዘመናት አማኞች ከተጋፈጧቸው ሁናቴም ይበልጥ ተስፋ አስቆራጭ ነው፡፡ ዛሬ የቤተ ክርስቲያን አባላትና ፓስተሩ ዓለም አቀፍ ዓላማዎችን በሚያሟላና ለተልእኮው የገንዘብ ድጋፍ በሚያደርግ መልኩ በመንፈሳዊ ነገር አንድ ሆነው የጠበቀ ኅብረት ሊመሰርቱ ይገባል፡፡

**አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን በዓለም ዙሪያ ያለው ስፋትና መጠን ምን ያህል ግዙፍ እንደሆነ አስቡ (ራእ. 14፡6-7)፡፡ እያንዳንዳችን ይህን ሥራ በገንዘባችን ለመደገፍ ስላለብን ኃላፊነት ምን ያህል አስተውለናል?**

## ሰኞ **የካቲት 12**

# የእግዚአብሔር በረከቶች

በሚልክ. 3፡10 እንደተመለከትነው በአሥራታቸው ታማኝ ለሆኑ እግዚአብሔር ታላቅ በረከት እንደሚያፈስላቸው ቃል ገብቷል፡፡ ሆኖም የእግዚአብሔር በረከት

ባለ አንድ ገጽ ብቻ አይደለም፡፡ ነገሩን ጎላ አድርጎ ለመመልከት ያህል ለምሳሌ ሌሎች ነገሮችን ወደ ጎን ብለን የቁሳዊውን ሀብት ክምችት ብቻ እንደ በረከት የምንመለከት ከሆነ ከትክክለኛው የእግዚአብሔር በረከት አኳያ እንዲህ ያለው ዕይታ እጅግ ጠባብ ነው፡፡

በሚልክያስ የቀረበው በረከት መንፈሳዊ እንዲሁም ጊዜያዊ ነው፡፡ የእግዚአብሔር በረከት--በመዳን፣ በደስታ፣ በአእምሮ ሰላምና እግዚአብሔር ሁሌም ለእኛ በሚያደርግልን ምርጥ ነገሮች በተጨባጭ የተደገፈ ነው፡፡ ደግሞም በእግዚአብሔር ስንባረክ በረከቶቻችንን በችግር ውስጥ ላሉ ወገኖች የማካፈል ግዴታ አለብን፡፡ እኛ የተባረክነው ሌሎችን እንድንባርክ ነው፡፡ እግዚአብሔር እኛን ተጠቅሞ በረከቱን ወደ ሌሎች ማስተላለፉ እርግጥ ነው፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ 1ጴጥ. 3፡8-9፡፡ ጴጥሮስ በመባረክና መባረክን ወደ ሌሎች በማስተላለፍ መሃል ስላለው ዝምድና ምን እያለን ነው?**

------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------

አሥራትን በመመለስ የሚገኘው በረከት ሁሌም እጥፍ ነው፡፡ እኛ በመባረካችን ሌሎችን እንባርካለን፡፡ ከተሰጠን ላይ ለሌሎች መለገስ እንችላለን፡፡ እግዚአብሔር በእኛ ላይ የሚያፈሳቸው በረከቶች በውስጣችን አልፈው ወደ ውጭ ይኸውም ወደ ሌሎች ይፈሳሉ፡፡ "ስጡ፣ ይሰጣችኋል፤ በምትሰፍሩት መስፈሪያ... ተሰፍሮ በዕቅፋችሁ ይሰጣችኋል" (ሉቃስ 6፡38)፡፡

**በተጨማሪ በሐዋ. 20፡35 የቀረበው መልእክት ከአሥራት ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ የምናውለው እንዴት ነው?**

አሥራት መመለስ የሚያስተምረን ታላቁ በረከት በእግዚአብሔር መታመን ነው (ኤር. 17፡7)፡፡ "በዓይነቱ ልዩ የሆነው የአሥራት ሥርዓት የተመሰረተው ልክ እንደ እግዚአብሔር ሕግ ጽኑ በሆነው መርኅ ላይ ነው፡፡ ይህ የአሥራት ሥርዓት

ለአይሁዶች በረከት ባያመጣ ኖሮ እግዚአብሔር ባልሰጣቸው ነበር፡፡ ስለዚህ ይህን ሥርዓት እስከ ጊዜው ፍጻሜ ለሚከተሉ ሁሉ በረከት ይሆንላቸዋል፡፡ ሰማያዊ አባታችን ይህን ሥርዓት የተከተለ ቸርነት ያቋቋመው ለራሱ ሳይሆን ለሰዎች ታላቅ ብልጽግና ለማምጣት ሲል ነው፡፡ ይህ የበጎነት ሥርዓት ለሰዎች እንደሚያስፈልግ እግዚአብሔር ተመልክቶ ነበር፡፡" —Ellen G. White, *Testimonies for the Church*, vol. 3, pp. 404, 405.

**ሌላው ሰው ለእርስዎ የሰጠውን አገልግሎት ተከትሎ በጌታ ስለተባረኩባቸው ጊዜያት ያስቡ፡፡ እርስዎም በተመሳሳይ ወደ ሌላው ወገን መውጣት የሚችሉት እንዴት ነው?**

## ማክሰኞ የካቲት 13

# የአሥራት ዓላማ

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍ "እያበራየ ያለውን በሬ አፉን አትሠር፤ 'ደግሞም፣ ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋል' " ይላል፡፡ (1ጢሞቴ5፡18)፡፡ ሙሴ በዘዳግም 25፡4 ስለ በሬ፣ የሱስ ደግሞ በሉቃ. 10፡7 ስለ ሠራተኛ የተናገረውን ጳውሎስ ይጠቅሳል፡፡ ስለ በሬ የተነገረው ሀረግ ምሳሌያዊ የአነጋገር ስልትን የተከተለ እንደመሆኑ እየሠራ ያለን በሬ የሚበላውን አትንፈገው የሚል አንደምታ አለው፡፡ በተመሳሳይ ሁለተኛው ምሳሌያዊ አነጋገር ደግሞ፤ ወንጌል ለመስበክ ቀናኢ የሆኑ ወገኖች ደሞዝ ሊከፈላቸው እንደሚገባ ይጠቁማል፡፡

እግዚአብሔር የሚፈጥረውም ሆነ የሚሠራው ሥርዓትን ተከትሎ ነው፡፡ ሥርዓተ ፀሐይን፣ ሥርዓተ ምህዳርን፣ ቅንባሮተ ልመትን (በሰውነታችን የሚካሄድ የምግብ መፈጨት ሥርዓት)፣ የነርቭ ሥርዓትንና የሌሎች አያሌ ነገሮች ንድፍ አውጪ እርሱ ራሱ ነው፡፡ የአሥራት ሥርዓት ጥቅም ላይ የዋለው ለሌዋውያን ሲሆን (ዘኍ. 18፡26) በዚህም አሥራት በመገናኛው ድንኳን አገልጋዮቹን ለመደገፍ ይውል ነበር፡፡ ዛሬ በእኛ ዘመን ህይወታቸውን ለወንጌል ሥራ አሳልፈው የሰጡ ሰባኪዎችን

ከሌዋውያኑ ጋር አመጣጥነን ልንመለከታቸው እንችላለን፡፡ እግዚአብሔር የዘረጋውና በመላው የደኅንነት ታሪክ ጥቅም ላይ የዋለው ሥርዓተ አሥራት-- አገልግሎቱ እንዲደገፍ እርሱ የመረጠው ዘዴ ነው፡፡

**ጳውሎስ "ወንጌልን የሚሰብኩ ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ከወንጌል እንዲቀበሉ ጌታ አዘአል" (1ቆሮ. 9፡14) ሲል ምን ማለቱ ነው? የሃረጉ ሥነ ምግባራዊ አንደምታስ ምንድን ነው? ወንጌል የሚያሰራጩ ወገኖችን ስለ መደገፍ አስፈላጊነት 2ቆሮ. 11፡7-10 ምን ያስተምራል?**

------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------

"እናንተን ለማገልገል ስል ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ርዳታ በመቀበሌ እነርሱን ዘርፌአቸዋለሁ" (2ቆሮ. 11፡8) በማለት ጳውሎስ ይናገራል፡፡ ጳውሎስ ሀብታም የነበረችውን የቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን እያገለገለ ከደኻዋ የመቄዶኒያ ቤተ ክርስቲያን ምንዳ መቀበሉን በምጸት እየተናገረ ነበር፡፡ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክት ወንጌልን የሚሰብኩ ሊከፈላቸው ይገባል የሚል ነው፡፡

አሥራት ለአንድ የተወሰነ ዓላማ ጥቅም ላይ ሊውልና በዚያው እንደጸና ሊቆይ ይገባል፡፡ "አንድ የተለየ ጥቅም ላይ እንዲውል የተመደበው አሥራት ለድኾች መደጎሚያ የገንዘብ ምንጭ አይደለም፡፡ ይልቁንም በተለይ ወንጌልን ለዓለም ለማዳረስ የሚሠሩ ታማኞችን ለመደገፍ ሊውል የተገባ ነው፡፡ ከዚህ ዓላማ ውጪ ወደ ሌላ መሄድ የለበትም፡፡" —Ellen G. White, *Counsels on Stewardship*, p. 103.

**ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡ ዘሌዋ. 27፡30፡፡ በዚህ ስፍራ የምንመለከተው መርኅ ከዛሬው ጋር ገጣሚ የሚሆነው በምን መልኩ ነው?**

**ረቡዕ** **የካቲት 14**

# ጎተራ

ለነፋስ ግምጃ ቤት (ኤር. 10፡13)፣ ለውሃ ማከማቻ (መዝ. 33፡7)፣ ለበረዶና ለዐመዳይ መጋዘን (ኢዮ. 38፡22) ያለው እግዚአብሔር ሁሉንም ሙሉ ለሙሉ ይቆጣጠራል፡፡ አሥራት ግን እጅግ የከበረው የእርሱ ጎተራ ነው፡፡ “ ‘በመገናኛው ድንኳን በሚያገለግሉበት ጊዜ ለሚሠሩት ሥራ ደመወዝ እንዲሆናቸው ከእስራኤል የሚወጣውን አሥራት ሁሉ ለሌዋውያን ርስት አድርጌ ሰጥቻቸዋለሁ’ ” (ዘኁ. 18፡21)፡፡ ይህ አሥራት ስለ ሚውልበት ስፍራ በመጀመሪያ የተጠቀሰው ጥቅስ ዛሬም “የግምጃ ቤቱ መርጎ” በመባል ይታወቃል፡፡ እስራኤላውያን አሥራታቸውን እግዚአብሔር በመረጠው ስፍራ ይዘው የሚመጡበት ተጨማሪ መመሪያ ሰጥቷቸው ነበር (ዘዳ. 12፡5-6)፡፡ በሰለሞን ዘመን አሥራት የሩሳሌም ወደሚገኘው ቤተ መቅደስ ይመለስ ነበር፡፡ ነቢዩ ሚልክያስ “ ‘አሥራቱን ሁሉ ወደ ጎተራ አስገቡ’ ” (ሚልክ. 3፡10) በማለት ለእስራኤላውያን የነገራቸውን ተከትሎ የዚህን “ጎተራ” ምንነትና የሚገኝበትን ስፍራ ጠንቅቀው ተረድተው ነበር፡፡ አምላካዊው ግምጃ ቤት ኃይማኖታዊ አገልግሎቶች የሚከናወኑበትንና ሌዋውያን የሚደገፉበትን ስፍራ ይወክል ነበር፡፡

**የእግዚአብሔርን ጎተራ ለማሳየት ሌሎች ምን ዓይነት ስያሜዎች ጥቅም ላይ ውለዋል? 1ዜና. 26፡20፣ 2ዜና. 31፡11-13፣ ነህ. 10፡38)፡፡**

-----------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------

ቅዱስ የሆነውን አሥራት ወደ እግዚአብሔር ጎተራ ማምጣት ብቸኛው ልንከተለው የሚገባ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌ ነው፡፡ እግዚአብሔር በእያንዳንዱ አግባብ አሥራትን የሚያስተዳድርበት ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ነበረው፡፡ ዓለም አቀፍ ሰባተኛ

ቀን አድቬንቲስትን አስመልክቶ ቤተ ክርስቲያን የምትከተለው የግምጃ ቤት መርኅ ተቀባይነት ያለውና በተግባርም የዋለ ነው፡፡ አባላት--የቤተ ክርስቲያን አባል በሆኑበት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት አሥራታቸውን ለሰበካው (ፊልድ) እንዲመልሱ ይበረታታሉ፡፡ ፓስተሮች ደሞዛቸውን ከሰበካው ግምጃ ቤት ይቀበላሉ ነው፡፡

"የእግዚአብሔር ሥራ እየተስፋፋ በሄደ መጠን ለእርዳታ የሚቀርቡ ጥሪዎች ያለማሰለስ ይበራከታሉ፡፡ ታዲያ እነዚህ ጥሪዎች ምላሽ ያገኙ ዘንድ ክርስቲያኖች 'በቤቴ መብል እንዲኖር አሥራቱን ሁሉ ወደ ጎተራ አስገቡ' (ሚልክ. 3፡10) የሚለውን አምላካዊ ትእዛዝ ሊሰሙ የተገባ ነው፡፡ ራሳቸውን በክርስቲያንነት የገለጹ ወገኖች አሥራታቸውንና መባቸውን በታማኝነት ለእግዚአብሔር የሚያመጡ ከሆነ ጎተራው ሙሉ ይሆናል፡፡ እንዲህ ከሆነ ቤተ ክርስቲያን የወንጌል ሥራን ለመደገፍ ልዩ ልዩ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች መጠቀም አያስፈልጋትም፡፡" —Ellen G. White, *The Acts of the Apostles,* p. 338.

**ሰዎች አሥራታቸው ወደ ፈለጉት አቅጣጫ ቢልኩ ሊከሰት ስለሚችለው ነገር አሰብ ያድርጉ፡፡ ሁሉም ሰው እንደዚያ አድርጎ ቢሆን በእግዚአብሔር ሥራ ላይ ምን ሊከሰት ይችል ነበር? ጉዳዩ እንዲህ ከሆነ አሥራታችንን ወደ ትክክለኛው ክፍል መላካችን አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?**

## ሐሙስ የካቲት 15

# አሥራት እና ጽድቅ በእምነት

**በሮሜ 3፡19-24 የምናገኘው የእምነታችን ማዕከልና ወሳኝ እውነት ምንድን ነው? ይህን አስተምህሮ ሁልጊዜ የእምነታችን መሰረት አድርገን መጠበቃችን የግድ የሆነው ለምንድን ነው?**

------------------------------------------------------------------------------------------

ሁላችንም ኃጢአት የሠራንና የእግዚአብሔር ክብር የጎደለን ፍጡራን እንደመሆናችን የደኅንነት ባለቤቶች መሆን እንደማይገባን ከእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ገጽ ፍሬ ሃሳብ መረዳት እንችላለን (ሮሜ 3፡23)፡፡ በችሎታችን ወይም በመልካም ሥራችን የጽድቅ ባለቤት ከሆንን ደግሞ፤ እንዲህ ያለው ጽንሰ ሃሳብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ሊጣረስ ነው፡፡

**ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡ ሮሜ 4፡1-5፡፡ ጥቅሶቹ ከመልካም ሥራ በተቃራኒ ስለ ጸጋ ምን ያስተምሩናል?**

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

ስለዚህ ደኅንነት ለማይገባቸው የተሰጠ ስጦታ ነው (ኤፌ. 2፡8-9)፡፡ የደኅንነት ባለቤት መሆን የቻልነው የክርስቶስ ፍጹም መሥዋዕትነት ለእኛ በመቆጠሩ ነው፡፡ አሥራትን በተመለከተ የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር በመመለሳችን ይህ አምላክ የእኛ ዕዳ የለበትም፡፡ አሥራት የእግዚአብሔር በመሆኑ ከተስማማን የራሱን ለራሱ መልሰን በጎ ምላሽ መጠበቅ ይኖርብናል?

እንደ ክርስቲያን መልካም ተግባሮችን እንድናደርግ የተፈጠርን ብንሆንም አሥራታችንን መመለሳችን ከሌሎች በጎ ተግባራት በላቀ የደኅንነት ባለቤት አያደርገንም፡፡ "ምክንያቱም፣ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀልንን መልካም ሥራ እንድንሠራ በክርስቶስ ኢየሱስ የተፈጠርን የእግዚአብሔር እጅ ሥራዎች ነን" (ኤፌ. 2፡10)፡፡

አሥራት መመለስ እግዚአብሔር እንድናደርግ ከጠየቀን አኳያ ግለሰቡ የሚገኝበትን ሁናቴ ይኸውም ትሁትና ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ወይም ሀሳበ ግትር እና እምቢተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡ እግዚአብሔርን የምንወድ ከሆነ እንታዘዛለን፡፡ አሥራት እኛ በእርግጥ በዚህ ምድር መጋቢዎች መሆናችንንና ሁሉም ነገር የእግዚአብሔር መሆኑን ማስተዋላችንን ውጫዊ በሆነ አኳኋን የምንገልጽበት መንገድ ነው፡፡ ሰንበት

የእግዚአብሔርን ፈጣሪነትና አዳኝነት በየሳምንቱ የምናስታውስበት ዕለት እንደመሆኑ፤ አሥራት መመለስም ተመሳሳይ ተዛምዶ ሊኖረው ይችላል፡፡ በመሆኑም እኛ የራሳችን አለመሆናችንን--ይልቁንም ህይወታችንና መዳናችን ከእግዚአብሔር የተሰጡ ስጦታዎች መሆናቸውን ያስታውሰናል፡፡ በውጤቱም አሥራት መመለስ የዚያ እምነት ተጨባጭ መገለጫ መሆኑን በመቀበል እውነታውን ልንገነዘብና የእምነት ህይወት መኖር እንችላለን፡፡

**ሉቃ. 21፡1-4 በእምነት ስለ መኖር የሚሰጠን ፍንጭ ምን ይመስላል?**

## አርብ **የካቲት 16**

**<u>ተጨማሪ ሃሳብ</u>፡** እያንዳንዱ እስትንፋስ፣ እያንዳንዱ የልብ ምት እና እያንዳንዱ የህልውናችን መንስኤ የሚመጣው ከጌታ ብቻ መሆኑን በቀላሉ ስንረሳ እንስተዋላለን፡፡ በሐዋ. ምዕ. 17 ("ዓለምንና በውስጡ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ" [ሐዋ. 17:24] ) እርሱ ፈጣሪ ብቻ ሳይሆን ሁሉንም ነገር ደግፎ የያዘ ("የምንኖረውና የምንንቀሳቀሰው፤ ያለነውም በእርሱ ነው [ሐዋ. 17:28]) እውነተኛ አምላክ መሆኑን ጳውሎስ ለአቴናውያን ሲመሰክር ይደመጣል፡፡ የአቴና ሰዎች ስለ እውነተኛው አምላክ አያውቁም ነበር፡፡ ነገር ግን ይህን ለምናውቅ ለእኛ ይህ ዕውቀታችን የዕለት ከዕለት አኗኗራችን አስኳል ሊሆን ይገባል፡፡ እግዚአብሔር በእኛ ላይ ያለው ባለቤትነት ስፍር ቁጥር የሌለው እንደመሆኑ፤ እኛም እንደ ባለቤትነቱ አግባብ መመላለስ ይጠበቅብናል፡፡

"እግዚአብሔር በእኛ ላይ የባለቤትነት መብት አለው፡፡ ሀብት ንብረቱን በሰው ልጆች እጅ ያኖረው ይህ አምላክ ከሰጠው አንድ አሥረኛ ለሥራው በታማኝነት እንዲመለስ ይጠይቃል፡፡ ይኸው መጠን በአምላካዊው ጎተራ እንዲገባ ያዛል፡፡ ይህ ለተቀደሰ ዓላማ መዋል የሚኖርበት፣ ባለቤቱ እንደ ራሱ ንብረት የሚመለከተው አሥራት ቅዱስ እንደ መሆኑ፤ የደኅንነትን መልእክት ለሁሉም የዓለም ክፍሎች ለሚያስራጩ ወገኖች መዋል ይኖርበታል፡፡ ወደ አምላካዊው ግምጃ ቤት የሚፈሰው የገንዘብ መጠን የእውነት ብርሃን በቅርብም ሆነ በሩቅ ወዳሉ ወገኖች

የሚደርስበት ነው፡፡ የጌታን ድንጋጌ በታማኝነት በመታዘዝ ሁሉም ነገር የእርሱ መሆኑን አምነን መቀበላችንን እናሳያለን፡፡"—Ellen G. White, *Testimonies for the Church,* vol. 6, p. 386.

## መወያያ ጥያቄዎች:

1. **ጊዜው በፍጥነት ወደ ዘላለማዊነት እየተሻገረ ይገኛል፡፡ የእግዚአብሔር የሆነውን ለራሳችን አናስቀር፡፡ በውስጣችን ምንም መልካም ነገር ሳይኖር መስጠት እንደማንችል ሁሉ ያለ አንዳች ጥፋት መከልከልም አንችልም፡፡ በፍጥረትም ሆነ በቤዛነት የእርሱ የሆነውን ልባችንን ምንም ሳናስቀር እንድንሰጠው ይጠይቀናል፡፡ ዕውቀትዎን እንዲያካፍሉ ሲጠይቆት ከማካፈል ወደ ኋላ አይበሉ፤ ገንዘብዎን ሲጠይቆትም እንዲሁ--ይስጡ ምክንያቱም የእርሱ ነውና፡፡"—Ellen G. White, *The Acts of the Apostles,* p. 566. ኤለን ኋይት በዚህ መልእክቷ "የእግዚአብሔር የሆነውን ለራሳችን አናስቀር... በውስጣችን ምንም መልካም ነገር ሳይኖር መስጠት እንደማንችል ሁሉ ያለ አንዳች ጥፋት መከልከልም አንችልም" ስትል ምን ማለቷ ነው? አሥራት ሳንመልስ ስንቀር ከራሳችን ምን እንሰርቃለን?**

2. **ሁሉም የቤተ ክርስቲያን አባላት አሥራታቸውን ከአምላካዊው "ጎተራ" በተቃራኒ ለፈለጉት ፕሮጀክት ቢያውሉ ሊከሰት በሚችለው አንደምታ ዙሪያ ተወያዩ፡፡ እንዲህ ያለው አስተሳሰብ መጥፎ የሆነው ለምንድን ነው? በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ምን ሊከሰት ይችላል? እንዲህ ያለው ድርጊት በመሃላችን አስከፊ መሰነጣጠቅ የሚያስከትለው ለምንድን ነው?**

3. **በሉቃ. 21 እንደምናነበው ምንም እንኳ የሱስ በወቅቱ በቤተ መቅደስ ይካሄድ የነበረውን ንቅዘት ያውቅ የነበረ ቢሆንም ነገር ግን ድሃዋ መበለት ይዛ ስለቀረበችው ስጦታ አመስግኗል፡፡ ለቤተ ክርስቲያን በሚመለስ አሥራት አጠቃቀም ዙሪያ ጥያቄ አለኝ በሚል አሥራቱን ወደ ሌላ ፕሮጀክት ለማዞር ለሚያስብ ሰው ይህ ምን ሊያስተምር ይገባል?**

# የምስጋና ስጦታዎች

**ሰንበት ከሰዓት**

**ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ማቴ.** 6፡19–21፣ ኤፌ. 2:8፣ 1ጴጥ. 4:10፣ ሉቃ. 7:37–47፣ 2ቆሮ. 8:8–15፣ 2ቆሮ 9:6-7፡፡

**የሳምንቱ መታሰቢያ ጥቅስ:-**

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና" *(ዮሐ. 3፡16)፡፡*

አምላካችን ለጋስ አምላክ ነው፡፡ ይህ ታላቅ እውነት እጅግ ብርቱ ሆኖ በየሱስ መሥዋዕትነት ታይቷል፡፡ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከ መስጠት ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና" (ዮሐ. 3፡16)፡፡ "እናንተ ክፉዎች ሆናችሁ ሳላችሁ፣ ለልጆቻችሁ መልካም ስጦታን መስጠት ካወቃችሁበት፣ የሰማዩ አባታችሁ ታዲያ ለሚለምኑት መንፈስ ቅዱስን እንዴት አብልጦ አይሰጥ!" (ሉቃ. 11፡13)፡፡

የእግዚአብሔር ጸባይ መስጠት፣ መስጠት ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ጸባይ ማንጸባረቅ የምንፈልግ ሁሉ መስጠት ይጠበቅብናል፡፡ "ራስ ወዳድ ክርስቲያን" ከሚለው ሀረግ የበለጠ ከተጨባጩ እውነታ ጋር የሚጋጭ ነገር የለም፡፡

ለተደረገልን በጎነት ምላሻችንን ከምናቀርብባቸው መንገዶች አንዱ ስጦታ ነው፡፡ ስጦታዎቻችን--ምስጋናችንንና ፍቅራችንን የምንገልጽበትን ዕድል ይሰጡናል፡፡ የሱስ

የተዋጁትን ቅዱሳን እንኳን በደህና መጣችሁ ብሎ በሚቀበልበት በዚያ ቀን ጸጋውን ተቀብለው የዳኑ ወገኖችን ስንመለከት እነዚህ ነፍሳት የመንግሥተ ሰማይ ወራሾች የሆኑት በእኛ ስጦታ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

በዚህ ሣምንት አንዳንድ ጠቃሚ የስጦታ ክፍሎችን እንመለከታለን፡፡ ከገንዘባችን፣ ከጊዜያችንም ሆነ ከመክሊታችን ላይ በለጋስነት መቸር ማለት--ባመንነው መሰረት መመላለስና የምናገለግለውን የእግዚአብሔር ባህሪ በጠንካራ መንገድ መግለጽ ነው፡፡

**እሁድ** **የካቲት 18**

## "ሀብትህ ባለበት"

ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡ ማቴ. 6፡19-21፡፡ ምንም እንኳ ለጥቅሶቹ ዕንግዳ ባንሆንም፤ ምድራዊው ሀብትና ንብረት በእኛ ላይ ሊኖረው ከሚችለው ብርቱ ተጽእኖ ነፃ የምንሆነው እንዴት ነው? ቆለ. 3፡1-2፡፡

------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------

" 'ሀብትህ ባለበት ልብህም በዚያ ይሆናልና' " (ማቴ. 6፡21) ሲል ክርስቶስ ይነግረናል፡፡ የዚህ መግለጫ ሙሉ ዐውደ ሃሳብ ቀደም ባሉት ሁለት ቁጥሮች ማለትም--ሀብትን በምድርና በሰማይ በማከማቸት መሃል ያለው ልዩነት በንጽጽር ቀርቦአል፡፡ በምድር የሚከማቸው ሀብት በሶስት ቃላት ይኸውም፡ ብል፣ ዝገት እና ሌባ (ማቴ፣ 6፡19) በሚል ተገልጾአል፡፡ እነዚህ ሁሉም ምድራዊ ሀብታችን ምን ያህል ጊዜያዊና መንገደኛ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ ምድራዊ ነገሮች ምን ያህል በፍጥነት ሊጠፉ እንደሚችሉ የማያውቅ ከቶ ማን አለ? "በዚህ ምድር ማንኛውም ነገር ሊበሰብስ፣ ሊጠፋ፣ ሊሰረቅና ሊታጣ የሚችል እንደመሆኑ--ተለዋዋጭ፣ የማያስተማምንና ደኅንነቱ የማይጸና ነው፡፡ ሰማይ ግን የምድር ተቃራኒ እንደመሆኑ በዚያ ማንኛውም ነገር ዘላለማዊ፣ ጸንቶ የሚኖር፣ አስተማማኝ ደኅንነት ያለውና የማይጠፋ ነው፡፡ —C. Adelina Alexe, "Where Your Heart Belongs," in *Beyond*

*Blessings, edited by Nikolaus Satelmajer,* (Nampa, Idaho: Pacific Press Publishing Association, 2013), p. 22.

ወደ ንብረትዎ መልከት ያድርጉ፡፡ ያፈሩት ሀብት የቱንም ያህል አነስተኛ ሊሆን ቢችል የኋላ ኋላ መወገዱ አይቀርም፡፡ ይሁን እንጂ ብልህ መጋቢ ሀብቱን ሰላማዊ ስፍራ ከሆነው ሰማይ ውጪ ማኖሩ ሊያሳስበው ይገባል፡፡ በዚያ የተከማቸ ሀብት--የዓለም ኢኮኖሚ መቀዛቀዝ፣ ሌብነት ወይም ዝርፊያ አያሰጋውም፡፡

ማቴ. 6፡19-21 የመጋቢነትን እጅግ አስፈላጊ ጽንሰ ሃሳብ ይዟል፡፡ ያፈሩት ሀብት ልቦን ከመሳብ፣ ከመጥለፍ፣ ከመነዝነዝና ከማጥመድ አይቦዝንም፡፡ በቁሳዊው ዓለም ልብ የሚከተለው ሀብትን በመሆኑ፤ ሀብት የሚገኝበት ስፍራ እጅግ አስፈላጊና ወሳኝ ነው፡፡ በምድራዊው አስፈላጊ ነገርና ጥቅም ላይ አብልጠን ትኩረት ካደረግን ስለ ሰማያዊ ነገሮች ማሰብ አዳጋች ይሆንብናል፡፡

በእግዚአብሔር እናምናለን እየተባለ ልብ ግን ያለው በምድራዊው መዝገብ ላይ ከሆነ ይህ--መመጻደቅ ነው፡፡ ተግባራችን ከአንደበታችን ከሚወጣው ቃል ጋር መስማማት አለበት፡፡ በሌላ አነጋገር በምድር ያለውን ሀብታችንን በዐይነ ሥጋ ብንመለከተውም፤ ነገር ግን መባችንና ስጦታችን በሰማይ መከማቸቱን በእምነት ልናይ ይገባል (2ቆሮ. 5፡7)፡፡ ምንም እንኳ የሚያስፈልጉን ነገሮች በተጨባጭ መሟላት የሚገባቸው ቢሆንም ነገር ግን ዘላለማዊ ባህሪ ያለውን ትልቁን ሥዕል ሁሌም በአእምሮአችን ልናኖር የተገባ ነው፡፡

**ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡ ዕብ. 10፡34፡፡ ጳውሎስ ምድራዊውንና ሰማያዊውን ሃብት በንጽጽር በማቅረብ ምን ዓይነት አስፈላጊ ነጥብ ያነሳል?**

## ሰኞ የካቲት 19

# የአምላካዊው ጸጋ መጋቢዎች

**በኤፌ. 2፡8 መሰረት ሌላው በእግዚአብሔር የተሰጠን ነገር ምንድን ነው?**

ጸጋ "የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፡፡" ጸጋ ለእኛ የማይገባ አምላካዊ ስጦታ ነው፡፡ እግዚአብሔር በዚህች ምድር ላይ ጸጋውን አፍስሶአል፡፡

እኛ የማንቃወመው ከሆነ ይህ ጸጋ ቁልቁል ወደ ህይወታችን ወርዶ ለአሁንና ለዘላለም ይለውጠናል፡፡ ሰማያዊው ባለጠግነትና ብርታት በሙሉ በእግዚአብሔር ጸጋ ውስጥ ተካትቶአል (2ቆሮ. 8፡9)፡፡ መላእክት ሳይቀሩ በዚህ ወደር የለሽ ስጦታ ይደነቃሉ (1ጴጥ. 1፡12)፡፡

እግዚአብሔር ከሰጠን ስጦታዎች ሁሉ እጅግ የከበረው በየሱስ ክርስቶስ የተሰጠን ጸጋ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡ ጸጋው ባይሰጠን ያለ ተስፋ በቀረን ነበር፡፡ ኃጢአት በሰው ልጆች ላይ ያለው ተጽእኖ እጅግ ግዙፍ በመሆኑ ሰብዓዊው ፍጡር ከዚህ አሳዛኝ ክስተት ራሱን ነፃ ማድረግ አይቻለውም፡፡ ለእግዚአብሔር ሕግ መታዘዝ እንኳ በራሱ ህይወት ሊሰጠን አይችልም፡፡ “ታዲያ ሕግ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል የሚቃወም ነውን? ከቶ አይደለም፤ ሕግ የተሰጠው ሕይወትን ለማስገኘት ቢሆን ኖሮ፣ በርግጥም ጽድቅ በሕግ በኩል በተገኘ ነበር፡፡” (ገላ. 3፡21)፡፡ ደግሞም እኛን ሊያድን የሚችል ሕግ ቢሆን፤ የእግዚአብሔር ሕግ ይሆን ነበር፡፡ ነገር ግን ሕግ ያን ማድረግ እንደማይችል ጳውሎስ ተናግሯል፡፡ ከዳንን--የምንድነው በጸጋው ብቻ ይሆናል፡፡

**ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡ 1ጴጥ. 4፡10፡፡ መጋቢነት ከጸጋ ጋር እንዴት ይዛመዳል? ለእግዚአብሔርና ለሌሎች መስጠት አምላካዊውን ጸጋ እንዴት ሊያሳይ እንደሚችል ያስረዱ፡፡**

______________________________________________________________________________

አምላካዊውን የጸጋ ስጦታ ስንቀበል በምላሹ “የእግዚአብሔር ልዩ ልዩ ጸጋ መጋቢ” (1ጴጥ. 4፡10) እንሆናለን ሲል ጴጥሮስ ተናግሯል፡፡ ይህ ማለት እግዚአብሔር ስጦታዎችን ሰጥቶናል፡፡ እኛ ደግሞ ከዚያ ከተሰጠን ላይ መልሰን መስጠት ያስፈልገናል፡፡ በጸጋው የተሰጠን ስጦታ ራሳችንን ደስ ለማሰኘትና ለግል ጥቅማችን ብቻ ሳይሆን የወንጌልን ሥራ ለማፋጠን ጭምር ነው፡፡ በነፃ ስለተሰጠን (ጸጋ ማለት ይኸው ነው) አቅማችን በፈቀደ መጠን በነፃ መስጠት ይጠበቅብናል፡፡

**በእግዚአብሔር ስለተሰጡት ሁሉም ነገሮች ያስቡ፡፡ በነፃ ለተሰጡት ጸጋ መጋቢ መሆን የሚችሉባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው?**

**ማክሰኞ** **የካቲት 20**

# ምርጡ ስጦታችን

**ጥቅሱቹን ያንብቡ፡ ሉቃ. 7፡37-47፡፡ ታሪኩ ስጦታ ለማቅረብ ትክክለኛው መነሻ ምክንያትን ምን መሆን እንዳለበት ያስተምረናል?**

______________________________________________________________________

______________________________________________________________________

ማርያም ወደ ክፍሉ ስትገባ የሱስ በጠረጴዛው ፊት ማዕድ ተቀምጦ ተመለከተችው፡፡ ከዚያም ውድ ዋጋ ያለውን የአልባስጥሮስ ሽቶ ብልቃጥ ሰብራ አፈሰሰችበት፡፡ አንዳንዶች አጉል ህይወት የኖረች ሴት መሆኗን ከግምት በማስገባት ይህ ድርጊቷ ተገቢ እንዳልሆነ አሰቡ፡፡

ነገር ግን ማርያም ከእርኩሳን መናፍስት ነፃ ሆና የተፈወሰች ሴት ነበረች (ሉቃ. 8፡2)፡፡ ከዚያም ለዓልአዛር ትንሳኤ ምስክር ከሆነች በኋላ በከፍተኛ ምስጋና የተሞላች ሴት ሆነች፡፡ በጣም ውድ ንብረቷ የነበረውን ሽቶ፤ ለየሱስ አመስጋኝነቷን የምታሳይበት መንገድ አድርጋ ተጠቀመችበት፡፡

ይህ ታሪክ ስጦታ ስንሰጥ እውነተኛው መነሻ ምክንያታችን ምስጋና ሊሆን እንደሚገባ ይነግረናል፡፡ ደግሞስ በዋጋ ሊተመን ለማይችለው የጸጋ ስጦታው ምን ሌላ ምላሽ ሊኖረን ይችላል? አምላካዊው ቸርነት እንድንሰጥ ያበረታታናል፡፡ ቸርነቱ ከምናቀርበው ምስጋና ጋር ውህደት ሲፈጥር ጊዜያችንን፣ መክሊታችንን፣ ሀብታችንንና አካላችንን ያካተተ ትርጉም ያለው ስጦታ ይሆናል፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ዘፀ. 34፡26፣ ዘሌዋ. 22፡19–24፣ ዘኁ. 18፡29፡፡ ምንም እንኳ ዐውደ ጽሑፉ ከዛሬው ዓለም ፍጹም የተለየ ቢሆንም ነገር ግን ከምናቀርበው ስጦታ አኳያ ከጥቅሶቹ ልንወስድ የሚገቡን መርኆዎች ምንድን ናቸው?**

______________________________________________________________________

ምንም እንኳ ምርጥ ያልናቸው ስጦታዎች የልባችንን የማያደርሱ ቢመስሉንም በእግዚአብሔር ፊት ግን ትልቅ ቦታ አላቸው፡፡ ምርጥ የሆነውን ለእግዚአብሔር መስጠታችን በህይወታችን ውስጥ እርሱን ማስቀደማችንን ያሳያል፡፡ መቼም የሆነ ውለታ ፍለጋ ስጦታ አንሰጥም፡፡ ይልቁንም በክርስቶስ የሱስ ለተሰጠን ነገር ከማመስገንና ከማድነቅ የተነሳ የስጦታ እጆቻችንን እንዘረጋለን፡፡

“በምስጋና የተሞላ ፍቅር፣ አምልኮና ቸርነት ትንሽዋን ስጦታ የመስጠት ተነሳሽነትን ይፈጥራል፡፡ መለኮታዊ መዐዛ የተላበሰው በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የመሥዋዕት ስጦታ እጅግ የከበረ ዋጋ አለው፡፡ ነገር ግን መስጠት የምንችለውን ያህል ቤዛ ለሆነልን አዳኝ ለመስጠት ፈቃደኞች ከሆንን በኋላ በእርግጥ ምን ያህል የምስጋና ዕዳ ለእግዚአብሔር እንዳለብን ከተመለከትን፤ ለእኛ የከበረ ብለን ያቀረብነው ማንኛውም ስጦታ በጣም አነስተኛና በቂ እንዳልሆነ ይሰማናል፡፡ ሆኖም ይህን ለእኛ ምስኪን ሆኖ የታየንን ስጦታ መላእክት እንደ መልካም መአዛ ገጸ በረከት በዙፋኑ ፊት ያቀርቡና ተቀባይነት ያገኛል፡፡” —Ellen G. White, *Testimonies for the Church*, vol. 3, p. 397.

## ረቡዕ የካቲት 21

# የልብ መነሻ ምክንያቶች

ቀደም ባለው ትምህርት የምስኪኗን መበለት ልግስና ታሪክ ተመልክተን ነበር፡፡ የእርሷ መባ ከሌሎቹ ስጦታዎች ጋር ሲነጻጸር እጅግ አነስተኛ ቢመስልም ነገር ግን እውነተኛውን የባህሪዋንና የልቧን ተፈጥሮ ያሳየ ስለ ነበር “እርሷ ግን የሰጠችው በደኻ ዐቅሟ ያላትን መተዳደሪያ በሙሉ ነው” (ሉቃስ 21፡3) ብሎ የሱስ እንዲናገር መንስኤ ሆናው ነበር፡፡

እግዚአብሔር ብቻ (ያዕ. 4፡12) እውነተኛውን የእኛን መነሻ ምክንያት ያውቃል (ምሳ. 16፡2፣ 1ቆሮ. 4፡5)፡፡ አትረፍርፎ መስጠት እምብዛም የእምነታችንን ጥልቀት ስለማይጠይቅ፤ ከተሳሳተ መነሻ ምክንያት ተነስተን ትክክለኛ ነገር ልናደርግ የምንችልበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል፡፡ ነገር ግን ስለ ሌሎች በጎ ሲባል መሥዋዕት የሚያስከፍል ስጦታ ስንሰጥ፤ በእርግጥ ይህ ልግስናችን ስለ ልባችን የሚለው ብርቱ ነገር አለው፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ 2ቆሮ. 8፡8-15፡፡ ጳውሎስ ስለ መስጠትና ስለ መስጠት መነሻ ምክንያቶች ምን እያለ ነው? መጋቢነትን አስመልክቶ ከጥቅሶቹ ምን ዓይነት መርኅዎችን መውሰድ እንችላለን?**

________________________________________________________________________

________________________________________________________________________

ለመስጠት የቱንም ዓይነት መነሻ ምክንያት ሊኖር ቢችልም ነገር ግን ሂደቱ ከእኔነት ራስን ለሌሎች መሥዋዕት ወደ ማድረግ ያሸጋግራል፡፡ ይህ በራስ ወዳድነትና በመስጠት መካከል የሚደረግ የማያቋርጥ ጦርነት ከማንኛውም መንፈሳዊ ውጊያ በላይ በብርቱ ተጋድሎ የተሞላ ነው፡፡ ራስ ወዳድነት በአንድ ወቅት የጋመ ፍም የነበረን ልብ እንደ በረዶ ያቀዘቅዛል፡፡ ችግሩ የሚከሰተው ራስ ወዳድነት የክርስትና ተሞክሮአችን አካል እንዲሆን ስንፈቅድና ለዚሁ ራስ ወዳድነታችን ማመካኛ እየፈለግን በክርስቶስ ስም ማድረግ ስንጀምር ነው፡፡

የሁሉም ነገር ሥረ መሰረት አንድ ቃል ሲሆን ይኸውም ፍቅር ነው፡፡ ለሌሎች በጎ ሲባል ራስን መሥዋዕት አድርጎ እስከ መስጠት ፈቃደኛ የመሆን ፍቅር--እኔነት ካልተካደ በቀር ተገልጦ መታየት አይችልም፡፡

የእግዚአብሔር ፍቅር በሕይወታችን መንጸባረቅ ካልቻለ በቀር መስጠታችን የእግዚአብሔርን ፍቅር አያንጸባርቅም፡፡ የራስ ወዳድ ልብ ዝንባሌ ወደ ራሱ ብቻ በመሆኑ--ራሱን ብቻ ይወዳል፡፡ እኛ እንደ ተወደድን ሁሉ ሌሎችን መውደድ መማር እንችል ዘንድ ጌታ የልባችንን "ሸለፈት" እንዲገርዝ እንጠይቀው (ዘዳ. 10:16)፡፡

የሁሉም እውነተኛ ልግስና መሰረት የሆነው ፍቅር የአጠቃላዩ የክርስትና ለጋስነት ድምር ነው፡፡ እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር እኛም ለሌሎች የፍቅር አጸፋ እንድንሰጥ መንፈሳችንን ይቀሰቅሳል፡፡ ይህ ደግሞ ለመስጠት ዋና መነሻ ምክንያት ነው፡፡

**ከፍቅር ስሜት ይልቅ ከግዴታ አኳያ በፈቃደኝነት መስጠት ምን ችግር አለው?**

**ሐሙስ** **የካቲት 22**

# የመስጠት ተሞክሮ

ክርስቶስ ወደዚህ ምድር የመጣው ትክክለኛውን የእግዚአብሔር ጸባይ ሊገልጥ ነው ካልን አሁን አንድ ነገር ግልጽ ሊሆን ይገባል፡ እግዚአብሔር ይወደናል፣ ለእኛ እንዲሆን የሚሻውም ምርጥ የሆነውን ብቻ ነው፡፡ እርሱ ፈጽሞ ጉዳት የማያደርስብንን፣ ለገዛ ጥቅማችን የሚበጀውን ብቻ እንድናደርግ ይጠይቀናል፡፡ ይህ ደግሞ ለተሰጠን ነገር ደግ፣ ለጋስ፣ ፍልቅልቅና ደስተኛ ለጋሾች እንድንሆን እርሱ ያደረገልንን ጥሪን ያካትታል፡፡ በሙሉ ፈቃደኝነታችን ላይ የተመሰረተው የልግስና ስጦታችን እንደ ተቀባዮቹ ሁሉ ለገዛ ራሳችን--ለሰጪዎቹ ጥቅም የሚያስገኝ ነው፡፡ ከመቀበል ይልቅ መስጠት ምን ያህል የተባረከ እንደሆነ በዚህ መልኩ የሚሰጡ ራሳቸው ብቻ ያውቃሉ፡፡

**ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡ 2ቆሮ. 9፡6-7፡፡ እንዴት መስጠት እንዳለብን ጥቅሱ ጠቅለል አድርጎ የሚያቀርበው ሃሳብ ምን ይመስላል?**

____________________________________________________________

____________________________________________________________

በልግስና መስጠት እጅግ ግላዊና መንፈሳዊ ድርጊት ሊሆን ይገባል፡፡ በክርስቶስ ለተሰጠን ነገር ምስጋናችንን የምንገልጽበት የእምነት ሥራ ነው፡፡

“እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ” (ያዕ. 2፡20 /1962 ትርጉም/) እንደሆነ ሁሉ መስጠት እምነት እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ እምነታችን እንዲጨምር ከተፈለገ በተግባር ከመግለጽ ውጪ ሌላ ምንም የተሻለ ነገር የለም፡፡ ይኸውም እምነታችን ፈልቆ እንዲወጣ የሚያደርጉ ነገሮችን መተግበር ነው፡፡ በነጻና በልግስና ስንሰጥ የክርስቶስን ጸባይ የምናንጸባርቅበት ጎዳና ላይ ነን፡፡ በገዛ ድርጊታችን እርሱን እየተለማመድን እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል አብልጠን እየተማርን ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ መልኩ የሚፈጸም የልግስና ተግባር በጌታ ፊት ተአማኒነትን

በመገንባት "እግዚአብሔር ቸር መሆኑን ቀምሳችሁ እዩ፤ እርሱን መጠጊያ የሚያደርግ ምንኛ ቡሩክ ነው!" ለማለት ዕድል ይሰጠናል (መዝ. 34፡8)፡፡

"በየሱስ ፊት ላይ የሚያበራው ክብር የመሥዋዕትነት ፍቅር ሆኖ ይታያል፡፡ ከቀራንዮ የሚፈነጥቀው ብርሃን ራስን ለሌላ አሳልፎ የመስጠት ፍቅር ሲሆን ይህም ፍቅር ለምድራዊና ለሰማያዊ ሕይወት መመሪያ ሕግ ነው፡፡ 'የራስዋን የማትሻ ፍቅር' የምትመነጨው ከእግዚአብሔር ልብ ነው፡፡ ትሑቱና ራሱን ያዋረደው የሱስ ሰው ሊደርስበት በማይችለው ብርሃን የሚኖረውን እግዚአብሔር ባሕሪ ገለጸ፡፡" *የዘመናት ምኞት ገጽ 9-10 (አማርኛው ትርጉም)፡፡*

**ከተሰጠዎት በላይ በነፃ እና በልግስና በመስጠት እምነት በተጨባጭ እያደገ የሚሄድበትን እውነታ የተለማመዱበት መንገድ ምን ይመስላል?**

## አርብ **የካቲት 23**

**ተጨማሪ ሃሳብ፡** *"የነፃነት መንፈስ የሰማይ መንፈስ ሲሆን፤ የራስ ወዳድነት መንፈስ ደግሞ የሰይጣን መንፈስ ነው፡፡ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ያቀረበው የክርስቶስ ፍቅር እነሆ በመስቀል ላይ ተገለጠ፡፡ ሰብዓዊው ፍጡር ይድን ዘንድ ያለውን ሁሉ ከሰጠ በኋላ ከዚያም ራሱን መሥዋዕት አደረገ፡፡ እያንዳንዱ የዚያ የተባረከ አዳኝ ተከታይ ቅን ይሆን ዘንድ የክርስቶስ መስቀል ተማጽኖውን ያቀርባል፡፡ በዚያ በጉልህ የተቀመጠው መርኅ መስጠት፣ መስጠት የሚል ነው፡፡ ይህ በቅን ልብ ገቢራዊ የሚሆን የልግስና ተግባር የእውነተኛ ክርስቲያን ህይወት ፍሬ ነው፡፡ ምድራዊው መርኅ መያዝ፣ መሰብሰብ፣ ማጋበስ ሲሆን፤ በዚህም ደስታ ይገኛል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ሆኖም ፍሬው ሁሉ ሥቃይ፣ መከራና ሞት ነው፡፡"*—Ellen G. White, in *Advent Review and Sabbath Herald*, Oct. 17, 1882.

## *መወያያ ጥያቄዎች፡*

❶ **ስስትን ከክርስቶስ መንፈስ ጋር በእጅጉ ተቃራኒ የሚያደርገው ምንድን ነው? በኃጢአት የወደቀው ሰብዓዊ ፍጡር ከሚያዘነብልበት ተፈጥሮው በተቃራኒ ህሊናችን የሚፈቅደውን በማድረግ ራሳችንን መጠበቅ**

የምንችልባቸው መንገዶች ምንድን ናቸው?

❷ “እያንዳንዱ ሰው በቅሬታ ወይም በግዴታ ሳይሆን፣ በልቡ ያሰበውን ያህል ይስጥ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ሰው ይወዳል” (2ቆሮ. 9፡7)፡፡ “በደስታ” በሚል የተተረጎመው ይህ የግሪክ ቃል በአዲስ ኪዳን የምናገኘው አንድ ስፍራ ላይ ብቻ ሲሆን በእንግሊዝኛው “በመፍነክነክ” የሚል ፍቺ አለው፡፡ አባባሉ ስለ አኳኋናችን ምን ይነግረናል?

❸ በክርስቶስ የተቀበሏቸውን ነገሮች በሙሉ በዝርዝር ይጻፉ፡፡ ስለሚጽፏቸው ነገሮች ይጸልዩባቸው፡፡ ለተቀበልናቸው ነገሮች ምላሽ መስጠት ለምን እንዳስፈለገ እነዚህ ያሰፈሯቸው ዝርዝሮች ምን ሊያስተምሩን ይገባል?

❹ ራስ ወዳድነት--ራስን ከንቱ ለማድረግ አስተማማኝ ጎዳና የሆነው ለምንድን ነው?

❺ በአሁኗ ደቂቃ በእርስዎ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በእጦት የምትገኝን እህት ወይም ወንድም አሰብ ያድርጉ፡፡ ዛሬ ነገ ሳይሉ--አሁኑኑ ወደ ግለሰቡ ደርሰው ለማገልገል ምን ማድረግ ይችላሉ? ጉዳዩ ብርቱ መሥዋዕትነት የሚያስከፍሎ ቢሆን እንኳ ምን ማድረግ ይችላሉ?

# የመጋቢነት ሚና

**ሰንበት ከሰዓት**

*ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ቆለ. 1:16–18፣ ዕብ. 4:14–16፣ 3ዮሐ. 3፣ ዘፍ. 6:13–18፣ ራእ. 14:6–12፣ 1ጴጥ. 1:15-16፡፡*

**የሳምንቱ ዋና ጥቅስ፡-**

“እግዚአብሔር በቅድስና እንድንመላለስ እንጂ ለርኩሰት አልጠራንምና” *(1ተሰ. 4፡7)፡፡*

*የመጋቢነት ጽንሰ ሃሳብ ከያዘው ስፋትና ጥልቀት አኳያ በግዙፉ ገጽታ ብቻ ተደምመን በቀላሉ ልንስጥምና ውሉን ልንስት እንችላለን፡፡ መጋቢነት ቀላል ቢመስልም ነገር ግን ካለው ውስብስብ ይዘት አኳያ በቀላሉ በተሳሳተ አቅጣጫ ሊስተዋል ይችላል፡፡ ሆኖም ክርስቲያንም ሆነ ቤተ ክርስቲያን ከመጋቢነት ፋይዳ ውጪ ሊኖሩም፣ ሊሠሩም አይችሉም፡፡ ክርስቲያን መሆን መልካም መጋቢ መሆን ነው፡፡*

*“ይህ ጽንሰ-ሐሳብ ወይም ፍልስፍና ሳይሆን የሥራ መርኅ-ግብር ነው፡፡ የክርስትናን ሕግ የተከተለ የአኗኗር እውነት ነው. . . ሕይወትን በአጥጋቢ ሁኔታ ለማስተዋል ወሳኝና አስፈላጊ ነው፡፡ ለእውነተኛና በንቃት ለሚንቀሳቀስ ኃይማኖታዊ ተሞክሮ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ ጉዳዩ ለአእምሮ ተስማሚ ሀሳብ የያዘ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን መላው የሕይታችንን ክፍል የሚነካ የበጎ ፈቃዳችን ውጤትና ቁርጠኝነት ወሳኝ*

ውሌ ነው፡፡” —LeRoy E. Froom, *Stewardship in Its Larger Aspects (Mountain View: Calif.*, Pacific Press Publishing Association, 1929), p. 5.

አንዳንዶቹ የክርስቲያን መጋቢ እምቡጥ መርኅዎች ምንድን ናቸው? በዚህ ሣምንት መጋቢነት በክርስትና ሕይወት የሚጫወተውን ሚና የበለጠ እንመለከታለን፡፡

## እሑድ የካቲት 25

# ክርስቶስ እንደ አስኳል

የሱስ የመላው የመጽሐፍ ቅዱስ ገጾች አስኳል እንደመሆኑ (ዮሐ. 5፡39) ራሳችንን ከእርሱ ጋር ካለን ተዛምዶ አኳያ መመልከት ያሻናል፡፡ የሱስ የኃጢአትን ቅጣት ከፍሎ “ ‘ለብዙዎች ቤዛ’ ” ሊሆን መጣ (ማር. 10፡45)፡፡ በሰማይም ሆነ በምድር ሥልጣን ሁሉ የየሱስ ነው (ማቴ. 28፡18)፡፡ ደግሞም ሁሉም ነገር በእጁ ውስጥ ነው (ዮሐ. 13፡3)፡፡ ስሙ ከሌሎች ሁሉ የላቀ ነው፡፡ እናም አንድ ቀን ጉልበት ሁሉ ለእርሱ ይንበረከክለታል (ፊልጵ. 2፡9-11)፡፡ “የሱስ የማንኛውም ነገር ሕያው አስኳል ነው” —Ellen G. White, *Evangelism*, p. 186.

ክርስቶስ የመጋቢነታችን የልብ ትርታና የኃይላችን ምንጭ ነው፡፡ በእርሱ ምክንያት ትርጉም ያለው ሕይወት እንኖራለን፤ እርሱ የሕይወታችን ማዕከላዊ ክፍል መሆኑንም ለወጪ ወራጁ ሁሉ እናሳያለን፡፡ ጳውሎስ በአያሌ ውጣ ውረዶች ውስጥ እንዳለፈ እንገምታለን፡፡ ሐዋርያው በማንኛውም ስፍራ ቢሆን ወይም ምንም ቢደርስበት ለመኖሩ አንድ ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር ነበረው “ለእኔ መኖር ክርስቶስ ነው፤ ሞትም ማትረፍ ነው” (ፊልጵ. 1፡21)፡፡

**እነዚህን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ቆላ. 1፡16–18፣ ሮሜ 8፡21፣ 2ቆሮ. 5፡17፡፡ ለእኛ የሁሉም ነገር ማዕከል ክርስቶስ መሆኑን አስመልክቶ ጥቅሶቹ ምን ይነግሩናል?**

-----------------------------------------------------------------------------------------

የሕይወታችን አስኳል የሆነው ክርስቶስ የሌለበት እውነተኛ መጋቢነት የለም (ገላ. 2፡20)፡፡ “የተባረከ ተስፋችን” (ቲቶ 2፡13) ማዕከላዊ ክፍል ነው፡፡ “እርሱ ከሁሉ በፊት ነው፤ ሁሉም ነገር በአንድ ላይ ተያይዞ የጸናው በእርሱ ነው (ቆላ. 1፡17)፡፡

በፈረሶች በሚጎተተው ሠረገላ--ሁለቱ ተሽከርካሪ አካላት የሚያያዙበት ዘንግ የጋሪውን ክብደት የሚሸከመው ማዕከላዊ ክፍል እንደመሆኑ፤ ክርስቶስ የመጋቢው ሕይወት እምብርት ነው፡፡ ሁለቱ ተሽከርካሪ አካላት የሚያያዙበት ጠጣር ዘንግ መንኰራኩሮቹ እንዲዘወሩ በማድረግ ለሠረገላው ጽናት እንደሚሰጥ--የሱስም የክርስትና ተሞክሮአችን ጽኑና አስተማማኝ አስኳል ነው (ዕብ. 13፡8)፡፡ በማንኛውም የምናስበውም ሆነ የምናደርገው ነገር ላይ የእርሱ ተጽእኖ ሊሰማን ይገባል፡፡ በዙሪያችን ያሉ የመጋቢነት ገጽታዎች እምብርት እርሱ--ክርስቶስ ነው፡፡

" 'ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና' " (ዮሐ. 15:5)፡፡ የመጋቢነት ማዕከላዊ ክፍል ባዶውን የተተወ ከንቱ ነገር ሳይሆን ባህሪያችንን ለማረቅ ለአሁንና ለዘላለም በውስጣችን እየሠራ ያለ እውነት፣ ያውም ሕያው ክርስቶስ ነው፡፡

**የሱስ የሕይወታችን አስኳል ነው ማለት አንድ ነገር ሲሆን--ቢሆን ማለት ግን ሌላ ነገር ነው፡፡ የሱስ በእርግጥ ፈቅደውለት ቃል በገባው መሰረት በውስጥዎ እየኖረ ለመሆኑ ምን ያህል እርግጠኛ መሆን ይችላሉ?**

## ሰኞ   የካቲት 26

# የቤተ መቅደሱ ኃይማኖታዊ አስተምህሮ

ብዙውን ጊዜ አማኞች ቤተ መቅደሱን ከመጋቢነት ዐውድ አይመለከቱትም፡፡ የቤተ መቅደሱ አገልግሎት ለእምነታችን ወሳኝ ሥርዓት እንደ መሆኑ መጋቢነትም የዚህ ሥርዓት አካል ነው፡፡ "ክርስቶስ በሰማያዊው መቅደስ አገልግሎት የመስጠቱ ትክክለኛ ግንዛቤ የእምነታችን መሰረት ነው፡፡" —Ellen G. White, *Evangelism*, p. 221. የመጋቢነትን ሚና ከዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጽንሰ ሃሳብ አኳያ ማስተዋላችን እጅግ አስፈላጊና ወሳኝ ነው፡፡

በ1ነገሥ. 7፡33 ስለ ሠረገላ መንኰራኩር የተጻፈ መልእክት እናገኛለን፡፡ የቤተ መቅደሱን ነገረ መለኮት የመንኰራኩሩ እምብርት አድርገን እንመለከታለን፡፡ ከሁለቱ የሠረገላው መንኰራኩሮች ወይም ተሽከርካሪ አካላት ጋር የተቆራኘው የሠረገላው እምብርት የሆነው ዘንግ በዞረ ቁጥር ለተሽከርካሪው አካል የበለጠ ጽናትና ጥንካሬ ይሰጣል፡፡ ለኃጢአት መሥዋዕት ሆኖ ከሞተ በኋላ በድል ያረገው

(2ጢሞቴ. 1፡10) ክርስቶስ በሞቱ የቤተ መቅደስ አገልግሎት መሰረት በመሆን (ዕብ. 6፡19-20) ለእምነታችን ፅናት አስገኘ፡፡ አሁን በሰማያዊው ቤተ መቅደስ ሆኖ ስለ እኛ እያገለገለ ይገኛል (ዕብ. 8፡1-2)፡፡

"*ሶላ ስክሪፕቱራ ወይም መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ* የተሰኘውን መርኅ የምትከተለው ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ቤተ ክርስቲያን ነገረ መለኮታዊ ሥርዓት የተገነባው ከቤተ መቅደሱ ኃይማኖታዊ አስተምህሮ አጠቃላይ ምልከታ አኳያ ነው፡፡" —Fernando Canale, *Secular Adventism? Exploring the Link Between Lifestyle and Salvation* (Lima: Peru, Peruvian Union University, 2013), pp. 104, 105.

**የሚከተሉት ጥቅሶች ስለ የሱስ የቤተ መቅደስ አገልግሎት ምን ይነግሩናል? 1ዮሐ. 2:1፣ ዕብ. 4:14–16፣ ራእ. 14:7፡፡**

------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------

የቤተ መቅደሱ ነገረ መለኮት፤ የሁሉም ክርስትና ኃይማኖታዊ አስተምህሮ እምብርት የሆነውን ታላቁን የደኅንነትና የመዋጀት እውነት ገልጦ ለመመልከት ይረዳል፡፡ በቤተ መቅደሱ ውስጥ--ስለ እኛ የሞተውን ክርስቶስ ብቻ ሳይሆን በሰማያዊው መቅደስ እየሰጠ ያለውንም አገልግሎት እንመለከታለን፡፡ በተጨማሪም በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ የእግዚአብሔርን ሕግ አስፈላጊነትና የመጨረሻውን የፍርድ እውነታ ማየት እንችላለን፡፡ በፈሰሰው የየሱስ ደም ዕውን መሆን የቻለው የቤዛነቱ ተስፋ--ዋንኛውና የዚህ ሁሉ ማዕከል ነው፡፡

በቤተ መቅደሱ ኃይማኖታዊ አስተምህሮ እንደተገለጸው የመጋቢነት ሚና ከታላቁ የደኅንነት እውነት መልህቅ ጋር የተያያዘውን ሕይወት ያንጸባርቃል፡፡ ክርስቶስ ለእኛ ያደረገውንና እያደረገ ያለውን አብልጠን በጥልቀት ባስተዋልን ቁጥር ከመቼውም ይልቅ ወደ እርሱ፣ ወደ አገልግሎቱ፣ ወደ ተልዕኮውና ወደ አስተምህሮው እንቀርባለን--የመጋቢነትንም መርኅዎች በህይወታችን በተግባር እንገልጻለን፡፡

**ከኃጢአት፣ ከራሳችንና ከራስ ወዳድነት ጋር እያደረግን ላለው ትግል--ዕብ. 4፡14-16 ምን ተገኝቶላችኋል ይለናል? ከጥቅሶቹ ብርታትና ተስፋ ማግኘት የምንችለው እንዴት ነው?**

**ማክሰኞ** **የካቲት 27**

## ክርስቶስን ማዕከል ያደረጉት ኃይማኖታዊ አስተምህሮዎች

ታላቁ የደኅንነት እውነት እና የመስቀሉ ትርጉም የተገለጸበት መቅደሱ የሁሉም ነገር ማዕከላዊ ክፍል ነው፡፡ ሁሉም ኃይማኖታዊ ትምህርቶቻችን በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ከወንጌል ተስፋና ደኅንነት ጋር መቆራኘታቸው የግድ ነው፡፡ ስለ ሠረገላው ተሸከርካሪ አካል እንደተነገረው የሌሎች ኃይማኖታዊ አስተምህሮዎች ምንጭ በየሱስ የሚገኘው የታላቁ የጽድቅ በእምነት እውነት ነው፡፡

"የክርስቶስ ለኃጢአት ሥርየት መሆን የሁሉም እውነቶች ስብስብ ታላቅ እውነት ነው፡፡. . . የአዳኙን አስደናቂ መሥዋዕትነት የሚያጠኑ በጸጋና በዕውቀት ያድጋሉ፡፡" —Ellen G. White Comments, *The SDA Bible Commentary*, vol. 5, p. 1137.

**የሱስ በዮሐ. 14፡6 " 'እውነት' " ብሎ ስለ ራሱ ሲጠቅስ ምን ማለቱ ነው? ይህን ቃል ከዮሐ. 17፡17 ጋር ያስተያዩ፡፡ ከእውነት ጋር ምን እንፍጠር? (3 ዮሐ. 3)፡፡**

---------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------

የነገረ መለኮት ትምህርቶቻችን በማንነታችንና በምንመራበት አቅጣጫ ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ፡፡ ኃይማኖታዊ አስተምህሮዎች መስተዋል የማይችሉ ረቂቅ የነገረ መለኮት ጽንሰ ሀሳቦች አይደሉም፡፡ ሁሉም እውነተኛ አስተምህሮ በክርስቶስ ደኅንነት ላይ የተመሰረተ ሲሆን፤ እያንዳንዱ አስተምህሮ በተለያየ መንገድ በሕይወታችን ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይገባል፡፡ እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት--የማንነታችን ሥረ መሰረት ከማንኛውም ነገር በላይ በኃይማኖታዊ አስተምህሮአችን ውስጥ በጥልቀት ይገኛል ማለት ይቻላል፡፡ ከመጽሐፍ ቅዱስ የመነጩት አስተምህሮዎች የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ማንነት አቀዳጅተውናል፡፡

የመጋቢነት ሚና በየሱስ በተገለጠው መሰረት በመለኮት እውነት ውስጥ መኖር ሲሆን፤ በዚህ መሰረት መመላለስ በህይወታችን ላይ የአዎንታዊ የጥራት ባለቤት ያደርጋል፡፡ "በእርግጥ ስለ እርሱ ሰምታችኋል፤ በኢየሱስም እንዳለው እውነት በእርሱ ተምራችኋል፡፡ ቀድሞ ስለ ነበራችሁበት ሕይወት፣ በሚያታልል ምኞቱ የጎደፈውን አሮጌ ሰውነታችሁን አውልቃችሁ እንድትጥሉ ተምራችኋል፤ ደግሞም በአእምሮአችሁ መንፈስ እንድትታደሱ፣ እውነተኛ በሆነው ጽድቅ እንዲሁም ቅድስና እግዚአብሔርን እንዲመስል የተፈጠረውን አዲሱን ሰው እንድትለብሱ ነው፡፡" (ኤፌ. 4፡21-24)፡፡

እውነትን ማወቅ ብቻ ሳይሆን በእውነት መኖር ምን ማለት እንደሆነ ከጥቅሱ እንረዳለን፡፡ ኃይማኖታዊ አስምህሮዎች የቱንም ያህል ትክክል ሊሆኑ ቢችሉ-- መጋቢነት እነዚያን ትምህርቶች ማመን አይደለም፡፡ ይልቁንም መጋቢነት ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነት እውነትን በሕይወታችን ገልጦ ማሳየት ነው፡፡

## ረቡዕ የካቲት 28

# የሦስቱ መላእክት መልዕክት

በምድር ላይ የሚመጣውን ታላቅ ጥፋት አስመልክቶ እግዚአብሔር ሁለት ጊዜ ብቻ ማስጠንቀቂያ ሰጥቶአል፡፡ አንደኛው ለኖኅ ሲሆን (ዘፍ. 6፡13-18፣ ማቴ. 24፡37) ሁለተኛው--በሦስቱ መላእክት አማካኝነት የተሰጠው ማስጠንቀቂያ ነው (ራእ. 14፡6 -12)፡፡ እነዚህ መልእክቶች ወደፊት በምድር የሚከሰቱትን በዓይነታቸው ልዩ የሆኑ ትዕይንቶች የተሸፈኑበትን መጋረጃ ገልጠው ያሳያሉ፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ በመልእክቶቹ ዙሪያ ያለን ግንዛቤ እየበሰለ ቢመጣም ነገር ግን መልእክቱና ተልዕኮው አሁንም "የሦስተኛው መልአክ መልእክት በሆነው እውነት" ይኸውም ክርስቶስን በማመን በሚገኝ ጽድቅ ላይ መተማን ያደርጋል፡፡ —Ellen G. White, *Evangelism,* p. 190

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ራእ. 14፡6-12፡፡ የመልእክቶቹ ፍሬ ነገር ምንድን ነው? ለዓለም ምን እያሉ ነው? ከመልእክቶቹ አኳያ ምን ዓይነት ኃላፊነት ወድቆብናል? መጋቢነት ከመልእክቶቹ ጋር ተያያዥነት የሚኖረው እንዴት ነው?**

-------------------------------------------------------------------------------------------

እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት የእኛ ተልዕኮ ዓለም ለክርስቶስ ዳግም ምጽአት የሚዘጋጅበትን የሦስቱን መላእክት መልእክት ማቅረብ ነው፡፡ ዘላለማዊ ተጽእኖ ባለው በዚህ ጉዳይ ሕዝቦች ከውሳኔ መድረስ መቻል አለባቸው፡፡ በተልዕኮው ከእግዚአብሔር ጋር ሽርክና መፍጠር የመጋቢነት ሚና ነው (2ቆሮ. 5፡20፣ 6፡1-4)፡፡

"ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስቶች በዚህ ዓለም በተለየ ሁኔታ ጠባቂዎችና ብርሃን ተሸካሚዎች ናቸው፡፡ ለሚጠፋው ዓለም የመጨረሻው ማስጠንቀቂያ ለእነርሱ ተሰጥቶአል፡፡ ከእግዚአብሔር ቃል ላይ የሚነሳው አስደናቂ የብርሃን ጸዳል በእነርሱ ላይ ያንጸባርቃል፡፡ የመጀመሪያው፣ የሁለተኛውና የሦስተኛው መልአክ መልእክትን የማወጅ እጅግ የተከበረና የተቀደሰ ኃላፊነት ተሰጥቶአቸዋል፡፡ ከዚህ የላቀ ተፈላጊነት ያለው ሥራ ከቶ የለም፡፡ ምንም ዓይነት ነገር ትኩረታቸውን እንዲይዝ መፍቀድ የለባቸውም፡፡" —Ellen G. White, *Testimonies for the Church*, vol. 9, p. 19.

ከመሬቱ ጋር ከሚነካካበት ነጥብ ጋር ቁርኝት ያለው የተሸከርካሪው አካል ጠርዝ የሦስቱን መላእክት ተልዕኮ ይወክላል፡፡ የእነርሱ ተልዕኮ መንፈሳዊ መዋለልን መከላከልና በመጨረሻዎቹ ክስተቶች ወቅት የእኛን ኃላፊነት መወሰን ነው፡፡ ይህን መልእክት ለዓለም የምናውጅ መጋቢዎች መሆን አለብን፡፡

**ስለ መጨረሻዎቹ ክስተቶች ሲታሰብ በዚህ ጊዜ እንዲህ ይሆናል በሚሉ--የጊዜ ሠንጠረዦችን በማውጣትና በመመደብ መጠለፍ በቀላሉ ሊከሰት የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ በእርግጥ የጊዜ ሠሌዳዎች የራሳቸው ሚና ሊኖራቸው ቢችልም ነገር ግን መልእክቱን ለዓለም ለመስበክ ካለን ብርቱ ቁርጠኝነት አኳያ የሱስን እና የእርሱን ለእኛ መሥዋዕት መሆን በቀዳሚነትና በማዕከልነት የሚያስቀምጡ ለመሆናቸው እርግጠኞች መሆን እንችላለን?**

## ሐሙስ የካቲት 29

# መጋቢነት

ክርስቶስ የተቀደሰ ህይወት እንድንኖር ይፈልጋል፡፡ "ቅድስና" ን በጉልህ የሚያሳየው የእርሱ ሕይወት ፍጹም የሆነው መጋቢነት ሊኖረው የሚገባውን ገጽታ ይገልጣል (ዕብ. 9፡14)፡፡ ሕይወታችንን በዐደራ የተሰጠንን ሀብት እንዴት ማስተዳደር

እንዳለብን ባካተተና እግዚአብሔርን በሚያስደስት መንገድ መመራት አለበት፡፡ መጋቢነት የዚያ ቅድስና መገለጫ ነው፡፡

**ጥቅሶቹን ያመሳክሩ፡ 1ጴጥ. 1፡15-16፣ ዕብ. 12፡14፡፡ "ቅዱስ መሆን" እና "ቅድስና" ምን ማለት ናቸው? ይህ ከመጋቢነታችን ጋር እንዴት ይዛመዳል?**

-----------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------

ከመሬቱ ጋር ንክኪ የሚፈጥረው የሥረገላው ተሽከርካሪ ክፍል ዙሪያውን በብረት ሲለበጥ ረጅም ዕድሜ ሊኖረው እንደሚችል ሮማውያን ደርሰውበት ነበር፡፡ የዕደ ጥበብ ባለሙያው ብረቱን በእሳት እያጋለ ውጪያዊውን የጠርዝ ክፍል ይለብጠዋል፡፡ የጋለው ብረት የሚፈለገውን ቅርጽ ከያዘ በኋላ ቀዝቃዛ ውሃ ውስጥ ሲነከር ይኮማተርና በተሽከርካሪው ጠርዝ ዙሪያ ልክክ ብሎ ይቀራል፡፡ ከዚያም ተሽከርካሪው ክፍል በተዘወረ ቁጥር የተለጠፈው የብረት ክፍል ብቻ ከመሬቱ ጋር ንክኪ ይፈጥራል፡፡

በሠረገላው ተሽከርካሪ ክፍል ጠርዝ ላይ የተለበጠው የብረቱ ጫፍ የመጋቢነትን ጽንሰ ሃሳብ ይወክላል፡፡ ይህ እንግዲህ መንፈሳዊ ህይወታችን በተጨባጩ ህይወታችን ላይ ሲለበጥ የሚስተዋል ገሃዳዊ እውነታ ነው፡፡ ህይወታችን ከውጣ ውረዶች ጋር ተጋፍጦ የሚያልፍባቸው የውድቀትና የስኬት ጎዳናዎች ናቸው፡፡ በአባጣ ጎርባጣው የዕለት ከዕለት ህይወታችን እምነታችን በተጨባጭ የሚፈተንበት አካሄድ ነው፡፡ መጋቢነት ውጪያዊው እኛነታችን የተለበጠበትን ማንነት እና ምን ያደረግን እንደሆን ገልጦ ያሳያል፡፡ የባህሪ እና በአግባቡ እየተመራ ያለ ህይወት ምስክር ነው፡፡ ክርስቶስን የሚገልጡት የየቀኑ ተግባሮቻችን ከመንገዱ ጋር ቀጥተኛ ንክኪ እንዳለው የሠረገላው ተሽከርካሪ ክፍል ናቸው፡፡

በተግባር የሚገለጡት ድርጊቶቻችን በብርቱ ኃይል የተሞሉ እንደመሆናቸው ለክርስቶስ በሚኖረን ቁርጠኝነት ቁጥጥር ስር ሊውሉ ይገባል፡፡ "ኃይልን በሚሰጠኝ በእርሱ ሁሉን ማድረግ እችላለሁ" (ፊልጵ. 4፡13) በሚለው የዋስትና ቃል እና ኪዳን ልንኖር የግድ ነው፡፡

"በውስጣችን በሚሠራው መንፈስ ቅዱስ መቀደስ--የክርስቶስን ተፈጥሮ በሰብዓዊው ማንነት ውስጥ መትከል ነው፡፡ ሕያውና ንቁ መርኅ የሚከተለው ወንጌልን ያማከለ ኃይማኖት--ህይወቱ ክርስቶስ ነው፡፡ በታረቀ ባህሪና በመልካም ሥራ የተገለጠው የክርስቶስ ጸጋ ነው፡፡ የወንጌል መርኅዎች ከማንኛውም ተጨባጭ የዕለት ከዕለት የህይወት ክፍል መነጠል አይችሉም፡፡ እያንዳንዱ ክርስቲያናዊ የግንኙነት መስመርና ተግባር በክርስቶስ ያለውን የህይወት ተሞክሮ የሚወክል ሊሆን ይገባል፡፡" —Ellen G. White, *Christ's Object Lessons*, p. 384.

***እስቲ ወደ የቀኑ የህይወት ተሞክሮዎ መልከት ያድርጉ፡፡ እንደ አዲስ ፍጥረት--በውስጥዎ እየሠራ ያለውን ክርስቶስ በተጨባጭ ይገልጣል? የእርሱ ቅድስና በእርስዎ መገለጡን መመልከት እንዲችሉ ምን ዓይነት ብልህ ምርጫ ማድረግ ያስፈልጎታል?***

## **አርብ** **የካቲት 30**

***ተጨማሪ ሀሳብ*:** *የሠረገላ ተሽከርካሪ ውጫዊ ክፍል ከመሬቱ ጋር በሚያደርገው ፍትጊያ ከተወሰነ አገልግሎት በኋላ እየተለጠጠ ይሄዳል፡፡ ይህ ዳግም የማስተካከል ሥራ ራሱን ብረቱን አግሎ መቀጥቀጥ፣ ማረቅና የመሳሰሉትን ሰፊ ሥራ ይጠይቃል፡፡ ብረቱን ወደ ቀድሞው ለመመለስ የሚደረገው ይህ የማስተካከል ሥራ በቅድስና ውስጥ የሚገኘውን መጋቢነት በተጨባጭ ይወክላል፡፡ በሂደት የቱንም ዓይነት ከባድ ውጤት ሊከተል ቢችል--ለእያንዳንዱ አነስተኛም ሆነ ግዙፍ የህይወት ፈርጅ ምላሻችን በክርስቶስ አስተሳሰብ የተቃኘ ይሆናል፡፡ በዚህ መሰረት ለገንዘብ አጠቃቀማችን፣ ለቤተሰባዊው ወይም ለአሠሪና ለሠራተኛ ግንኙነት--ለሁሉም የምንሰጠው ምላሽ እንደ ክርስቶስ ፈቃድ ይሆናል፡፡ ሆኖም ብዙዎቻችን በሚገባ እንደምናስተውለው አንዳንዴ እነዚህን ትምህርቶች የምንማረው "ምከረው፣ ምከረው እምቢ ካለ መከራ ይምከረው" የሚለውን ብሂል እየተከተልን ነው፡፡*

*ቅርጹን ያጣውን ብረት ወደ ቀድሞው መመለስ ቀላል ሥራ እንደማይጠይቅ ሁሉ፤ የሰውንም ጸባይ ማረቅ ከባድ ነው፡፡ እስቲ ስለ ጴጥሮስ ተሞክሮ ያስቡ፡፡ የሱስ በነበረበት የማይጠፋው ጴጥሮስ የሱስ እንዲህ ይለኛል ብሎ አልጠበቀም--"'እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ ጸለይሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን*

አበርታ' " (ሉቃስ 22፡32)፡፡ ጴጥሮስ በየሱስ ላይ ክህደት ከፈጸመ በኋላ የተለወጠ ህይወት ባለቤት ለመሆን ቢበቃም፤ ነገር ግን ይህ የሆነው በአስቸጋሪና ከባድ የመከራ ተሞክሮ ውስጥ ካለፈ በኋላ ነበር፡፡ አሁን የጴጥሮስ መጋቢነት እንደገና ትክክለኛውን ቅርጽ ያዘ፡፡ ጴጥሮስ አዲስና የተለወጠ ሰው ሆነ፡፡ ህይወቱ ወደ አዲስ አቅጣጫ ማምራት ጀመረ፡፡ ሆኖም ይህ መሆን የቻለው እውነተኛ ዋጋ ከከፈለ በኋላ ነበር፡፡

## መወያያ ጥያቄዎች፡

❶ **ተግባራዊው የጽድቅ ሥራ የሱስ "'ከኋላዬ ሊመጣ የሚፈልግ ማንም ቢኖር ራሱን ይካድ፤ መስቀሉንም በየዕለቱ ይሸከም '" (ሉቃስ 9፡23) በማለት ከሰጠው መመሪያ ጋር ያለው ተዛምዶ ምን ይመስላል? በገላ. 6፡14-- መሰረት የተሰቀለው ምንድን ነው? ይህ የቅድስናን ሂደት እንዴት ያሳየናል? ተግባራዊው ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ማሰብ እንድንማር እንዴት ይረዳናል? 1ቆሮ. 2፡16፡፡**

❷ **ጌታን መከተልዎ እና የክርስትና ህይወት ጉዞዎ ያመጣው ፈተናና መራር ሁኔታ በሰጠዎት ብርቱ ትምህርት ዙሪያ ተሞክሮዎ ምን ይመስላል? በዚህ ዙሪያ ተሞክሯቸውን ለመናገር ምቾት ያላቸው የሰንበት ትምህርት ጥናት አባላት የተማሩትን ያካፍሉ፡፡ አንዱ ከሌላው ተሞክሮ ምን መማር ይችላል?**

❸ **እኛ እንደ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ከሌሎች የክርስትና ተቋማት በተለይ ስለ ያዝናቸው አስተምህሮዎች አሰብ ያድርጉ፡ ሰንበት፣ የሞቱ ሰዎች ሁኔታ፣ ፍጥረት፣ ዳግም ምጽአት. . . እነዚህ የተለያዩ የእምነታችን ክፍሎች በአጠቃላዩ አኗኗራችን ላይ ተጽእኖ የሚኖራቸው እንዴት ነው?**

# አስራ አንደኛ ትምህርት

ከመጋቢት 1 – 7

# የእያንዳንዱን ቀን ውሳኔ የሚሻው.. ዕዳ

**ሰንበት ከሰዓት**

**ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ መዝ.** 37:21፣ ማቴ. 4:3–10፣ ማቴ. 6:33፣ ዘዳ. 28:12፣ ምሳ. 13:11፣ ምሳ. 21:5፣ 2ቆሮ. 4:18፡፡

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡-**

"ለእያንዳንዱ የሚገባውን ስጡ፤ ግብር ከሆነ ግብርን፣ ቀረጥ ከሆነም ቀረጥን፣ መፈራት ለሚገባው መፈራትን፣ ክብር ለሚገባውም ክብርን ስጡ፡፡ ዕዳ አይኑርባችሁ፤ ባልንጀራውን የሚወድ እርሱ ሕግን ፈጽሞአልና፡፡ *(ሮሜ 13፡7-8)፡፡*

አንዳንዴ ገንዘብ መበደር ፈልገው ሊያበድርዎ ፈቃደኛ የሆነ ሰው ሲያገኙ ራስዎን እንደ ዕድለኛ ሊቆጥሩ ይችላሉ፡፡ ምናልባት ግለሰቡ እንዲያ ለማድረግ የወሰነው ከንጹህ መነሻ ምክንያት መንስኤነት--ይኸውም ከደረሰብዎ የገንዘብ ዕጥረት እንዲወጡ ለማገዝ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን በአብዛኛው ሲታይ ሰዎች በቅን ልቦና ተነሳስተው ገንዘባቸውን አያበድሩም፡፡ ይልቁንም ተጨማሪ ገንዘብ ፍለጋ በአራጣ መልክ ይሰጣሉ፡፡

ከዕዳ ለመራቅ የምንችለውን ሁሉ ማድረግ አለብን፡፡ እርግጥ ነው በአንዳንድ ሁኔታዎች ማለትም ቤት ወይም መኪና ለመግዛት፣ ቤተ ክርስቲያን ለመገንባት ወይም ትምህርት ለመማር--ገንዘብ መበደር ሊያስፈልገን ይችል ይሆናል፡፡ ነገር ግን

በተቻለ መጠን በአስቸኳይ ከዕዳው ለመውጣት አቅደን በብልሃት መከወን አለብን፡፡

ግን ጥንቃቄ ማድረግ አለብን፡፡ የሌለንን ገንዘብ ማባከን ለእግዚአብሔር ሕዝቦች "በባህሪያቸው ላይ እንዲሠለጥን ሊያደርግ ወደ ሚችለው የአጉል ምኞት እና የምድራዊው ሀብት ፍቅር መግቢያ መንገድ ነው፡፡ እነዚህ ባህሪያት እስከ ገዙን ድረስ ደጎንነትና ጽድቅ ከበስተ ኋላ ይቀራሉ፡፡" —Ellen G. White, *Early Writings,* p. 267.

ከዕዳ ለመራቅና በሥርዓት ለመመላለስ አቅማችን የፈቀደውን ሁሉ ማድረግ እንድንችል ከህሎቶቻችንንና ችሎታዎቻችንን ማሻሻል አለብን፡፡ በዚህ ሳምንት መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዕዳ ምን እንደሚል እንመለከታለን፡፡

## እሁድ ጥር 2

# መበደርና ማጥፋት

ነቢያቱና ኤልሳዕ እንጨት ሊቆርጡ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ወርደው "አንዱ ዛፍ እየቆረጠ ሳለ መጥረቢያው በሮ ከውሃው ውስጥ ወደቀ፤ እርሱም 'አየ ጉድ ጌታዬ፤ የተውሶ መጥረቢያ እኮ ነው!' ብሎ ጮኸ" (2ነገሥ. 6፡5)፡፡ "ተውሶ" ማለት የሌላ ሰው የሆነን ንብረት በባለ ንብረቱ ፈቃድ ወስዶ መጠቀም የሚል ፍቺ አለው፡፡ ይህ ፈቃድ አደጋ ሊያመጣ የሚችል ብርቱ ኃላፊነት ይዞአል፡፡ አንድ ሰው የተበደረውን ገንዘብ ያለ አግባብ ጥቅም ላይ ማዋሉን ተከትሎ የከፋ መዘዝ ሊመጣ ይችል እንደሆነ እንጂ ገንዘብ መበደር ወይም መጥረቢያ መዋስ--ስልቻ ቀልቀሎ፣ ቀልቀሎ ስልቻ እንዲሉ ሁለቱም ያው አንድ ናቸው፡፡

ገንዘብ የምንበደርበት ብቸኛው ምክንያት የተቸገርንበት ጉዳይ ላይ ለማዋል ነው፡፡ አደጋ ሊያስከትል የሚችለውን ብድር የመክፈል አቅም እንዳለን እና ለወደፊቱ ምንም ዓይነት የበጀት ጉድለት እንደማይኖር በማሰብ እንበደራለን፡፡ ሆኖም ግን የወደ ፊቱን አናውቅም (መክ. 8፡7)፡፡ ስለዚህ ገንዘብ መበደር ሁሌም አደጋ አለው፡፡

**የሚከተሉት ጥቅሶች ስለ ዕዳ ምን ይላሉ?**

መዝ. 37:21 ________________________________________________

መክ. 5:5 ________________________________________________

ዘዳ. 28:44, 45 ________________________________________________

ምናልባት በጥበብ እንጠቀመዋለን በሚል እሳቤ ገንዘብ እንበደር ይሆናል፡፡ ነገር ግን በብድር እጃችን የገባውን ገንዘብ ለማጥፋት መፈተናችን ወደ ሌላ አስቸጋሪ ሁናቴ ውስጥ ይከተናል፡፡ እርግጥ ነው የተበደርነውን ገንዘበ ማጥፋት አኗኗራችን ላይ ቀውስ በመፍጠር አቅማችንን ይፈታተናል፡፡ ለመበደር እየተፈተኑ የማጥፋት ባህል ደኻውንም ሆነ ሀብታሙን እያቃወሰ ያለ--የፍጆታው ገበያ የልብ ትርታ ነው፡፡ ለመበደር ስንፈተን የእግዚአብሔርን እርዳታ መማጸን የግድ ይሆናል (1ቆሮ. 10፡13) ምክንያቱም መበደር እርግማን ሊሆን ይችላልና (ዘዳ. 28፡43-45)፡፡

ገንዘብ የመበደር መጥፎ ልማድ አይጀምሩ፡፡ ከጀመሩም በተቻለ ፍጥነት ከፍለው ይጨርሱ፡፡ ገንዘብን ለአንገብጋቢ ጉዳይ ብቻ በማዋሉ ረገድ ብልህ እንሁን፡፡ እግዚአብሔር በብሩ ላይ የሾመን ጌቶች እንጂ--ዓለም ለገንዘቧ የካነችን አንሁን፡፡

በእርግጥ ገንዘብ ልንበደርባቸው የሚገቡ አንዳንድ ሁናቴዎች አሉ፡፡ ሆኖም በጥንቃቄና ሁሉንም የተበደርነውን መጠን በምንችለው ፍጥነት ለመከፈል በማቀድ ልንተገብረው ይገባል፡፡

**አጥብቆ በዕዳ መያዝ ምን ዓይነት መንፈሳዊ አደጋዎች ያስከትላል?**

## ሰኞ ጥር 3

# መጋቢነትና ቅጽበታዊው እርካታ

“ያዕቆብም ለዔሳው እንጀራና የምስር ወጥ ሰጠው፤ እርሱም ከበላና ከጠጣ በኋላ ተነሥቶ ሄደ፡፡ ዔሳው ብኩርናውን እንዲህ አድርጎ አቃለላት፡፡” (ዘፍ. 25፡34)፡፡ ዔሳው ስሜቱን ብቻ አጥብቆ የሚከተል አስቸጋሪ የውጭ ሰው ነበር፡፡ ቤት ደርሶ ወንድሙ የሠራው ምስር ወጥ እንደሸተተው ወዲያውኑ መብላት እንዳለበት

ተሰማው፡፡ ከዚህ ውጪ በረሃብ ልሞት ደርሻለሁ ማለቱ የማይመስል ነበር፡፡ በጠንካራ ውስጣዊ ስሜት ቁጥጥር ስር ውሎ የነበረው ዔሳው የጊዜያዊው ስሜቱ ግፊት የማመዛዘን ኃይሉ ላይ እንዲያይል በመፍቀድ፤ ብኩርናውን ለአንድ ጊዜ መብል ቅጽበታዊ እርካታ ሸጠው፡፡ ዔሳው ብኩርናው እንዲመለስ "በእንባ ተግቶ ቢፈልግም መልሶ ሊያገኘው አልቻለም" (ዕብ. 12፡17)፡፡

በተቃራኒው የየሱስ ምሳሌነት ተሰጥቶናል፡፡ የሱስ ለ40 ቀናት በመጾም ተርቦ በነበረበት ወቅት ሰይጣን ሦስት ጊዜ ፈተነው (ማቴ. 4፡3-10)፡፡ የሱስ ግን የቀረቡለትን ፈተናዎች ምንነት ከመመልከት ውጪ በዚያ በረሃብ በተዳከመና በዛለ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ስለ ሥጋው እርካታ አላሰበም፡፡ የሱስ ህይወቱን ሙሉ በኃጢአት የሚገኘውን ደስታና እርካታ ሲቃወም ኖሮአል፡፡ በዚህም እኛም በኃጢአት ላይ ኃይል ሊኖረን እንደሚችል አሳይቶናል፡፡ በብኩርናው ያልተደራደረው ወይም ብኩርናውን ያልሸጠም እርሱ--ሁላችንም አብረነው ወራሾች እንሆን ዘንድ ጥሪ ያቀርብልናል (ሮሜ 8፡17፣ ቲቶ 3፡7)፡፡ የሱስ በተፈተነ ጊዜ የሰጠንን ምሳሌ እየተከተልን ብኩርናችንን እንጠብቃለን (1ቆሮ. 10፡13)፡፡

ከምድራዊው ህይወት በኋላ ልምድ የምንቀስምበት ዕድል ስለሌለን፤ ይህ ዓለም ሊሰጠን የሚችለው ምርጥ ነገር ቢኖር ተሞክሮ ነው፡፡ ለራስ መኖር ለእግዚአብሔር ከመኖር ጋር ይቃረናል፡፡

**የሚከተሉት ጥቅሶች ቅጽበታዊ እርካታ በታማኝ ወገኖች ላይ ጭምር ሊያስከትል ስለሚችለው አደጋ ምን ያስተምሩናል? 2ሳሙ. 11:2–4፣ ዘፍ. 3:6፣ ፊልጵ. 3:19፣ 1 ዮሐ. 2:16፣ ሮሜ 8:8፡፡**

------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------

ለጊዜያዊው እርካታ የሚቋምጥ አእምሮ ያልተገራና በቁጥጥር ስር ያልዋለ የመሆኑ ምልክት ነው፡፡ ይህ የረጅም ጊዜ ዕቅድ ጠንቅ የሆነ ግልብ ባህሪ የትዕግሥት ጠላት እንደመሆኑ በተጠያቂነት ላይ እየተሳለቀ ጉዳት ያደርሳል፡፡ ለጊዜያዊው እርካታ የመቋመጥን ስሜት ማዘግየት መቻል የዕውቀትን መርኅ መከተል ነው፡፡ ልዩ ልዩ ግፊቶችንና የምንገኝባቸውን ሁናቴዎች በአግባቡ ለመምራት የሚረዳን የሕይወት

ክህሎት ነው፡፡ በተለይ ዓለም ከሚያቀርብልን የገንዘብ ብድር--ጥበብ በጎደለው አካሄድ ከመዘፈቅ የሚጠብቀን ነው፡፡ ሆኖም ይህ ጽንሰ ሃሳብ ዓለማዊ አወቃቀርን በተከተለው በፍጥነት ፍላጎትን የማርካትና በቅጽበት ሀብታም የመሆን ምድራዊ መላ ፊት ዝነኛ አይደለም፡፡ ፈጣን የሆነውን ቅጽበታዊ ደስታና እርካታ አንዴ ከተለማመድን በዚያ አናበቃም፡፡ ይልቁንም አሁንም፣ አሁንም እንፈልጋለን፡፡ ከእግዚአብሔር ስጦታዎች የተቀበልን መጋቢዎች በእንዲህ ዓይነቱ ወጥመድ መውደቅ የለብንም፡፡

## ማክሰኞ ጥር 4

# ገቢን ያገናዘበ አኗኗር

"በጠቢብ ቤት ምርጥ ምግብና ዘይት ተከማችቶ ይገኛል፤ ተላላ ሰው ግን ያለ የሌለውን ያሚጥጣል" (ምሳ. 21፡20)፡፡ ጥቅሱ እንደ ገቢው መጠን በኃላፊነት ቤቱን የሚያስተዳድረውን መጋቢ ከቅንጡውና አባካኙ ጋር በማነጻጸር ያቀርብልናል፡፡ ተላላ ሰዎች በገቢያቸው መጠን ለመኖር የሚያስችላቸውን ዕቅድ አያወጡም፡፡ ገንዘባቸውን በጥበብ ማስተዳደር ወይም በቁጠባ መኖር እንደ ማይፈለግ ምግብ--መከራ ሆኖ ስለሚሰማቸው ሥርዓት ወይም ረብ በጎደለው አካሄድ የተበደሩትን ሳይቀር እጃቸው ላይ ያለውን በሙሉ ያባክናሉ፡፡ ሆኖም እንደ ቤት ላለው ቋሚ ንብረት በጥንቃቄ መርምረንና በአቅማችን መኖር እንዳለብን አገናዝበን ልንበደር እንችላለን፡፡

ሀብታሞች ሀብታቸው ሳይነካ በበቂ ሁኔታ መተዳደር ይችላሉ፡፡ የእነርሱ ችግር ሁሌም ስለ ሀብታቸው መጨነቃቸውና እንዴት ሊጠብቁት እንደሚገባ ሌት ተቀን ማሰላሰላቸው ነው፡፡ ሰዎች ገቢያቸው በጣም አነስተኛ ሆኖ ደሞዝ ደረሰ አልደረሰ ብለው ግራ የሚጋቡ ከሆነ፤ ጭንቀታቸው ሀብት ማፍራት ሳይሆን--ህይወትን ጠብቆ ማቆየት ነው፡፡ የቱንም ያህል መጠን ያለው ገንዘብ እጃችን ላይ ቢኖር፤ በዚያው ልክ እንዴት መኖር እንዳለብን መጽሐፍ ቅዱስ ምክር ይሰጠናል፡፡ ጳውሎስ ህይወትን እጅግ ቀለል አድርጎ በማቅረብ "ነገር ግን ምግብና ልብስ ካለን፣ ያ ይበቃናል" (1ጢሞቴ. 6፡8) ሲል ምክሩን ይለግሳል፡፡ ምድራዊውን ሀብትና

ንብረት እጅግ አንገብጋቢ አድርጎ የማይመለከተው ጳውሎስ፤ ለእርሱ በክርስቶስ መኖር በቂ እንደሆነ ይናገራል (ፊልጵ. 1፡21)፡፡

ከምንም ነገር በላይ የትኛው መርኅ ሊታወስ የግድ ነው? ማቴ. 6፡33፡፡ በዚህ መልኩ ህይወታችንን መምራት እንዳለብን እንዴት እርግጠኞች መሆን እንችላለን?

-----------------------------------------------------------------------------------------------

ገንዘባችንን እንደ ገቢ ሳይሆን ነገር ግን በዐደራ እንድናስተዳድረው እንደ ተሰጠን ሀብት ልንቆጥር ይገባል፡፡ ዕቅድ ወይም በጀት ማውጣት ይህን ተግባር ለመፈጸም የምንጠቀምበት ዓይነተኛ ዘዴ ነው፡፡ ዕቅድ በጥልቅ ሊጠና የሚገባው ዕውቀት የሚሻ ክህሎት ነው፡፡ ሚዛናዊ በሆነ የገንዘብ ዕቅድ አስተዳደር ስኬታማ ለመሆን፤ በሥርዓት የታነጸ ተግባርና ጥረት አስፈላጊ ነው (ምሳ. 14፡15)፡፡ የመጋቢነት መርኅ ግብርን ተከትለን የገንዘብ አያያዝ ስኬት ላይ ለመድረስ ቁርጥ ሃሳባችን ከሆነ፤ ከቁጥጥር ውጪ የሆኑትን የገንዘብ አያያዝ ስህተቶች ማስወገድ እንችላለን፡፡

በገንዘብ አያያዝ ላይ ችግር ከገጠሞት ዕቅድ ያውጡ፡፡ ዕቅዱ የተወሳሰበ መሆን የለበትም፡፡ ለምሳሌ የጥቂት ወራቶችን አጠቃላይ ወጪ ድምር ሠርቶ የወሩን አማካይ ወጪ ማግኘት ይቻላል፡፡ ምንም ቢመጣ ፍንክች ሳንል በወጣው ዕቅድ መሰረት መኖር ዋናው ቁልፍ ነገር ነው፡፡ ይህን በማድረግ ከዕዳ መራቅ ይቻላል፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሉቃስ 14፡ 27-30፡፡ በጥቅሱ የሱስ ደቀ መዝሙርነት ስለሚያስከፍለው ዋጋ በምሳሌ ሲናገር፤ ህንፃ የሚሠራ ሰው ግንባታው የሚፈጅበትን ወጪ አስቀድሞ አስልቶ ወደ ሥራ እንደሚገባና--ማጠናቀቅ ካልቻለ ግን ምን ሊከሰት እንደሚችል ያሳየናል፡፡ ከዚህ ምሳሌ ስለ መጋቢነት ልናገኝ የሚገባው ትምህርት ምንድን ነው?**

## ረቡዕ ጥር 5

# ባለ ዕዳ መሆንን መቃወም

**ዘዳ. 28፡12 ብዙ ዕዳ ውስጥ ስለ መግባት ምን ያስተምረናል? በጥቅሱ በሥራ ላይ የምናየው መርኅ ምንድን ነው?**

ዕዳን በተቻለ መጠን ማራቅ እንዳለብን ብዙዎቻችን ይሰማናል፡፡ ሌላው ለተበደረው ነገር ተያዥ ወይም ዋስ መሆንን መጽሐፍ ቅዱስ አይበረታታም (ምሳ. 17፡18፤ 22፡26)፡፡ ዕዳ በነገ ላይ ተጽእኖ አሳድሮ ከዚያው ከምንገኝበት ደካማ የገቢ ሁኔታ ላይ መልሰን እንድንሰጥ ያስገድደናል፡፡ *አዳራሽ መጋበዝ ለመደና ሰዉ፤ **ዕዳ**ስ መብላት ሆነ የሚያስለቅሰው፤* እንዲሉ ክርስቲያኖች ከዚህ መራሩን ጣዕም የሚቀይር ከሚመስላቸው ዕዳ ለመታቀብም ሆነ እንዴት መምራት እንዳለባቸው ሲቸገሩ ይስተዋላሉ፡፡ ዕዳ ሥነ ምግባር የጎደለው ተግባር በሚል ባይፈረጅም፤ መንፈሳዊ ህይወታችንን ግን አያጠነክርም፡፡

"ቤታችንን ስናስተዳድር በበጀት አጠቃቀም ዙሪያ ቆምጨጭ ካላልን ከባድ ዕዳ ውስጥ ልንገባ የምንችልባቸው ሁናቴዎች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡ ያስቀመጡትን ገደብ ጥሰው አይውጡ፡፡ በሽታን እንደሚርቁ በራስዎ ላይ መከራ ሊያመጣ የሚችለውንም ዕዳ አጥብቀው ይራቁ፡፡

በብድር የተወሰደ ገንዘብ የአበዳሪ ግዞተኛ ያደርጋል--"ተበዳሪ የአበዳሪ ባሪያ ነው" (ምሳ. 22፡7)፡፡ ብድር ከዓለማችን ምጣኔ ሐብት ጋር ድርና ማግ ሆኖ በመጣመሩ እንደ ተለመደ ነገር እንወስደዋለን፡፡ ለነገሩ አገራት ሁሉ የሚንቀሳቀሱት በብድር አይደል? በተመሳሳይ ሰዎች ቢበደሩ ክፋቱ ምኑ ላይ ነው? እንዲህ ያለውን አስተሳሰብ መያዝ ስህተት ነው፡፡

"በአምላካዊው በረከት ዕዳዎን ከፍለው ይጨርሳሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ግን *ጎመን በጤና* ብለው ከማንኛውም ብድር ለመራቅ ከእግዚአብሔር ጋር ጽኑ ኪዳን ይግቡ፡፡ በአነስተኛ ወጪ በቂና የተመጣጠነ ምግብ በቤት አብስሎ መመገብ በጣም ቀላል ነው፡፡ እርስዎ ለዝርዝሮቹ ሳንቲሞች ከተጠነቀቁ ድፍኖቹ ብሮች ራሳቸውን ይጠብቃሉ፡፡ እዚህም እዚያም የምንዘራቸው ትናንሽ የሚመስሉ ሳንቲሞች ብዙም ሳይቆይ ዋናውን ብር ይዘው ይነጉዳሉ፡፡ በዕዳ አጥር ተከብበው እያሉ ቢያንስ ሳያቅማሙ ራስዎን ይካዱ፡፡ ባለ ዕዳ ለመሆን የመረጡበትን አስተሳሰብም ሆነ እንደ ፈለጉ የመሆንን ልል ፍላጎት ይካዱ--እያንዳንዷን ሳንቲም አጠራቅመው ብድርዎን ይከፈሉ፡፡ ከዚህ በኋላ በተቻሎት ፍጥነት ከዕዳ ያምልጡ፡፡ ዳግም ነፃ ሰው ሆነው በሁለት እግሮችዎ መቆም ከቻሉ በኋላ ከማንም ምንም አይበደሩ፡፡ ይህ ሲሆን

የታላቅ ድል ባለቤት ይሆናሉ፡፡" —Ellen G. White, *Counsels on Stewardship,* p. 257.

ዕዳ ክርስቲያኖችን ሊያቆም የማይችል ደካማ መሰረት ነው፡፡ መንፈሳዊ ተሞክሮአችንን ይጎዳል፤ የእግዚአብሔርን ሥራ በምንደግፍበት ችሎታ ላይም አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ ለሌሎች በልበ ሙሉነት ለመለገስ የሚያስችለንን ብቃት ከመዝረፉ በተጨማሪ--ከእግዚአብሔር በረከት ለመቀበል የሚያስችሉንን ዕድሎች ይሰርቃል፡፡

**አላስፈላጊ ባለዕዳነትን ለማስወገድ የሚረዱዎትን ምን ዓይነት ምርጫዎች አሁን ማድረግ ይችላሉ? ከዕዳ ነፃ ሆነው ለመኖር ምን ማድረግ ይኖርቦታል?**

**ሐሙስ** ጥር 6

# ቁጠባና የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት

ጉንዳኖች ለክረምት የሚሆናቸውን ቀለብ በበጋ ሠርተው ይሰበስባሉ (ምሳ. 6፡6-8)፡፡ እኛም ገንዘባችንን ለአንድ የተወሰነ ዓላማ ያለማቋረጥ ስንቆጥብ የእነርሱን አሠራር ማጤናችን ብልህነት ነው፡፡ የምንቆጥብበት ምክንያት ከማባከን በተቃራኒ ለኑሮ የሚያስፈልገንን ወጪ በበቂ ሁኔታ ለመያዝ ወይም የምናገኘውን ለማከማቸት ነው፡፡ ገንዘብ ማስተዳደር ብልሃትን፣ በጀት ማውጣትንና በዲሲፕሊን መምራትን ይጠይቃል፡፡ የምንቆጥበው ለራሳችን ብቻ ከሆነ--መጋቢዎች መሆን ሲገባን የእግዚአብሔርን ሐብት እየሰረቅን ነው፡፡

"በአላስፈላጊ መንገድ የሚጠፋ ገንዘብ በእጥፍ እንደ ባከነ ይቆጠራል፡፡ ገንዘቡ መጥፋቱ ሳያንስ የመቆጠብ ክህሎትንም ያዳክማል፡፡ ታዲያ ይህን ብር ለይተን አስቀምጠን ቢሆን ኖሮ በምድር በቁጠባ በተባዛ ወይም በሰማይ በመስጠት በበለጸገ ነበር. . . ቁጠባ በገንዘብ ላይ ያለንን ሥልጣን የሚያጎለብት መልካም ምግባር ነው፡፡ ሁሉ አማረሽ ሆነን ገንዘብ እንዲቆጣጠረን በመፍቀድ ፋንታ እኛ ራሳችን እንቆጣጠረው፡፡" —Randy C. Alcorn, *Money, Possessions and Eternity* (Carol Stream: Illinois, Tyndale House Publishers, 2003), p. 328.

**የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ምሳ. 13:11፣ ምሳ. 21:5፣ ምሳ. 13:18፡፡ ከገንዘብ ነክ ጉዳዮች ጋር በተሻለ እንድንሠራ ሊረዱን የሚችሉ ምን ዓይነት ተጨባጭ ቃላቶች ቀርበዋል፡፡**

-----------------------------------------------------------------------------------------

መጋቢዎች የእግዚአብሔርን ሀብት ሲያስተዳደሩ ለቤተሰባቸው የሚያስፈልገውን መጠን ይቆጥባሉ፣ በሰማይም የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት ያደርጋሉ፡፡ አንድ ሰው የቱንም ያህል ገቢ ሊኖረው ቢችል፤ ጉዳዩ ያለው የሚያገኘው የገንዘብ መጠን ላይ ሳይሆን--ምን ያህል መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የገንዘብ አስተዳደር ዕቅድ እየተገበረ ነው? የሚለው ላይ ነው፡፡ የቤተሰባችንን ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችለን ብልህ የቁጠባ ባህል መዘርጋት አለብን፡፡ የቁጠባን ዘዴ ማስፋት በዕጦት ሊገጥም ከሚችል አደጋ ለመጠበቅ ወይም መጠኑን ለመቀነስ ይረዳል (መክ. 11:1-2)፡፡ በዚህ መልኩ ቅድሚያ ለሚሻው ቅድሚያ እየሰጡ አላስፈላጊ ወጪን መቀነስና (ምሳ. 24:27) ከሌሎች ባለሙያዊ ምክር መፈለግ (ምሳ. 15:22) በዚህ ሞዴል--እነዚህ ሁለቱ አርአያነት ያላቸው ውጤታማ ዘዴዎች ናቸው፡፡ የምንፈልጋቸው ነገሮች እየተሟሉ ሲመጡና ሀብት እያፈራን ስንሄድ "እንድታፈራ ችሎታ የሰጠህ እርሱ ስለሆነ አምላክህን እግዚአብሔርን አስበው" (ዘዳ. 8:18) የሚለውን አምላካዊ ቃል ጠብቀን መራመድ ይኖርብናል፡፡

" *'መንግሥተ ሰማይ'* " (ማቴ. 13:44) የእግዚአብሔር መጋቢዎች መዋዕለ ንዋያቸውን የሚያፈሱበት ደኅንነቱ የተጠበቀ አስተማማኝ ስፍራ ምሳሌ ነው፡፡ የኤኮኖሚ መቀዛቀዝ፣ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ሥጋት ወይም ሌባ በዚያ የለም፡፡ እንደውም ፈጽሞ እንደማያረጅ የገንዘብ ቦርሳ ነው (ሉቃ. 12:33)፡፡ አንድ ሰው ክርስቶስን የግል አዳኙ አድርጎ ሲቀበል ይህን ሒሳብ ይከፍታል፡፡ አሥራትና ስጦታው የሒሳቡ ተቀማጮች ናቸው፡፡ ለፍጆታ የምንከፍላቸውን ወጪዎችና የመሳሰሉትን አስፈላጊ ምድራዊና ዓለማዊ ነገሮች በጥንቃቄ መያዝ ቢኖርብንም ነገር ግን ትኩረታችን ሁሌም በዘላለማዊ እውነቶች ላይ ሊሆን ይገባል፡፡

**ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡ 2ቆሮ. 4:18፡፡ ኃላፊነት እንደሚሰማቸው መጋቢዎች እየኖርን ይህን እውነት ሁል ጊዜ ከፊታችን ጠብቀን መጓዝ የሚኖርብን እንዴት ነው?**

## **አርብ** ጥር 7

***ተጨማሪ ሀሳብ፡-*** እያንዳንዱ በተፈጥሮ የሚገኝ ችሎታ፣ ስጦታ ወይም መክሊት አብሮን ሊወለድ ቢችል፣ ከትምህርት ወይም ከአካባቢያችን ወስደን ብናበለጽገው--ምንጩ ያው እግዚአብሔር ነው፡፡ የጉዳዩ አስፈላጊ ክፍል በችሎታዎቻችንና ክህሎቶቻችን ምን ልናደርግ ይገባል የሚል ነው፡፡ መጋቢዎች በትምህርትና በልምድ የችሎታዎቻቸውና የመክሊቶቻቸው ጌቶች እንዲሆኑ እግዚአብሔር ይጠብቃል (መክ. 10፡10)፡፡

ባስልኤል "በጥበብ፣ በችሎታና በዕውቀት፣ በማናቸውም ዐይነት ሙያ የእግዚአብሔር መንፈስ ሞልቶበታል" (ዘፀ. 25፡31)፡፡ እርሱና ኤልያብ (ዘፀ. 35፡34) የእነርሱን ጥበብ ለሌሎች የማስተማር ችሎታ ነበራቸው፡፡

በዚህ ቁሳዊ ዓለም ስንኖር በተለይ ዕዳን ከእኛ አርቀን መልካም መጋቢዎች ለመሆን የሚያስችለንን ትምህርት መማር እንችላለን፡፡ ሁሌም ቢሆን በንባብ፣ በዐውደ ጥናቶች፣ በመደበኛ ትምህርትና በመጨረሻም በልምድ ችሎታን ማጎልበት ከእኛ ይጠበቃል፡፡ መክሊቶቻችንን ማጎልበታችን ምርጥ የሆነውን ለእግዚአብሔር እንድናበረክትና መልካም መጋቢዎች እንድንሆን ያስችለናል፡፡

የመክሊቱ ምሳሌ እያንዳንዱ አገልጋይ " 'እንደ ችሎታው' " ተሰጥኦ መቀበሉን ያሳየናል (ማቴ. 25፡15)፡፡ ሁለቱ አገልጋዮች ተቀብለውት የነበረውን መክሊት በእጥፍ ሲያሳድጉ ሦስተኛው ግን መሬት ቆፍሮ ቀበረው፡፡ ሁሌም ቢሆን እጃችን ላይ ያለውን ነገር ለማጎልበትና ከፍ ያለ ደረጃ ላይ ለማድረስ ሌት ተቀን ልንተጋ ይገባል፡፡ በተረፈ መሬት ውስጥ ቀብሮ ማኖር የአንድን ግለሰብ ችሎታ ወይም ብቃት በምንም መልኩ አይገልጽም፡፡ ገንዘብን መቆጣጠርና ማስተዳደር፣ ከዕዳ መውጣት፣ በሥነ ስርዓት መኮትኮትና መዳበር፣ ብቃትን የሚያጎለብት ተግባራዊ ተሞክሮ ማድረግ--እነዚህ በእግዚአብሔር የተባረኩ አካሄዶች ናቸው፡፡ በሆነ ነገር ስኬታማና የተሻለ ለመሆን፤ ያንን ነገር ደግመን ደጋግመን ማድረግ ከእኛ ይጠበቃል፡፡

"የየቀኑ ህይወታችን በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ሲታነጽና ሲገነባ፤ አምላካዊው ቃል በጸባያችን ላይ ጥልቅና ዘላቂ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡ ጢሞቴዎስ እነዚህን ትምህርቶች ተምሮአል፤ በተግባር ላይም አውሏል፡፡ እርሱ ልዩ ተሰጥኦ ባይኖረውም፤ በእግዚአብሔር የተሰጠውን ችሎታ ለጌታ አገልግሎት በማዋሉ ምክንያት ሥራው የከበረ መሆን ችሎአል፡፡" —Ellen G. White, *The Acts of the Apostles*, p. 205.

## መወያያ ጥያቄዎች፡

**❶ ራስን መቆጣጠር ምንጊዜም ለክርስቲያኖች አስፈላጊ ቢሆንም ነገር ግን ለገንዘብ ቀውስ ብሎም ውድመት ሊዳርግ ከሚችል አካሄድ ራስን መቆጣጠር በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ እንደ ቤተ ክርስቲያን እንደዚህ ዓይነት ችግር ውስጥ ሊገኙ የሚችሉ ሰዎችን ለመርዳት ምን ማድረግ እንችላለን?**

**❷ ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡ ሮሜ 13፡7-8፡፡ እነዚህን ቃላት በዕለት ተዕለት ሕይወታችንና ከሌሎች ጋር ባለን ግንኙነት እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንችላለን?**

**❸ አንዳንዶች የሱስ በቅርቡ ስለሚገለጥ ዕዳ ውስጥ መግባታችን እምብዛም ሊያስጨንቀን አይገባም ሲሉ ይሞግታሉ፡፡ እርስዎ ለዚህ አባባል መልስዎ ምንድን ነው?**

# አስራ ሁለተኛ ትምህርት

ከመጋቢት 8 – 14

# የመጋቢው ልማዶች

**ሰንበት ከሰዓት**

***ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡*** ኤፌ. 5:15–17፣ ቆለ. 3:23፣ ሉቃስ 12:35–48፣ ያዕ. 4:14፣ ሐዋ. 3:21፣ 1ቆሮ. 9:24–27፡፡

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡-**

*"ጎልማሳ መንገዱን እንዴት ያነጻል? በቃልህ መሠረት በመኖር ነው፡፡ በሙሉ ልቤ ፈለግሁህ፤ ከትእዛዛትህ ፈቀቅ እንዳልል አድርገኝ፡፡ አንተን እንዳልበድል፣ ቃልህን በልቤ ሰወርሁ፡፡" (መዝ. 119:9-11)፡፡*

ልማዶችዎ የህይወትዎን ዓላማና አቅጣጫ ገልጠው ያሳያሉ፡፡ መልካም የሆኑትን ልማዶች የሚያጎለብቱ መጋቢዎች--በጣም ታማኝ መጋቢዎች ናቸው፡፡ ዳንኤል በየቀኑ የመጸለይ ልማድ ነበረው (ዳን. 6:10)፡፡ ወደ ምኩራብ መግባት ለጳውሎስ ልማዱ ነበር (ሐዋ. 17:1-2)፡፡ በተጨማሪ ጳውሎስ "'አትሳሳቱ መጥፎ ጓደኝነት መልካሙን ጠባይ ያበላሻል' " (1ቆሮ. 15:33) ሲል ጽፏል፡፡ መጥፎውን ባህሪ በመልካም ለመተካት መልካሙን ባህሪ መኮትኮትና ማዳበር ይጠበቅብናል፡፡

"ልማዶቻችን ግላዊ ማንነታችንን ለአሁንና ለዘላለም ቀርጸው ያኖራሉ፡፡ ትክክለኛውን ልማድ የሚተገብር ህይወት ባለቤት የሆኑና በማንኛውም የሥራ አፈጻጸም የታመኑ ሰዎች በሌሎች መንገድ ላይ የሚያበሩ የብርሃን ፈርጦች ይሆናሉ፡፡"—Ellen G. White, *Testimonies for the Church*, vol. 4, p. 452.

በጎ ልማድ የሚፈጥረው ጎዳና አንድ ሰው የተመኘውን ሽልማት ለማግኘት የሚረዳው ፈጣን መንገድ ነው፡፡ ልማድ ስር የሰደደ ውሳኔ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር አንድ ነገር ለማድረግ--ከማድረግ ውጪ ማሰብም አያስፈልግም--እንደማለት፡፡ ያ ልማድ የግለሰቡን ድርጊት ተከትሎ በጣም ጥሩ ወይም በጣም መጥፎ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ሣምንት መጋቢው የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት የሚያስችለውን ኀይለኛ ልምዶች እንመለከታለን፡፡

## እሑድ *መጋቢት 9*

# እግዚአብሔርን መሻት የማስቀደም--ልማድ

ሁላችንም ብንሆን ልማዶች አሉን፡፡ ጥያቄው--ምን ዓይነት ናቸው? ጥሩ ወይስ መጥፎ? የሚል ሲሆን፤ ከሁሉም መልካም ልምዶች በላይ አንድ ክርስቲያን እግዚአብሔርን በየቀኑ የማስቀደም መሻት በውስጡ ሊኖር ይገባል፡፡

"በየማለዳው ራስዎን፣ ነፍስዎን፣ አካልዎንና መንፈስዎን ለእግዚአብሔር ቀድሰው ይስጡ፡፡ በአዳኝዎ ላይ የአምልኮና የመታመን ልማዶችን አብልጠው ይመስርቱ፡፡" —Ellen G. White, *Mind, Character, and Personality*, vol. 1, p. 15. እንዲህ ዓይነት ልምድ ካለን ወደ ዘላለማዊ ህይወት በሚወስደው በጠባብ በር እንገባለን (ማቴ. 7፡14)፡፡

" 'ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይኑሩህ' " (ዘፀ. 20፡3) በማለት እግዚአብሔር ተናግሯል፡፡ የሱስ ከመሰረታዊ ፍላጎቶቻችን ዐውድ ሲናገር " 'ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን እሹ' " (ማቴ. 6፡33) ይላል፡፡ በተጨማሪ እንዲህ ተብለናል "'እናንተ ትፈልጉኛላችሁ፤ በፍጹም ልባችሁ ከፈለጋችሁኝ ታገኙኛላችሁ' " (ኤር. 29፡13)፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ማቴ. 22፡37-38፣ ሐዋ. 17፡28፣ ኤፌ. 5፡15-17፣ ቆለ. 3፡23፡፡ እግዚአብሔርን በሕይወታችን እንዴት ማስቀደም እንዳለብን የሚረዱን እነዚህ ጥቅሶች ምን ይላሉ?**

--------------------------------------------------------------------------------------

ጌታን ከሁሉ ማስቀደም እንዳለብን ከተሰጡን ምሳሌዎች ሁሉ የየሱስን ዓርአያነት የሚያህል የለም፡፡ የሱስ ከሁሉም ነገር በላይ አባቱን አስቀደመ፡፡ ይህን የማስቀደም ተግባር መመልከት የጀመረው ገና ብላቴና ሆኖ በፋሲካ በዓል ወቅት ከወላጆቹ ጋር ወደ የሩሳሌም በመጣ ጊዜ ነበር፡፡ ማርያም ከአጠገቧ ያጣችውን የሱስ "በቤተ መቅደስ" አግኝታው ይህ እንዴት ሊከሰት እንደቻለ ስትጠይቀው "በአባቴ ቤት መገኘት" ይገባኛል (ሉቃስ 2፡46-49) ሲል ነበር የመለሰው፡፡

ከጸሎት ልማድ ህይወቱ እንደታየው፤ የሱስ ህይወቱን ሙሉ ከአባቱ ጋር መሆን ምኞቱ ነበር፡፡ ይህን ልማዱን ደቀ መዛሙርቱ ሙሉ ለሙሉ አልተረዱም ነበር፡፡ የሱስ ከአብ ጋር ሙሉ ለሙሉ ጥምረት መፍጠር ልማዱ ማድረጉን ተከትሎ፤ ሁሉም የጨለማ ኃይላት ከአባቱ ሊነጥሉት አልተቻላቸውም፡፡

እግዚአብሔርን በሙሉ ልባችን፣ ሀሳባችንና ነፍሳችን ለመውደድ በመወሰን የየሱስን ምሳሌ መከተል እንችላለን (ማቴ. 22፡37፡፡ ዘወትር በመጸለይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል በማጥናትና የየሱስን ጸባይ ለመከተል በመመኘት፤ በምናደርገው ነገር ሁሉ እግዚአብሔርን በሕይወታችን ማስቀደም ልማዳችን ማድረግ እንችላለን፡፡ ደግሞስ ለክርስቲያኖች ከዚህ የተሻለ ምን ሊኖር ይችላል?

**እስቲ--እግዚአብሔርን ምን ያህል በህይወቴ አስቀድሜአለሁ? ብለው ራስዎን ይጠይቁ፡፡**

## ሰኞ *መጋቢት 10*

# የየሱስን ዳግም ምጽአት የመጠባበቅ--ልማድ

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሉቃስ 12፡35-48፡፡ ምሳሌያዊው ታሪክ ራሳችንን ከየሱስ ዳግም ምጽአት ጋር እንዴት ማገናኘት እንዳለብን ምን ያስተምረናል? ሁላችንም ዘወትር የምናደርጋቸው ነገሮች ከተጨባጩ ዳግም ምጽአት ዐውድ አኳያ ሊሆኑ የሚገባው ለምንድን ነው?**

---------------------------------------------------------------------------------------------

መጋቢነት በየሱስ ዳግም ምጽአት ብርሃን በተግባር ገልጠን የምናሳየው ልማድ መሆን አለበት፡፡ ታማኝ ሳይሆኑ--ታማኝ እንደሆኑ የሚያስመስሉ መጋቢዎች ባህሪ

ውሎ አድሮ በድርጊታቸው ይገለጣል፡፡ እውነተኛና ታማኝ መጋቢዎች ግን ጌታቸው አጠገባቸው ያለ ያህል ተግተው እየተጠባበቁና እየሠሩ ኃላፊነታቸውን ይወጣሉ፡፡ ለወደፊት እየኖሩ በየቀኑ በታማኝነት ይሠራሉ፡፡ "እኛ ግን አገራችን በሰማይ ነው፤ ከዚያ የሚመጣውንም አዳኝ፣ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በናፍቆት እንጠባበቃለን" (ፊልጵ. 3፡20)፡፡

አብርሃም ዘላለማዊቷን ከተማ የተጠባበቀ ሲሆን (ዕብ. 11፡10) ጳውሎስ ደግሞ የክርስቶስን ዳግም ምጽአት ተጠባብቆአል (ዕብ. 10፡25)፡፡ እነርሱ ስለ ወደፊቱ በጥልቅ የሚያስቡ፣ ተስፋ የሚያደርጉ፣ ዕቅድ የሚያወጡና በማንኛውም ቅጽበት የሱስን ለመገናኘት ዝግጁ የነበሩ ሰዎች ናቸው፡፡ እኛም የወንጌል መልእክት መደምደሚያ ወደ ሆነው የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ተስፋ አትኩረን የመመልከታችንን ልማድ ከማዳበር ወደ ኋላ አንበል (ቲቶ. 2፡13)፡፡ አልፎ አልፎ ወይም በድንገት ወደ ትንቢት ከማጮለቅ ይልቅ ክርስቶስ ሲመለስ ለሚጠብቀን ዘላለማዊነት ሁሌም ግንዛቤ ሊኖረንና ያለማቋረጥ እየተመለከትን፣ እየተጠባበቅንና እየሠራን ልንገኝ ይገባል፡፡ ይህን እያደረግን በምድር የመጨረሻ ጊዜያቶች ክስተት ዙሪያ የሚሰነዘሩ ወፍ ዘራሽና ምናባዊ መላ ምቶችን ከእኛ ማራቅ ይኖርብናል፡፡ የዳግም ምጽአቱ ተስፋ ለሕይወታችን አቅጣጫ በመስጠትና ስለ ዛሬው ትክክለኛ ግንዛቤ በማስጨበጥ በሕይወት ውስጥ አስፈላጊ የሆነውን ነገር እንድናስታውስ ይረዳናል፡፡ ወደ የሱስ ዳግም ምጽአት የመመልከት ልምድ ለመጋቢው ትርጉምና ዓላማ ይሰጠዋል፡፡

መስቀሉ ከአዳኙ ጋር ላለን ቀጠሮ መንገዱን ጠርጎልናል፡፡ ክርስቶስ በአባቱ ግርማ ከቅዱሳን መላእክት ጋር የሚመጣበትን ሁናቴ የሚያመላክቱንን በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጡ ምልክቶች እንጠባበቃለን (ማር. 8፡38)፡፡ "ስለዚህ ዐይናችን የሚያተኩረው በሚታየው ነገር ላይ ሳይሆን በማይታየው ላይ ነው፤ የሚታየው ጊዜያዊ ነውና፤ የማይታየው ግን ዘላለማዊ ነው" (2ቆሮ. 4፡18)፡፡

አዎን፤ ሁሌም በተጨባጭ በዙሪያችን ያለው የሞት ሁኔታ በዚህ ምድር ያለን ቆይታ ምን ያህል ውሱንና ጊዜያዊ መሆኑን እንድንገነዘብ ሊረዳን ይገባል፡፡ ደግሞም የዳግም ምጽአቱ ተስፋ ሞት ራሱ ጊዜያዊና ኃላፊ መሆኑን ያሳየናል፡፡ እንግዲያው እያንዳንዱ መጋቢ ክርስቲያን እንዴት መኖር እንዳለበት ተጽእኖ ሊያደርግ በሚገባ

ተስፋ--ይኸውም በክርስቶስ ዳግም ምጽአት ብርሃን የመመላለሱ ተገቢነት እምብዛም አይገርምም፡፡ የክርስቶስን ዳግም ምጽአት ተስፋ እየተጠባበቁ መኖር ለአሁንም ሆነ ለሁል ጊዜ ልማዳችን እናድርገው፡፡ መጠሪያ ስማችን በራሱ ተጠባባቂ የመሆናችንን እውነታ ይገልጣል፡፡

## ማክሰኞ *መጋቢት 11*

# ጊዜን በብልሃት የመጠቀም--ልማድ

" 'እኛ ትላንት ስለተወለድን አንዳች አናውቅምና፤ ዘመናችንም በምድር ሁሉ እንደ ጥላ ነውና' " (ኢዮ. 8:9)፡፡

እየሠራ ያለውን ሠዓት ማቆም ይቻል እንደሆን እንጂ እየከነፈ ያለውን ጊዜ ማቆም ግን ፈጽሞ አይታሰብም፡፡

***ካልተጠቀሙበት ተሸቀዳድመው ቶሎ፤***

***ጊዜ ታክሲ አይደለም አይጠብቅም ቆሞ፡፡***

እንደተባለው ምንም ሳንሠራ እጆቻችንን አጣጥፈን ብንቀመጥ፤ ጊዜ ይሄዳል፣ ይነጉዳል እንጂ ቆሞ አይጠብቀንም፡፡

**የሚከተሉት ጥቅሶች በዚህ በህይወት፣ በምድር ስላለን ጊዜ ምን ያስተምሩናል? ያዕ. 4:14፣ መዝ. 90:10-12፣ መዝ. 39:4-5፣ መክ. 3:6–8፡፡ በዚህ ምድር ያለን ጊዜ ምን ያህል የከበረ እንደሆነ አስመልክቶ ከጥቅሶቹ ልንወስድ የሚገባን መሰረታዊ መልእክት ምንድን ነው?**

------------------------------------------------------------------------------------------

ውሱን በሆነውና ዳግም መታደስ በማይችለው በጊዜ ውስጥ የምንመላለስ ክርስቲያኖች መልካም መጋቢዎች መሆናችን በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህ ህይወትና ለቀጣዩ፤ አስፈላጊ በሆነው ነገር ላይ ትኩረት እያደረግን፤ ጊዜን በጥበብ ጥቅም ላይ የማዋልን ልማድ ማጎልበት ይኖርብናል፡፡ *ጊዜ ወርቅ ነው፤ ግን አላፊ ነው*--እንዲሉ የእግዚአብሔር ቃል ጊዜን አስፈላጊ አድርጎ በሚገልጽልን መሰረት በከንቱ እንዳያልፍ በአግባቡ ልንዳኘው የግድ ነው፡፡ ምክንያቱም ጊዜ አንዴ ከሄደ መልሰን ልንጠቀመው አንችልም፡፡ ገንዘብ ቢጠፋብን--ቆየት ብለን፤ ምናልባትም

እጥፉን መልሰን እናገኘዋለን፡፡ ጊዜ ግን እንደዚያ አይደለም፡፡ አንዷ ሰከንድ አለፈች ማለት--ለዘላለም ነጎደች ነው፡፡ ምናልባት ያቺን ያለፈች ሰከንድ ወደ ኋላ ከመመለስ ይልቅ የፈሰሰን ውሃ ማፈስ ይቀል ይሆናል፡፡ በዚህ የተነሳ በእግዚአብሔር ከተበረከቱልን እጅግ የከበሩ ነገሮች መሃል አንዱ ጊዜ ነው፡፡ የተሰጠንን ጊዜ በአግባቡ ጥቅም ላይ የማዋል ልማድ ማጎልበታችን ምንኛ አስፈላጊ ነው!

"ዘመናችን የእግዚአብሔር ነው፡፡ እያንዳንዱ ደቂቃ የእርሱ እንደመሆኑ መልሰን ለእርሱ የማዋል እጅግ የከበረ የውዴታ ግዴታ አለብን፡፡ ማንንም ያለ አንዳች መከሊት እንዲሁ ያልተወው አምላክ ጊዜያችንን በአግባቡ ጥቅም ላይ እንድናውል በጥብቅ ይጠይቀናል፡፡

"የጊዜ ዋጋ ከስሌት በላይ ነው፡፡ ክርስቶስ እያንዳንዱን ጊዜ እንደ ከበረ ነገር ይመለከተው እንደ ነበር ሁሉ፤ እኛም የእርሱን ምሳሌ ልንከተል ይገባል፡፡ ህይወት እጅግ አጭር እንደመሆኗ ከንቱ በሆነው ቧልትና ፌዝ አናባክናት፡፡ ለዘላማዊው ህይወት ዝግጅት የምናደርግባቸው ጥቂት የሙከራ ጊዜያቶች ብቻ አሉን፡፡ ስለዚህ የምናባክነው፣ ለራስ ወዳዱ የግል ፍላጎት ወይም ለኃጢአት እርካታ የምናውለው ጊዜ የለንም፡፡" —Ellen G. White, *Christ's Object Lessons,* p. 342.

**"እንግዲህ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንደ ጥበበኞች እንዴት እንደምትኖሩ ተጠንቀቁ" (ኤፌ. 5፡15-16)፡፡ ጳውሎስ በዚህ መልእክቱ ምን ይነግረናል? ምክረ ሃሳቦቹን አሁን የምንገኝበት ሁናቴ ላይ ተግባራዊ ማድረግ የምንችለው እንዴት ነው?**

## ረቡዕ *መጋቢት 12*

# አዕምሮን፣ አካልንና ነፍስን ጤናማ አድርጎ የመጠበቅ--ልማድ

እኛ መጀመሪያ--በአእምሮ፣ በአካልና በመንፈስ ፍጹም ሆነን በእግዚአብሔር ተፈጠርን፡፡ ነገር ግን ኃጢአት እጹብ ድንቅ በነበረው ማንኛውም የፍጥረት ሥራ ላይ ውድመትና ጥፋት አደረሰ፡፡ እግዚአብሔር እኛ መጀመሪያ ወደ ነበረን ፍጹም ማንነት የመመለስ ሂደት ላይ መሆኑ መልካም የምስራች (ወንጌል) ነው፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሐዋ. 3፡21፣ ራእ. 21፡1-5፡፡ በጥቅሶቹ ምን ዓይነት ተስፋ እናገኛለን? የመጨረሻውን ዳግም መታደስ እየተጠባበቅን ዛሬን እንዴት ልንኖር ይገባል?**

ክርስቶስ በዚህ ምድር ይመላለስ በነበረ ጊዜ ሰብዓዊውን ፍጡር ለመጨረሻው ተሃድሶ ለማዘጋጀት--በመንፈስ፣ በአእምሮና በአካል የማነቃቃት ሥራውን ግንባር ቀደም ሆኖ ያለመታከት ሠራ፡፡ የየሱስ የፈውስ አገልግሎት እስከ መጨረሻው በተቻለ ጤናሞች ሆነን እንድንመላለስ የእግዚአብሔር ፍላጎት የመሆኑ ምስክር ነው፡፡ ሰለዚህ መጋቢዎች ጤናማውን የአኗኗር ዘይቤ እየተከተሉ አእምሮአቸውን፣ አካላቸውንና ነፍሳቸውን የማበልጸግ ልማድ ይከተላሉ፡፡

**በመጀመሪያ፡** አእምሮ አብልጦ ጥቅም ላይ እንዲውል በተደረገ ቁጥር--ይበልጥ እየበለጸገ፣ እየጎለበተ ይሄዳል፡፡ "በመጨረሻም ወንድሞች ሆይ፤ እውነት የሆነውን ሁሉ፣ ክቡር የሆነውን ሁሉ፣ ትክክል የሆነውን ሁሉ፣ ንጹሕ የሆነውን ሁሉ፣ ተወዳጅ የሆነውን ሁሉ፣ መልካም የሆነውን ሁሉ፣ በጎነት ቢሆን ወይም ምስጋና፣ እንደ እነዚህ ስላሉት ነገሮች አስቡ" (ፊልጵ. 4፡8)፡፡ እንዲህ ያለው አስተሳሰብ ሰላም ያመጣል (ኢሳ. 26፡3) ደግሞም "ሰላም ያለው ልብ ለሰውነት ሕይወት ይሰጣል" (ምሳ. 14፡30)፡፡ ጤናማው አእምሮአዊ ልማድ--ሰብዓዊው የኃይል ማዘዣ ጣቢያ ምርጥ አገልግሎት እንዲሰጥ ያስችለዋል፡፡

**በሁለተኛ ደረጃ፡** እንደ የአካል ብቃት እንቅስቃሴና ተገቢውን ምግብ የመመገብ መልካም የጤና አጠባበቅ ልማድ መኖሩ፤ ለራሳችን ጥንቃቄ እያደረግን መሆኑን ያሳያል፡፡ ለአብነት ያህል የአካል ብቃት እንቅስቃሴ የጭንቀት ስሜት እንዲሁም የደም ግፊት እንዲቀንስ ያደርጋል፣ ተለዋዋጩን ስሜት (ሙድ) ያሻሽላል፣ እንዲሁም በማንኛውም መድኃኒት ቤት መደርደሪያ ሊገኝ ከሚችል ጸረ-እርጅና መድኃኒት ይልቅ ፍቱኑ እርሱ ነው፡፡

**በሦስተኛ ደረጃ፡** መጋቢው ነፍሱን ለማበረታታት የሚያስችለውን መልካም ልማድ ያዳብራል፡፡ ነፍሳችንን ወደ እግዚአብሔር አንስተን (መዝ. 86፡4-5) እርሱን እንጠባበቅ (መዝ. 62፡5)፡፡ "ለእውነት ታማኝ ሆነን ስንመላለስ" (3ዮሐ. 3) ነፍሳችን ትበለጽጋለች "ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ ያለነቀፋ" ትጠበቃለች (1ተሰ. 5፡23)፡፡

**ስለ ልማዶችዎ አሰብ ያርጉና--በመንፈስዎ፣ በአካልዎ፣ በአእምሮዎና በጤናዎ ላይ ምን ዓይነት ተጽእኖ እያሳደሩ እንደሆነ ይመልከቱ፡፡ መሻሻል ያመጡ ዘንድ በከፊል**

**ወይም ሙሉ ለሙሉ ለውጥ እንዲያደርጉ የሚጠየቁባቸው ክፍሎች ይኖሩ ይሆን? የመጨረሻውን ተሃድሶ በሚጠባበቁበት በአሁኑ ወቅት የሕይወትዎ የጥራት ደረጃ እንዲሻሻል የትኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተስፋ የኔ ብለው ይይዛሉ? ምን ዓይነት ምርጫዎች ማድረግስ ይችላሉ?**

**ሐሙስ** *መጋቢት 13*

## ራስን የመግዛት፡ ልማድ

ራስን መግዛት ወይም በሥነ ምግባር መምራትና ማስተዳደር መጋቢው ሊኖሩት ከሚችሉ እጅግ አስፈላጊ ባህሪያት መካከል አንዱ ነው፡፡ "እግዚአብሔር የኀይልና የፍቅር፣ ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሀት መንፈስ አልሰጠንምና" (2ጢሞቴ. 1፡7)፡፡ ራስን በሥነ ምግባር ማነጽ ለሚለው ሃረግ የግሪክ አቻው ቃል *ሶፍሮኒስሞስ* ሲሆን በአዲስ ኪዳን ጥቅም ላይ የዋለው በዚህ ስፍራ ብቻ ነው፡፡ ቃሉ ሚዛን ጠብቆ መጓዝንና ከአምላካዊው መርኅዎች ያለማፈንገጥ ክህሎቶችን በውስጡ ይዞአል፡፡ ራስን በሥነ ምግባር መምራት "መልካሙን ከክፉ ለመለየት" (ዕብ. 5፡14) ይረዳናል፡፡ በዙሪያችን ያለውን ሁናቴ ለማስተዋል ያስችለናል፤ እንዲሁም ግፊቶችና ውድመት ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮች፤ የቱንም ዓይነት ውጤት ሊኖራቸው ቢችል እንኳ፤ በእርጋታና በትህትና ተቋቁመን ለማለፍ ያስችለናል፡፡ ከሳምሶን በተቃራኒ የነበረው ዳንኤል--በአናብስት ጉድጓድ ቢጣል እንኳ ከትክክለኛው ሥነ ምግባር ፍንክች አላለም፡፡ ባንጻሩ ከጥብቅ ሥነ ምግባር ያፈነገጠ ሕይወት ይመራ የነበረው ሳምሶን፤ ራሱን ለማረቅ ወይም ሚዛናዊውን አካሄድ ለመከተል ያሳየው ተነሳሽነት በእጅጉ አነስተኛ ነበር፡፡ በፈርዖን ቤት የነበረው ዮሴፍ ሥነ ምግባራዊውን መርኅ ሲከተል፤ ሰለሞን ግን በባዕድ አምልኮ ተዘፈቀ (1ነገሥ. 11፡4-5)፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ 1ቆሮ. 9፡24-27፡፡ ጳውሎስ ራስን ስለ መግዛት ምን ይላል?**

-----------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------

*"ዓለም ለሥጋ ፍላጎት ማርኪያ ውሎአል፡፡ ስህተትና ተረት ሰፍኖአል፡፡ ነፍሳትን ለማጥፋት የሰይጣን መሰናክሎች በዝተዋል፡፡ እግዚአብሔርን በመፍራት ራሳቸውን በፍጹም ቅድስና ለመጠበቅ የሚሹ ሁሉ ራስን የመግዛትና የመቆጣጠር ትምህርት መማር አለባቸው፡፡ የምግብ ፍላጎትና ስሜታዊ ግፊት ሁሉ ለአእምሮ ኃይል ተገዢ መሆን አለባቸው፡፡ ይህ ራስን የመቆጣጠር ችሎታ ከእግዚአብሔር ቃል የሚገኘውን የተቀደሰ እውነት ለማስተዋልና በተግባር ለመተርጎም የሚያስችለንን መንፈሳዊ የአእምሮ ጥንካሬ ለማግኘት አስፈላጊ ነው፡፡" የዘመናት ምኞት ገጽ 82-83 (አማርኛው ትርጉም)፡፡*

*ራስን መግዛት በዕለት ከዕለት ልማድ መዳበርና መሻሻል ይችላል፡፡ እግዚአብሔር-- ለእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ራሳችሁን አሠልጥናችሁ (1ጢሞቴ. 4:7) "በኑሮአችሁ ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ" (1ጴጥ. 1:15) ሲል ጥሪ ያቀርብልናል፡፡ መጋቢዎች ልዩ ችሎታና ብቃት እንዳላቸው አትሌቶችና ሙዚቀኞች፤ ራሳቸውን ለመግዛት የሚያስችላቸውን ልምምድና ሥልጠና ማድረግ አለባቸው፡፡ በእግዚብሔር ኃይልና ትጋት በተሞላው የገዛ ጥረታችን ግድ በሚሉ ጉዳዮች ዙሪያ ራሳችንን በሥነ ምግባር መምራትና ማስተዳደራችን የግድ ይሆናል፡፡*

***በዚህ በኃጢአት በወደቀና በተበላሸ ዓለም ታማኝ መጋቢዎች ሆነን ለመኖር የሚያስችለንን፤ ራስን በሥነ ምግባር የመምራት ኃይል በብቸኝነት ለሚሰጠን፤ ለእግዚአብሔር መገዛት መማር የምንችለው እንዴት ነው?***

## **አርብ** *መጋቢት 14*

***<u>ተጨማሪ ሀሳብ</u>፡*** *ጥቂቶች ብቻ ታማኝ ሆነው በቀሩባቸው ፍቅረ-ቁስ እና አመጸኝነት አብልጦ በተትረፈረፈበት በጥንቱ ዓለም፤ ሄኖክ እና ኖኅ ግን አረማመዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ ልማዳቸው አደረጉ (ዘፍ. 5:24፣ 6:9)፡፡ እነዚያን የመልካም መጋቢነት ዐደራዎች ሲወስዱ፤ የእግዚአብሔርን ጸጋ ተገንዝበው ተቀብለው ነበር፡፡*

*ከጥንት አንስቶ ለዘመናት ብዙዎች እንደ ሄኖክ እና ኖኅ አረማመዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር አድርገዋል፡፡ ለምሳሌ ዳንኤልና ጓደኞቹ "በአረማውያን የሐሰት ኃይማኖቶች መሃል የእውነተኛው ኃይማኖት ተወካዮች ሆኖው ለመቆም የአእምሮ ንጽህናና ፍጹም የሆነ ክርስቲያናዊ ባህሪ ሊኖራቸው የግድ መሆኑን ተገንዝበው ነበር፡፡ ደግሞም እግዚአብሔር ራሱ መምህራቸው ነበር፡፡ ተግተው መጸለያቸው፣*

በጥንቃቄ ማጥናታቸውና ከማይታየው ጋር የጠበቀ ቁርኝት መፍጠራቸው እንደ ሄኖክ እነርሱም አረማመዳቸውን ከእግዚአብሔር ጋር እንዲያደርጉ አስቻላቸው፡፡" —Ellen G. White, *Prophets and Kings,* p. 486.

"አረማመድን ከእግዚአብሔር ጋር ማድረግ" የመጋቢውን ድርጊት በመግለጽ በምድር ህይወቱ ነጋ ጠባ ከእግዚአብሔር ጋር መኖሩን ያሳያል፡፡ ብልሁ መጋቢ በተበላሸው ዓለም ውስጥ እየኖረ አረማመዱን ግን ከእግዚአብሔር ጋር ያደርጋል፡፡ በተመሳሳይ እኛም ከእግዚአብሔር ጋር እንዲህ ዓይነቱን ግንኙነት በመፍጠር ብቻ በክፉው ከመዘረር ወደ ማሸነፍ መሸጋገር እንችላለን፡፡

ታማኝ መጋቢ መሆን ሁሉንም የህይወታችንን ክፍል ባካተተ መልኩ ከእግዚብሔር ጋር በስምምነት መጓዝ መጀመር ይጠይቃል (አሞጽ 3፡3)፡፡ በክርስቶስ መራመድ (ቆላ. 2፡6)፣ በአዲስ ሕይወት (ሮሜ 6፡4)፣ በፍቅር (ኤፌ. 5፡2)፣ በጥበብ (ቆላ. 4፡5)፣ በእውነት (መዝ. 86፡11)፣ በብርሃን (1ዮሐ. 1፡7)፣ ያለ ነውር (ምሳ. 19፡1)፣ በአምላካዊው ሕግ (ዘፀ. 16፡4)፣ በመልካም ሥራ (ኤፌ. 2፡10)፣ በቀጥተኛው መንገድ (ምሳ. 4፡26) እንድንጓዝ ተጠርተናል፡፡

## መወያያ ጥያቄዎች፡

**❶ ትህትና ምንድን ነው? በመጋቢው ህይወት የሚኖረው ሚናስ ምን ይመስላል? (ማቴ. 11:29፣ ኤፌ. 4:2፣ ፊልጵ. 2:3፣ ያዕ. 4:10)፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖረን አረማመድ ትህትና አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው? (ሚክ. 6፡8)**

**❷ ራስን በሚጎዳ መጥፎ ልማድ ውስጥ የታሰሩን ሰዎች ልንረዳ በምንችልባቸው መንገዶች ዙሪያ ተወያዩ፡፡ እርስዎ እንደ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባልነትዎ እነዚህን ወገኖች ለመርዳት ምን ማድረግ ይችላሉ?**

**❸ ክርስቲያን መጋቢዎች ሊኖሯቸው የሚገቡ ሌሎች መልካም ልማዶች ምንድን ናቸው? ቲቶ 2:7፣ መዝ. 119:172፣ ማቴ. 5:8**

**❹ ስለ ጊዜና በጊዜ ምስጢራዊነት ዙሪያ ተነጋገሩ፡፡ ለመሆኑ ጊዜን እንዲህ የሚያከንፈው ነገር ምንድን ነው? ጊዜ ምን እንደሆነ እንኳ ማስተዋል የምንችለው እንዴት ነው? በዚህ ምድር ካለን አጭር ቆይታ አኳያ መልካም መጋቢዎች መሆናችን አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?**

# እስራ ሶስተኛ ትምህርት

ከመጋቢት 15 – 21

# የመጋቢነት ውጤቶች

**ሰንበት ከሰዓት**

**ለዚህ ሣምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡** 2ጢሞቴ. 3:1–9፣ ሕዝ. 14:14፣ ፊልጵ. 4:4–13፣ ምሳ. 3:5፣ 1ጴጥ. 2:11-12፣ ማቴ. 7:23፣ 25:21፡፡

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡-**

“ምንም እንኳ ክፉ እንደምትሠሩ አድርገው ቢያሟችሁም ለፍርድ በሚመጣበት ጊዜ መልካሙን ሥራችሁን ዐይተው እግዚአብሔርን እንዲያከብሩ፣ በአሕዛብ መካከል በመልካም ሕይወት ኑሩ” *(1ጴጥ. 2:12)፡፡*

እኛ እንደ መጋቢነታችን የምናመልከው አምላክ ምስክሮች ሆነን መመላለስ ይጠበቅብናል፡፡ ይኸውም መልካም በሆነው ነገር ሁሉ በዙሪያችን ላሉ ብርቱ ተጽእኖ አሳዳሪ መሆን ነው፡፡

ከገሃዱ ዓለም ተነጥሎ መኖር የታሪካችን አካል አይደለም፡፡ ይልቁንም የተሰጡንን ነገሮች ለማያውቁ የተሻለውን የአኗኗር ዘይቤ የማንጸባረቅ ልዩ መብትና ጥቅም ተችሮናል፡፡ መጋቢነት እግዚአብሔርን እየመሰልን እንድንኖር ለቀረበልን ጥሪ ምላሽ እየሰጡ እያበቡና እየዳበሩ መሄድ ነው፡፡ እግዚአብሔር በምድር ከሚስተዋለው ማንኛውም ዓይነት የአኗኗር ዘይቤ በተለየ የምንኖርበትን ችሎታ ሰጥቶናል (2ቆሮ. 6፡17)፡፡ ሌሎች ይህን ተገንዝበው ምስጢሩን እስከ መጠየቅ ይደርሳሉ፡፡ “ክርስቶስን ጌታ አድርጋችሁ በልባችሁ ቀድሱት፡፡ እናንተ ስላላችሁ ተስፋ

ምክንያትን ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ሁል ጊዜ የተዘጋጃችሁ ሁኑ፤ ነገር ግን ይህን ሁሉ በትሕትናና በአክብሮት አድርጉት" (1ጴጥ. 3፡15)፡፡

በዚህ የሩቡ ዓመት የመጨረሻ ክፍል ትምህርታችን--መጋቢው በህይወቱ ሐሴት የሚያደርግባቸው ቁልፍ የሆኑ ግላዊ ጥቅሞች፣ መንፈሳዊ ውጤቶች፣ ስኬታማ ተግባሮችና ተጽእኖዎች ዙሪያ ምልከታ የምናደርግ ሲሆን ይኸውም "የክብር ተስፋ የሆነው በእናንተ ውስጥ ያለው ክርስቶስ" (ቆላ. 1፡27) መሆኑን እናውቅ ዘንድ ነው፡፡

## እሁድ *መጋቢት 16*

# መጋቢነትና እውነተኛ መንፈሳዊነት

እውነተኛ መንፈሳዊነት ትልቅ ርዕሰ ጉዳይ ነው፡፡ እውነተኛ መንፈሳዊነት ያላቸው ሕዝቦች ለአምልኮ ያዘነበሉና እርሱን ደስ የሚያሰኘውን በተግባር እየገለጡ፣ (መዝ. 4፡3፣ ቲቶ 2፡12) ክርስቶስን እየመሰሉ የተቀደሰ ኑሮ ይኖራሉ (ቲቶ 1፡1)፡፡ እውነተኛ መንፈሳዊነት የእውነተኛ ኃይማኖት ማሳያና የዘላለማዊ ሕይወት ተስፋ ቃል ነው፡፡ የትኛውም ምድራዊ ፍልስፍና፣ ሀብት፣ ዝና፣ ሥልጣን ወይም ከታላቅ መወለድ የዚህ ተስፋ ባለቤት አያደርግም፡፡

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ 2ጢሞቴ. 3፡1-9፡፡ ጳውሎስ ከታማኙ መጋቢ ሕይወት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ስላለው ጉዳይ የሚሰጠው ማስጠንቀቂያ ምንድን ነው?**

---

መጽሐፈ ኢዮብ ስለ ኢዮብ ጸባይና ድርጊቶች ገለጻ ያደርግልናል፡፡ በሥቃይና መከራ ውስጥም ሆኖ--እውነተኛ መንፈሳዊነት የተላበሰውን ገጽታ ያሳየናል፡፡ በተጨማሪ ሰይጣን እንደዚያ ያለውን አኗኗር ምን ያህል እንደሚጠላ ያሳየናል፡፡ የኢዮብን ምርጥ እምነትና አኗኗር ባለቤትነት ማንም ሊስተካከለው እንደማይችል እግዚአብሔር ራሱ ማረጋገጫ የሰጠበት ጉዳይ ነው (ኢዮ. 2፡3)፡፡

"ዖፅ በሚባል አገር የሚኖር ኢዮብ የተባለ ሰው ነበረ፤ ይህ ሰው ነቀፋ የሌለበት፣ ቅን፣ እግዚአብሔርን የሚፈራና ከክፋት የራቀ ነበር" (ኢዮ. 1፡1)፡፡ የኢዮብ እምነት ከቃላት ያልዘለለ ወይም ኃይማኖታዊ ሥርዓት ብቻ ያቀፈ ሳይሆን የህይወቱ ክፍል

እንደነበር ከጥቅሱ እንመለከታለን (ኢዮ. 1፡5)፡፡ እግዚአብሔርን መፍራቱ በአስከፊ የመከራ ወቅቶቹ እንኳ ሳይቀር በእውነተኛ መንፈሳዊነት በኖረው አጠቃላይ የሕይወት ዘመኑ በይፋ መታየት የቻለ ነበር፡፡ በእውነተኛ መንፈሳዊነት መኖራችን ፍጹምነትን በዙሪያችን እንድናንጸባርቅ ያስችለናል እንጂ ፍጹማን ነን ለማለት አያስደፍርም፡፡

**ጥቅሱን ያንብቡ፡ ሕዝ. 14፡14፡፡ ጥቅሱ ስለ ተወሱት ሰዎች ጸባይ ምን ዓይነት ምስክርነት ይሰጣል? በእኛ በሁላችንም ውስጥ መታየት ስላለበት ነገር በጋራ የያዘው ነጥብ ምንድን ነው?**

---

መጋቢነት በእርግጥም በእውነተኛ መንፈሳዊነት የምንኖረው ህይወት መገለጫ ነው፡፡ ታማኝ መጋቢዎች በእውነተኛ መንፈሳዊነት የሚመላለሱ ሲሆን፤ ይህ ማንነት በአኗኗራቸውና በተቀበሉት ዐደራ አያያዝ ይገለጣል፡፡ እምነታቸው በሚያደርጉት ነገር ብቻ ሳይሆን በማያደርጉትም ጭምር ይታያል፡፡

## ሰኞ *መጋቢት 17*

# እርካታ

"ይህን ስል ስለ ጉድለት አልልም፤ የምኖርበት ኑሮ ይበቃኛል ማለትን ተምሬአለሁና" (ፊልጵ. 4፡11 /1962 ትርጉም/)፡፡ በምንገኝበት የትኛውም ሁኔታ መርካት ከቻልን የእርካታችን ምንጩ ምን ሊሆን ይገባል?

---

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልእክት "መንፈሳዊው ነገር ትርፍ ማግኛ" ስለሚመስላቸው ከንቱ ሰዎች ይገልጻል (1ጢሞቴ. 6፡5)፡፡ ዛሬ በአገልግሎት ስም በየቴሌቪዥን ጣቢያው የሚነግዱትን ከዚህ የተሻለ ምን ሊገልጻቸው ይችላል? የጣቢያ ታዳሚዎቻቸው በገንዘባቸው ታማኝ ከሆኑ (ታማኝነታቸው የእነርሱን አገልግሎት በገንዘባቸው መደገፍን ያካትታል) እነርሱም ሀብታም ይሆናሉ… ማለት ነው? ሀብትን ከታማኝነት ጋር ማመጣጠን በክርስትና ጭምብል ሥር የሚገኝ ሌላው የቁሳዊነት መገለጫ ነው፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ እውነተኛ መንፈሳዊነትን ከሀብት ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም፡፡ እንዲያማ ቢሆን አንዳንድ የምድራችን አጸያፊዎች በሀብታቸው ብዛት ከመንፈሳዊዎች ተርታ በተመደቡ ነበር፡፡ በዚህ ፋንታ ጳውሎስ "እውነተኛ መንፈሳዊነት ባለን ነገር ከመርካት ጋር ትልቅ ትርፍ ነው" (1ጢሞቴ. 6፡6) ይለናል፡፡ የእግዚአብሔር ጸጋ በገንዘብ ከሚገኝ ማንኛውም ትርፍ ባሻገር የከበረ ዋጋ ያለው እንደ መሆኑ፤ በማናቸውም ሁናቴ በደስታ የተሞላ መንፈሳዊነት ከሁሉ የላቀ ባለጸግነት ነው፡፡ ስለዚህ "ምግብና ልብስ ካለን" (1ጢሞቴ. 6፡8) ደስተኞች ልንሆን ይገባል፡፡ በመጨረሻ--የቱንም ያህል ኖሮን ነገር ግን ዝንባሌአችን የበለጠ ለማግኘት ከሆነ--ባለን ነገር ልንረካ አንችልም፡፡

"ባለን ነገር መርካትና ደስ መሰኘት መንፈሳዊ ምስጢርን የያዘ ታላቅ ጥበብ ነው፡፡ ይህ በጥልቅ ሊጠናና ሊማሩት የሚገባ ሽሽግ ነገር ነው. . . ጣፋጭ፣ ውስጣዊ፣ የተረጋጋና በደርባባ መንፈስ የታቀፈው ክርስቲያናዊው እርካታ፤ በማናቸውም ሁናቴ ራሱን በነፃ የሚያስገዛና በአምላካዊው ጥበብና አባትነት ሐሴት የሚያደርግ ነው፡፡. . . በአስቸጋሪ ጊዜያቶችና ሁናቴዎች ወቅት የተናወጡ ልቦችን በእጅጉ የሚያጽናና ጠቃሚ የከበረ ቅባት የያዘ ሣጥን ነው፡፡"—Jeremiah Burroughs, *The Rare Jewel of Christian Contentment*, pp. 1, 3.

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡ ሮሜ 8:28፣ ዕብ. 13:5፣ ፊልጵ. 4:4–13፡፡ በእርካታ የተሞላን ሰዎች ሆነን እንድንኖር ሊረዱን የሚችሉ ምን ዓይነት ነጥቦች እናገኛለን?**

__________________________________________________________________________

## ማክሰኞ *መጋቢት 18*

## *መታመን*

**ጥቅሱን ያንብቡ፡ ምሳ. 3፡5፡፡ ምን ዓይነት ወሳኝ መልእክት ተላልፎልናል? በተለይ በመጨረሻው ክፍል በራሳችን ማስተዋል መደገፍ እንደሌለብን የሚያነሳው ነጥብስ? (ኢሳ. 55፡9፣ 1ቆሮ. 4፡5፣ 13፡12፡፡**

__________________________________________________________________________

የእግዚአብሔር መጋቢዎች መርኅና ዓላማ “በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፤ በራስህ ማስተዋል አትደገፍ” (ምሳ. 3፡5) የሚል ነው፡፡

እርግጥ ነው--ይህን መናገሩ እንጂ ማድረጉ ብዙውን ጊዜ ቀላል ላይሆን ይችላል፡፡ እግዚአብሔር ለእኛ ባለው ፍቅሩና ጥንቃቄው እናምናለን እያልን--አስቸጋሪ ነገር በገጠመን ቁጥር በተደጋጋሚ ራሳችንን ጭንቀት ውስጥ የማንከት ስንቶቻችን ነን? አንዳንዴ በገዛ ራሳችን ምናብ የወደፊቱን አስፈሪ አድርገን እንስላለን፡፡

ታዲያ እኛ እንደ መጋቢ በእግዚአብሔር መታመን የምንማረው እንዴት ነው? ይህን የምናደርገው በእምነት ወጥተን በምናደርገው ነገር ሁሉ ጌታን በመታዘዝ ነው፡፡ መተማመን ወይም እምነት መጣል የአእምሮ ውጤት እንደ መሆኑ፤ አእምሮ--ሁሉንም አሟጦ ጥቅም ላይ አያውልም፡፡ በተቃራኒው አብልጠን በጌታ በታመን ቁጥር በእርሱ ላይ ያለንም እምነት የዛኑ ያህል እያደገ ይሄዳል፡፡ እንደ ታማኝ መጋቢዎች መመላለሳችን ለእግዚአብሔር ያለንን ታማኝነት የምንገልጽበት መንገድ ነው፡፡ ይህ መታመን የመጋቢው መሰረትና አነሳሽ ኃይሉ እንደመሆኑ በሚሠራቸው ነገሮች ውስጥ በገሃድ ይታያል፡፡

“ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ ውደድ” (ማቴ. 22፡37) በሚለው ጥቅስ “ልብህ” የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ሁል ጊዜ በምሳሌያዊ መንገድ ጥቅም ላይ ሲውል እንመለከታለን፡፡ ይህም ውሳኔያችን የሚመጣው ማንነታችንን ከሚመሰክረው ውስጣዊው የግብረገብ እኛነታችን ነው--የሚል አንደምታ አለው፡፡ ይህ ደግሞ ጸባያችንን፣ ተነሳሽነታችንንና አሳቢነታችንን ያካትታል፡፡

ከቁጥጥራችን ውጪ በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ በእግዚአብሔር ላይ እምነት መጣል ወይም በእርሱ መታመን ቀላል ነው፡፡ ምክንያቱም በእርሱ ላይ እምነት ከመጣል ውጪ ሌላ አማራጭ የለንም፡፡ ይልቁንም ሙሉ ለሙሉ “ከልብ” መታመን የሚመጣው በቁጥጥራችን ስር ባለ ነበር ላይ ምርጫ ሲኖረንና በእግዚአብሔር ላይ ያለን መታመን በአንድ ወይም በሌላ መንገድ እንድንመርጥ መንስኤ ሲሆነን ነው፡፡

ሐዋርያት በሙሉ ልባቸው በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን እምነት ያሳያሉ፡፡ “ዛሬ በሥራው ከተሰማሩ ወገኖች በተመሳሳይ ደካማና ረዳተ-ቢስ ተፈጥሮ የነበራቸው

ቢሆንም፤ እነርሱ ግን ሙሉ መታመናቸውን በጌታ ላይ አደረጉ፡፡ እግዚአብሔርን በማንኛውም ነገር ምርጥ ጀማሪና ፈጻሚ አድርገው የሚመላለሱ ሁሉ የዚህ ባለቤት ይሆናሉ፡፡" —Ellen G. White, *Gospel Workers*, p. 25.

**እንደ እውነቱ ከሆነ አንድ ሰው ከቁጥጥሩ ውጪ ለሆነው ነገር በእግዚአብሔር መታመን ይቀለው እንደሆን እንጂ አይከብደውም፡፡ ጉዳዩ በተገላቢጦሽ በእርስዎ ቁጥጥር ስር ቢሆንስ? በእግዚአብሔር ላይ ያለዎት መታመን በምርጫዎ ላይ ተጽእኖ እንዲኖረው ይፈቅዳሉ?**

## ረቡዕ መጋቢት 19

# ተጽእኖአችን

"ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁ፤ አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ" (ኤፌ. 5፡8)፡፡ ጳውሎስ የልብን መለወጥ እንደ አደባባይ ትዕይንት ይገልጸዋል፡ "በብርሃን ብንመላለስ" (1ዮሐ. 1፡7፣ ኢሳ. 30፡21) በዕቅድ የሚመራውና ነጋ ጠባ በሌሎች የሚስተዋለው መጋቢነታችን በጨለማው ዓለም ላይ ተጽእኖ የሚያደርግ ብርሃን ይሆናል፡፡

የሱስ "እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ" ሲል ተናግሯል (ዮሐ. 8፡12)፡፡ በየቀኑ ከሰዎች ጋር ባለን መስተጋብር በማይናወጥ ባህሪ የእግዚአብሔርን ብርሃን እናንጸባርቃለን፡፡

**ለእግዚአብሔር ክብር የሚያመጣው መጋቢነታችን በሌሎች ያለው ዕይታ ምን ይመስላል? የድርጊቶቻችን ተጽእኖስ? ማቴ. 5፡16፣ ቲቶ 2፡7፣ 1ጴጥ. 2፡11-12፡፡**

________________________________________________________________________

መጋቢነት የእግዚአብሔርን ንብረት ማስተዳደር ቢሆንም፤ ዐደራና ኃላፊነቱ ግን ከዚያም ባሻገር ነው፡፡ መጋቢነታችን በቤተሰባችን፣ በማኅበረሰባችን፣ በዓለማችን ብሎም በዩኒቨርስ ፊት የተገለጠ ነው (1ቆሮ. 4፡9)፡፡ በተግባር የሚታየው መጋቢነታችን፤ የሰማያዊው መንግሥት መርኅ በህይወታችን ላይ ያለውን ኃይል ገልጦ ያሳያል፡፡ በዚህም በሌሎች ላይ ተነሳሽነት መፍጠርና አርአያ መሆን

እንችላለን፡፡ የአዳኙን ይሁንታ በያዘው ደግነትና መልካም ስብዕና ክርስቶስን ገልጠን እናሳያለን፡፡

እንዲሁም የሥራ ሥነ ምግባራችን ከመጋቢነት እሴቶቻችን ጋር ስምሙ ሊሆኑ የግድ ነው፡፡ ኃላፊነታችን የጻድቅ ሰው መጋቢነት የሚታይበት አንድ ደረጃ ነው፡፡ "ጽድቅህ እንደ ብርሃን፤ የአንተን ፍትሕ እንደ ቀትር ፀሐይ ያበራዋል" (መዝ. 27፡6)፡፡ መጋቢው በሥራ ቦታም ይሁን በሌላ ተጽእኖውን "በስውር ቦታ ወይም ከእንቅብ በታች" (ሉቃስ 11፡33) አይሸሽገውም፡፡ ይልቁንም በተራራ ላይ እንዳለች ከተማ በሰዎች ፊት ያበራዋል (ማቴ. 5፡14)፡፡ እንዲህ ያለውን ዓላማ መር ሕይወት ስንኖር በዙሪያችን ባሉ ወገኖች አእምሮና ልብ ተጽእኖአችንን እናሳድራለን፡፡

"እያንዳንዱ የተፈጥሮ አካል የተመደበበት ሥራ አለው፡፡ ኃላፊነቱንም ያለማጉረምረም ያከናውናል፡፡ ከመንፈሳዊ ነገሮች አኳያ እያንዳንዱ ወንድ ወይም እያንዳንዷ ሴት ግላዊ የሥራ ፍላጎት መስክና ኃላፊነት አለው/አላት፡፡ እግዚአብሔር የሚጠይቀው ፍላጎት በክርስቶስ ከተሰጠው ስጦታ ልኬት ጋር ተመጣጣኝ ነው፡፡... የከበረ ዋጋ ያለውን--የባህሪ ጽናት የተላበሰ ስብዕና የሚያሳዩበት የእርስዎ ጊዜና ልዩ ሙብት እነሆ አሁን ነው፡፡" —Ellen G. White, *This Day With God*, p. 243.

**የሥራ ሥነ-ምግባርዎ አብረዋቸው በሚሠሩ ወይም በሚኖሩ ፊት ምን ዓይነት ተጽእኖ አለው? ስለ እምነትዎ የሚያስተላልፉላቸው መልእክት ምን ዓይነት ነው?**

## ሐሙስ *መጋቢት 20*

# ልንሰማ የምንፈልጋቸው (እና የማንፈልጋቸው) ቃላቶች

እኛ ፍጹም፣ ውብና ሰላማዊ የሆነው ሰማይ የመጨረሻ ግባችን የሆነ፣ የምድር መጻተኞችና ተጓዥ መንገደኞች ነን (ዕብ. 11፡13-14)፡፡ ሆኖም እስከ ጊዜው ድረስ ህልውናችን በዚህ ምድር ላይ ነው፡፡ በዚህ ዘመን ከእግዚብሔር ወይም ከሰይጣን ጎራ ከመሰለፍ ውጪ መሃል ሰፋሪ የሚባል ነገር እንደሌለ--በተለይ የታላቁ ተጋድሎ የክርስትና ዓለም አቀፋዊ ገጽታ ይፋ ያደርግልናል፡፡ "'ከእኔ ጋር ያልሆነ ሁሉ ይቃወመኛል፤ ከእኔም ጋር የማይሰበስብ ይበትናል' " (ማቴ. 12፡30)፡፡

**ክርስቶስ ዳግም ከተገለጠ በኋላ--እርሱን ተከትለናል የሚሉ ወገኖች ከነዚያ ሁለት ሐረጎች አንዱን ይሰማሉ፡፡ እነዚህ ሐረጎች ምንድን ናቸው? የእያንዳንዳቸውስ ፍቺ ምንድን ነው?**

*ማቴ. 25:21*____________________________________________________

*ማቴ. 7:23*____________________________________________________

"'ደግ አድርገሃል'" በሚል በክርስቶስ የሚነገሩት ቃላት መጋቢው ለመስማት የሚመኛቸው አስደሳችና አርኪ አባባሎች ናቸው፡፡ ብቃት በጎደለው ሰብዓዊ ማንነታችን--እንደ ችሎታችን መጠን መለኮታዊውን ሀብትና ንብረት የምናስተዳድርበት አምላካዊ ፈቃድ በማግኘታችን በቃላት ሊገለጽ የማይችል ደስታ ያጎናጽፈናል፡፡ የደኅንነታችን ሥረ መሰረት እኛ ለክርስቶስ የምንሠራው ሳይሆን እርሱ ለእኛ የሠራልን የመሆኑን እውነታ ጠንቅቀን እንገነዘባለን (ሮሜ 3፡21፤ 4፡6)፡፡

የታማኝ መጋቢ ህይወት የግለሰቡ ተጨባጭ እምነት ነጸብራቅ ነው፡፡ አንዳንዶች ራሳቸውን በእግዚብሔር ፊት ጻድቅ አድረገው ለማቅረብ የተመኙበት--የጽድቅ በሥራ አካሄድ ግለሰቦቹ በተናገሯቸው ቃላት መታየት ችሎ ነበር (ማቴ. 7፡21-22)፡፡ ማቴ. 7፡23--ራስን ስለማመጻደቅ ከንቱነት በትክክል ያሳየናል፡፡

"የክርስቶስ ተከታዮች የጌታ የሆነውን መልሰው ለእርሱ ሲሰጡ 'ደግ አድርገሃል አንተ መልካም ታማኝ አገልጋይ፤...ወደ ጌታ ደስታ ግባ' የተሰኙትን ቃላት በመስማት የሚሰጣቸውን ገጸ በረከት ከወዲሁ ያከማቻሉ፡፡' " —Ellen G. White, *The Desire of Ages*, p. 523.

በመጨረሻም፤ መጋቢነት የሰበበ ድርጊትና የትጉ ሥራ መንፈስ ኃይል የሆኑትን--እግዚአብሔርን ውደድ እና ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ--ሁለት ታላላቅ ትእዛዛት በህይወት መኖር ነው፡፡

**የገዛ ሕይወትዎ እና በመጋቢነት የተገለጠው ሕይወትዎ እነዚህን ሁለት ታላላቅ ትእዛዛት ምን ያህል በሚገባ አንጸባርቀዋል?**

## አርብ መጋቢት 21

**ተጨማሪ ሀሳብ፡** "ክርስቶስ ወደዚህ ምድር የመጣው የእግዚአብሔርን ፍቅር ለመግለጽ ነው፡፡ ተከታዮቹ እርሱ የጀመረውን ሥራ መቀጠል አለባቸው፡፡ አንዱ ሌላውን በመደገፍና በማበረታታት ጥረት እናድርግ፡፡ ለሌሎች መልካም መሻት እውነተኛ ደስታ የምናገኝበት መንገድ ነው፡፡ ሰው እግዚአብሔርንና ባልንጀራውን የሚወድ ከሆነ ወደ ገዛ ጥቅሙ አያዘነብልም፡፡ መንፈሱ ከራስ ወዳድነት በራቀ ቁጥር ይበልጥ ደስተኛ ይሆናል፡፡ ለዚህ ምክንያቱ እግዚአብሔር ለእርሱ ያለው ዓላማ ጠልቆ ስለሚሰማው ነው፡፡"—Ellen G. White, *Counsels on Stewardship*, pp. 24, 25.

"በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሕይወት ባለ ቁጥር--መብዛትና ማደግ አለ፡፡ የራሱ የጌታ የሆነውን የመቀበልና የመስጠት፣ የመቀበልና የመመለስ ቋሚ መለዋወጥ አለ፡፡ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ አማኝ ብርሃንና በረከት ይሰጣል፡፡ አማኙ ደግሞ ለጌታ በሚሠራው ሥራ ለሌሎች በልግስና የመመለስ ተግባር ይፈጽማል፡፡ ከሚቀበለው ላይ ሲሰጥ የመቀበል አቅሙ ይጎለብታል፡፡ ለትኩሱ ጸጋ እና እውነት አቅርቦት ስፍራ ይዘጋጃል፡፡ ግልጽነት የተላበሰ ብርሃንና መጠኑ የጨመረ ዕውቀት የእርሱ--የግለሰቡ ይሆናሉ፡፡ የቤተ ክርስቲያን ሕይወትና ዕድገት በዚህ መስጠትና መቀበል ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የሚቀበል ግን የማይሰጥ--ውሎ አድሮ መቀበል ያቆማል፡፡ እውነት ከእርሱ ወደ ሌሎች መፍሰስ ካልቻለ የመቀበል አቅሙን ያጣል፡፡ ትኩስና ለምለም የሆነውን በረከት የምንቀበል ከሆነ፤ ይህን ሰማያዊ ገጸ በረከት ማካፈላችን የግድ የሆናል፡፡"—Ellen G. White, *Counsels on Stewardship*, p. 36.

## መወያያ ጥያቄዎች፡

❶ **በጌታ መታመን ወደ እርካታ የሚመራን እንዴት ነው? በሙሉ ልብዎና ዕውቀትዎ በእግዚአብሔር ወደ መታመን የሚመራዎ እንዴት ነው? 2ቆሮ. 10፡5፡፡ "ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ እንዲሠራ" (ሮሜ 8፡28) ለማለት የሚቀለው--ለማመን ግን የሚከብደው ለምንድን ነው? ማለትም--**

በእግዚአብሔር እንታመናለን የሚለው የዕውቀት ደረጃ ስለ ወደፊቱ ሲያስብ በፍርሃት የሚዋጠው ለምንድን ነው?

❷ የሚከተሉትን ጥያቄዎች የሰንበት ትምህርት ጥናት አባላትን ይጠይቁና መልሶቹን ያስተያዩ፡፡ "መጋቢነትን በ25 ቃላት ወይም ባነሰ ያብራሩ፡፡" "መጋቢነት የክርስትና ህይወት አስፈላጊ ክፍል የሆነው ለምንድን ነው?"

❸ ጥቅሱን ደግመው ያንብቡ፡ ማቴ. 7፡21-23፡፡ ምን እየሆነ ነው ያለው? እነዚህ ሰዎች ስላደረጓቸው ነገሮች የሚያወሩት ለምንድን ነው? ንግግራቸው ስለ ራሳቸው ምን ይጠቁማል? መልካም መጋቢዎች ለመሆን ባለን ብርቱ ፍላጎት፣ የእምነትና የመታዘዝ ሕይወት ለመኖር በምናደርገው ጥረት፣ በእግዚአብሔር ስም መልካም ነገሮችን ለማድረግ በምናደርገው ያላሰለሰ ሙከራ—ተመሳሳይ ራስ ማታለል ውስጥ ላለመውደቃችን እንዴት እርግጠኞች መሆን እንችላለን?

❹ ስለ ክርስትና ተጽእኖ ስናስብ ቀድሞ ወደ አእምሮአችን የሚመጣው ግላዊው ምሳሌነት ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንዎ ደረጃ መደረግ የሚችለው ተጽእኖስ? በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያንዎ በማኅበረሰብዎ ላይ ምን ዓይነት ተጽእኖ አላት?

**የትንቢት መንፈስ መጻሕፍትን ተርጉሞና አሳትሞ ማሰራጨት ለሚፈልጉ ግለሰቦችም ሆነ ድርጅቶች የተሠጠ**

# <u>ማሳሰቢያ</u>

የትንቢት መንፈስ *(Spirit of Prophecy - SOP)* መጻሕፍት በሙሉ የሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት አለም አቀፍ ቤተክርስቲያን ንብረት ናቸው፡፡

እነዚህን ጽሁፎች በከፊልም ሆነ በሙሉ ወደ አማርኛም ሆነ ወደ ተለያዩ የአገሪቱ ቋንቋዎች በማስተርጎምና በማሳተም ለማዳረስ የሚፈልግ ግለስብም ሆነ ድርጅት፣ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት ለኢትዮጵያ ዩኒየን ሚሽን የጽሁፍ ክፍል ጥያቄውን በጽሑፍ በማቅረብና በአካልም ቀርቦ በመወያየት ወደ ሰምምነት ከተደረሰ በኋላ ትርጉሙ፣ ህትመቱና ስርጭቱ በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ተከናውኖ ሥራውን መፈፀም ይቻላል፡፡

በዚሁ መሠረት የትንቢት መንፈስ ጽሁፎችን በማሳተም ወንጌልን ለማዳረስ የሚጥሩ ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች በእጅጉ ይበረታታሉ፡፡

ሆኖም ግን ይህንን በመተላለፍ ያለ ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ዓለም አቀፍ ቤተ ክርስቲያን ፈቃድ በቤተክርስቲያኗ ስም የትንቢት መንፈስ ጽሁፎችን አሳትሞ ማስራጨት፣ በአገሪቱም ሆነ በዓለም ዓቀፍ የሥነ ጽሁፍ ህግ ያስጠይቃል፡፡ በተጨማሪም ድርጅቱ እያስተረጎመ ያለውን መጽሐፍ ሌላ አካል ተመሳሳዩን መጽሐፍ በመተርጎም ላልተፈለገ የጊዜ፣ የጉልበትና የገንዘብ ወጪም ይዳርጋል፡፡

ሰለሆነም የቤተክርስቲያኗ ህግና መተዳደሪያ ደንብ በሚፈቅደው መሠረት ሁላችንም ጽሁፎችን በማሳተምም ሆነ በማሰራጨት የሶስቱን መላዕክት መልዕክት ለማዳረስ እንድንችል ጌታ ይርዳን፡፡

***ድርጅቱ***

# ዓለም አቀፍ አድቬንቲስት ሬዲዮ
# የተስፋ ድምፅ

## ትግርኛ

ጠዋት 12:00 - 12:30
9530 Khz 31 ሜ.ባንድ
ማታ 1:30 - 2:00
15130Khz 19 ሜ.ባንድ
አየር ሞገድ

**አድራሻ**

ስልክ +251 115 511199
የውስጥ መስመር 205
ወይም
+251 910 145105

## አማርኛ

ጠዋት 12:30 - 1:00
15500 Khz 19 ሜ.ባንድ
ማታ 2:00 - 2:30
17570Khz 16 ሜ.ባንድ
አየር ሞገድ

**አድራሻ**

ስልክ +251 115 511199
የውስጥ መስመር 242
ወይም
+251 911 137222

ፖ.ሳ.ቁ 145 አዲስ አበባ

## ኦሮምኛ

ጠዋት 12:00 - 12:30
15500 Khz 19 ሜ.ባንድ
ማታ 2:30 - 3:00
15155 Khz 19 ሜ.ባንድ አየር ሞገድ

**አድራሻ**

ስልክ +251 115 511199
የውስጥ መስመር 237
ወይም +251 921 600938

---

የተላለፉ ፕሮግራሞችን እንደገና ለማዳመጥ ከመረጃ መረባችን www.awr.org ላይ በመግባት እንደገና ማግኘት ይችላሉ፡፡

---

የዓለም አቀፍ አድቬንቲስት ሬዲዮ የ24 ሰዓት
የአማርኛ ቋንቋ ስርጭትን በክርስቲያን ቻናል ጣቢያ
ውስጥ ከዚህ በታች በተቀመጠው መሰረት ያገኙታል

HC The Voice of Hope
Frequency: 12574
Symbol Rate: 09700
Polarity: Horizontal
Satellite: Intel Sat 68.5E
LNB: KU BAND

በተጨማሪም
በአሜሪካ ያሉ አድማጮቻችን 712 432 9970
በመደወል እንዲሁም
በእንግሊዝ ያሉ 033 001 03890 በመደወል
ፕሮግራሞቻችንን በማንኛውም ሰዓት
ማዳመጥ ይችላሉ

**የዓለም አቀፍ አድቬንቲስት ሬዲዮ የተስፋን ድምፅ ያዳምጡ**
**ለወዳጆችዎ በማስተዋወቅና በመጋበዝ የበረከቱ ተካፋይ ይሁኑ**